“ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ድንገት ነው እጇ ላይ የወደቀችው “
ዶ/ር ታዬ ንጉሴ

የፍቺው ዜና የፈጠረው ተስፋ
በፍቃዱ ዘ ሀይሉ

በእሥር ላይ የሚገኙት የዋልድባ መነኮሳት

አድዋ በጎሰኞች ዓይን
ዳንኤል ክብረት


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን

# ግዮን

ልዩ ዕትም


መልካም የአድዋ በዓል!


ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 1 የካቲት 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99




# ከመፈታት በኋላ መታሰር!




ግዮን መጽሔት

ልዩ ዕትም

ቅጽ 1 ቁጥር 1 የካቲት 24 2010 ዓ.ም

# ማውጫ




## አድዋ በጎሰኞች ዓይን 9

4 «ዛሬ ሲፈራ የነበረው ወገን ልጓሙን በጥሷል»
ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

6 ኢህአዴግ
በቁልቁለት ወይስ በለውጥ መንገድ ላይ ?

8 «ባለፉት 27 ዓመታት የኖርነው አንድ ቀን ነው »
አሕመድ ሙስጠፋ

10 " ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ድንገት ነው እጄ ላይ የወደቀችው "
ዶ/ር ታየ ንጉሴ

12 «ይህ ሕዝብ ነፃነት! ፍትሕ! ክፍታ! ይገባዋል!!!»
አንዱዓለም አራጌ

«አደባባይ የወጣነው ሰው እንዲሞት ፈልገን አይደለም»
ወይዘሪት ንግሥት ይርጋ
14

"የጎንደርን ሕዝብ ችግር በደንብ እጋራለሁ"
አቶ በቀለ ገርባ
16

«ማታ ማታ ዓይኔ ተሸፍኖ በሰንሰለት ታስሬ ለሴት ልጅ የማይገባ ዘግናኝ ጭካኔ ተፈጽሞብኛል»
እማዋይሽ ዐለሙ
18

20 የፖለቲከኛ እሥረኞች አፈታትና የኢሕአዴግ የሐሳብና የተግባር አንድነት ችግር

22 ክብር ለዐድዋ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን፣ ክብር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት!

24 "ከህዝቡ ጋር ሆነን አገራችንን በጋራ የምናድንበት መስመር ይኖረናል "
ማሙሸት አማረ

26 "ኢህአዴግ ይታረማል ብዬ አላስብም"
ተስፋሚካኤል አበበ (አበበ ቀስቶ)

28 «ፖሊስ ባጠፋው ጥፋት፣ ባወደመው ንብረት ልንከሰስ አይገባም ነበር»
አህመዲን ጀበል

29 "በግፍ መታሰራችን ትግላችንን የበለጠ አጠናክረን ለመቀጠል ምክንያት ይሆነናል"
ናትናኤል መኮንን

30 "ሁሌም ነፃነት ይናፍቀኛል"
ሲና ሰለሞን

31 "የምሰራው ስራ ከፖለቲካ ጋር አያገናኘኝም"
ኤልያስ ክፍሌ

32 የፍቺው ዜና የፈጠረው ተስፋ
በፍቃዱ ዘ ሀይሉ

# የግዮን መልዕክት

ግዮን ባለግርማ ወንዝ ነው፡፡ ግዮን በታላቅ ኃይል የሚፈስ ውሃ ነው፡፡ ግዮን መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት እንደሚለው ኢትዮጵያን የሚከብብ ወንዝ ነው፡፡ ረዥም ርቀት የሚጓዝ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የሰው ልጆች ሕይወት ተስፋ የሆነ ውሃ ነው፡፡ ከሣቴ ብርሃን የተባለውና በተሰማ ኃብተ ሚካኤል ግፀው ተዘጋጅቶ በ1947 ዓ.ም የታተመው የአማርኛ መዝገበ-ቃላት ትርጓሜ ‹‹ግዮን›› የእኛ መታወቂያ የሆነውና ኢትዮጵያን ‹‹የአፍሪካ የውሃ ማማ ›› ያሰኘው የወንዛችን ዓባይ መጠሪያ ነው፡፡ ግዮን የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ‹‹ጊሆን››፣ በግብፆች ‹‹ጌኦን›› የሚለው ቃል አቻ ነው፡፡ ወደ አማርኛ ሲመለስ ‹‹ዓባይ›› የሚለው ቃል የሚተካው ‹‹ግዮን›› የግዕዝ ቃል ሲሆን፤ ፍቺውም ‹‹ዘየሐውር በኃይል ወይርም በድምፀ ማዩ ዐቢያ ወግሩም›› እንዲሉ ነው፡፡

ይኸው ደግሞ የኢትዮጵያ ሞገስ፣ ግርማና በታላቅ ግርማ በሚፈሰው ወንዛችን የግዕዝ መጠሪያ፤ የኢትዮጵያውያን የፍቅር፣ የሕብረት፣የአንድነት መንፈስ ጎልብቶ ፍፁም በሆነ ሕጋዊና ሰላማዊ አቅጣጫ በኢትዮጵያችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይመሰረት ዘንድ ብዙኃኑን የሚያግባቡና የሚያስማሙ፣ ከጥላቻና ከቂም ታሪክ ቆፋሪነት የራቁ ጠቃሚ፣ የተዋቡና አመርቂ የኢትዮጵያዊነት ሐሣቦችን ለማስተናበር ግዮን! ብለን መጥተናል፡፡ የግዮን መጽሔታችን ዋና ዓላማም መልካሙን የኢትዮጵያዊነት ገጽታ ማጉላት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ዜጎቿ የሚኮሩበት፣ የሚመኩበትና የሚስማሙበት የጋራ ታሪክ፣ ባሕልና ማሕበራዊ እሴት የሚጠበቅበትን፣ የሚዘምንበትንና አቅጣጫ በማመላከት፤የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የፍቅር ኃይል በሚበጀው የሥልጣኔና የብልጽግና ጎዳና ላይ በመራመድ ተጠቃሚ የሚሆንባቸውን ባለርዕይ ሐሣቦችን ማንሸራሸር ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያችንና ለኢትዮጵያዊነት የሚበጀው፤ ከቂም፣ ከጥላቻ፣ ከአንድ ወገን ብቸኛ አውቃለሁ ባይነት የግትርነት አስተሳሰብና አመለካከት ርቆ ለጋራ ሀገር እና ለብዙኃኑ ሕዝብ ዘላቂ ሰላምና ጥቅም በአስተዋይነት ማሰብ ስለሆነ፤ ከዚህ የተወደደ ተግባር አንፃር መንግሥት የህሊናና የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት ላሳየው መልካም ጅምር ያለንን አክብሮት መግለጽ እንወዳለን፡፡ የኢትዮጵያውያን፣ የመላው አፍሪካዊያንና የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ኩራት የሆነውን፣ በፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል አንፀባራቂና ሕያው የሚሆን ስም ያለውን የዓድውን ድል122ኛ ዓመት መታሰቢያ በተመለከተ የተሰጠውን ልዩ ትኩረትም እናደንቃለን፡፡ አክብሮት
አድናቆታችንን ከመግለጻችንም በሻገር መንግሥት እና ገዥው ፓርቲ በመልካም ጅምሩ፣ በይቅርታና በምህረት ርምጃው ወደፊት ይቀጥል፤ ሀገርና ዜጎች ይበልጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ተጨማሪ የዴሞክራሲና የፍትሕ ማስፈኛ አማራጮችን ለመቃኘትም ይትጋ እንላለን፡፡

በመሆኑም በመጽሔታችን የመጀመሪያ ዕትም መንግሥት በወሰደው ይበል የሚያሰኝ አቋም መሠረት፤ ከእሥር ነፃ በሆኑት የህሊና እና የፖለቲካ እሥረኞችና ተያያዥነት ባላቸው ወቅታዊ ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ አትኩረናል፡፡፡ ይሁንና አብዛኛውን የመጽሔቷን ገጽ የተውነው፤ ከእሥር ከተፈቱት ዜጎች መካከል የተወሰኑት፤ የታሠሩበትን ምክንያት፣ በእሥር ያሳለፉትን ጊዜ በተመለከተ፣ የእነሱ መፈታት በሀገራችን ፖለቲካዊ ሂደት ላይ ምን አስተዋጽዖ አንደሚያበረክት እንዲናገሩና ሐሣብ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ነው፡፡ በተረፈ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው በነበራቸው የቀናኢነት ስሜት ዓድዋ ላይ የአንፀባራቂ ድል ባለቤት እንደሆኑት ሁሉ፤ በወደፊቷ ኢትዮጵያ መኖር የሚገባው ዴሞክራሲም እንደ ግዮን ውሃ ረዥም ርቀት የሚጓዝ፣ በመቶ ሚሊዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ተስፋ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ስለዚህም መጪው ትውልድ በነፃነት ስሜት የሚራመድበት፣ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ሐሴት እያደረገ ሊኖር የሚችልበት የዴሞክራሲ ሐውልት ለማቆም፣ የሀገራችንን ወቅታዊና ነባራዊ ችግር ለመቅረፍ፤ፖለቲከኞቻችን በትዕግስትና በማስተዋል ይሥሩ የሚለው መልዕክታችን ነው፡፡


**ጥቅምት 2010 ዓ.ም ተመሰረተ**

**ግዮን የሕትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማ**

ማኔጂንግ ዳይሬክተር:
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋና አዘጋጅ:
ፍቅር ሰይድ

አድራሻ:
አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

የልዩ ዕትም ተሳታፊዎች:

ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ሰለሞን ለማ
በፍቃዱ ዘ ሀይሉ
ሁሴን ከድር
ተረፈ ወርቁ
በታምራት መርጊያ

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 912165606
+251 912165606
ኢ-ሜይል:
gihonmeg@gmail.com
Facebook
gihon2010meg@gmail.com

አታሚ
ለታሪክ ማተሚያ ቤት
ስል ቁጥር: 0911515568
ቦሌ ክ/ከ የቤት ቁጥር 504/ሀ



# ‹‹አልባሳታችንን እንድንለውጥ መገደድ ማለት በእግዚአብሔር ስም የተሰጠንን ክብር እንዲዋረድ ማድረግ እንደሆነ ይሰማናል››

## በእሥር ላይ የሚገኙት የዋልድባ መነኮሳት

በእነ ተሻገር ወ/ሚካኤል ክስ መዝገብ የተከሰሱት እነ አባ ገ/ እየሱስ ኪ/ማርያም እና አባ ገ/ስላሴ ወ/ኃይማኖት (የዋልድባ መነኮሳት) ፤ መንግሥት ‹‹ክሳቸው ተቋርጦ›› በምህረት ወይም በይቅርታ ከእሥር ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ተብለው በብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ በኩል በጉጉት የሚጠበቁ ነበሩ። ይሁንና የወልድባዎቹ መነኮሳት መጽሔታችን የኅትመት ዝግጅቷን እስካጠናቀቀችበት የካቲት 21 ቀን 2010 ዓ.ም ምሽት ድረስ፤ ክሳቸው ስለመቋረጡም ይሁን ስለ መፈታታቸው ጉዳይ የተሰማ ዜና የለም። ይህም ሆኖ ብዙዎች መንግሥት ሌሎች የህሊና እሥረኞችን፣ ፖለቲከኞችንና ስለ ዕምነታቸው ሲሉ ሰላማዊ መፍትኄ ለማፈላለግ ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው የታሠሩ የኃይማኖት ሰዎችን እንደፈታው ሁሉ፤ እነዚህንም አባት መነኮሳት ከእሥራት ነፃ እንዲያደርጋቸው እየጠየቁ፣ መልካሙን እየተመኙ ነው። መነኮሳቱ ደግሞ በበኩላቸው በእሥር ላይ እያሉ ‹‹እየተፈፀመብን ነው›› የሚሉትን በደል ጉዳያቸውን ለሚመለከተው ፍ/ቤት በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። ለማንኛውም መንግሥት ይበል በሚያሰኘው እሥረኞችን በምህረትም ይሁን በይቅርታ የመፍታት ሂደቱ ገፍቶበት እነዚህም መነኮሳት ለለቃቸው እንደሚችል ተስፋ እያደረግን፤ መነኮሳቱ የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ያቀረቡትን አቤቱታ ቅጂ ይነበብ ዘንድ ከዚህ በታች አስፍረነዋል።

የካቲት 13 ቀን 2010 ዓም
የኮ/መ/ ቁጥር 197866
ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት

አዲስ አበባ
ከሳሽ የፌደራል ዐቃቤ ሕግ
ተከሳሾች እነ ተሻገር ወልደሚካኤል

ጉዳዩ:_ በእስር ቤት አያያዝ ላይ 4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች እየደረሰብን ያለውን በደል ስለማመልከት ይመለከታል።

አመልካቾች በዋልድባ ገዳም መነኮሳት ስንሆን ወንጀል ፈፅማችኋል በሚል ክስ ቀርቦብን በቂሊንጦ የቀጠሮ እስረኞች ማቆያ በእሰር ላይ እንደምንገኝ ይታወቃል።

አመልካቾች መነኮሳት እንደመሆናችን ኃይማኖታችን የሚያስገድደንን የራሳችን አልባሳት እንጠቀማለን። ይህን አልባሳታችን የምናወልቀው ስንሞት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ይህን አልባሳታችንን እንድንለውጥ መገደድ ማለት ለእኛ ዕእምነታችንን እንድንሸር፣ በእግዚአብሔር ስም የተሰጠንን ክብር እንዲዋረድ ማድረግ እንደሆነ ይሰማናል። በመሆኑም የዕምነት ልብሳችንን ከምንቀይር የስጋ ሞታችንን እንደምንመርጥ ለእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎች በተደጋጋሚ ግልፅ አድርገናል። ይሁን እንጅ የእስር ቤቱ አስተዳደር መጀመርያ ላይ ተቃውሟችንን የተቀበለ የመሰለ በመሆኑ በእኛ በኩል ለዚህ ፍርድ ቤት አቅርበን የነበረውን አቤቱታ ሳንገፋበት ቀርተናል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የእስር ቤቱ አስተዳደር አልባሳቱን እንድናወልቅ ከፍተኛ ጫና እያደረገብን ከመሆኑም በላይ ለከፍተኛ እንግልትና መዋረድ ተዳርገናል። ይኸውም:-

5ኛ ተከሳሽ የሆንኩት አባ ገ/ሥላሴ ወ/ኃይማኖት ወደዚህ ፍ/ቤት ለመምጣት የዕምነት ልብሴን እንዳወልቅ ስጠየቅ አላወልቅም በማለቴ ማዕረጋቸውንና የአባታቸውን ስም ያላወኳቸው ነገር ግን የደህንነትና ጥበቃ ኃላፊ መሆናቸው የሚታወቁ ገ/ እግዚያብሔር የተባሉ የእስር ቤቱ ኃላፊ እያዩና እራሳቸው እያገዙ ተፈሪ የተባለ ወታደር የጎማ ዱላ በመያዝ ወደ አንድ ሰዋራ ቦታ ሊወስደኝ ሲሞክር ምሰሶ ላይ ተጠምጥሜ እምቢ ብልም ልብሴን ከላየ ላይ ለመግፈፍ በኃይል እየጎተተ ያንገላታኝ ከመሆኑም በላይ አቅም አንሶኝ ከመሬት ወድቄ ከእነ ልብሴ መሬት ላይ ሲጎትተኝ በሌሎች ሀይ ባይነት የከፋ ጉዳት ሳይደርስብኝ ተርፌያለሁ። ያም ቢሆን በዕምነቴ መፅናቴ እንደ ጥፋት ተቆጥሮብኝ ለአንድ ወር ያህል መቀጣጫ በሆነው ዞን 5 በከፋ ሁኔታ እንድቆይ ተደርጌያለሁ።

4ኛ ተከሳሽ የሆንኩት እኔ አባ ገ/እየሱስ በተመሳሳይ ችግር እየደረሰብኝ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ ሁለታችንም ተለዋጭ ልብስ እንዳይገባልን ተከልክለን በላያችን ላይ ያለው ልብስ በእጅጉ ቆሽሾ በጤናችን ላይ ችግር እያስከተለ ይገኛል። በሌላ በኩል 4ኛ ተከሳሽ በአሁኑ ጊዜ ፈፅሞ ባለወኩት ምክንያት እና ለምን ያህል ጊዜም እንደምቆይ ባለወኩበት ሁኔታ በቀጣት መልክ ዞን 5 እንድቆይ ተደርጌያለሁ። ይህ ቦታ ጥፋት ፈፅሟል የሚባል እስረኛ በቅጣት መልክ ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ የሚደረግበት እጅግ አደገኛ እና ለከፍተኛ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት የሚዳርግ መሆኑ በግልፅ የሚታወቅ ነው።

**...ይህን አልባሳታችን የምናወልቀው ስንሞት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ይህን አልባሳታችንን እንድንለውጥ መገደድ ማለት ለእኛ ዕእምነታችንን እንድንሸር፣ በእግዚአብሔር ስም የተሰጠንን ክብር እንዲዋረድ ማድረግ እንደሆነ ይሰማናል...**

በአጠቃላይ አመልካቾች በተከሰስንበት ጉዳይ ይህ ፍርድ ቤት ሊሰጥ የሚችለው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ አስቀድሞ በእስር ቤት እየደረሰብን ያለው በደል ግን ዕምነታችንን የሚያዋርድ እና ስብዕናችንን የሚነካ በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል ያቀረብነውን አቤቱታ ጭምር በማየት የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ለኃይማኖት ነፃነት የሰጠውን ጥበቃ መሰረት በማድረግ በደል የፈፀሙብን የእስርቤቱ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ እርምጃ እንዲወስድልን እንዲሁም በእስርቤቱ አስተዳደር ላይም መብታችን የሚያስከብር ትዕዛዝ እንዲሰጥልን እናመለክታለን።

1ኛ) አባ ገ/እየሱስ ኪ/ማርያም
2ኛ) አባ ገ/ስላሴ ወ/ኃይማኖት

# «ዛሬ ሲፈራ የነበረው ወገን ልጓሙን በጥሷል»

## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ



**– መስከረም 3 ቀን 2004 ዓ.ም ለስምንተኛ ጊዜ ታሠረ፡፡**
**– የተከሰሰው «የግንቦት ሰባት አመራር አባል ሆነህ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የታህሪር አደባባዩን የመሰለ አብዮት ለማቀጣጠል ሞክረሃል» በሚል ነው፡፡**
**– የካቲት 7 ቀን 2010 ዓ.ም ከእሥር ተፈታ፡፡**
**– የእሥር ጊዜውን ያሳለፈው በማዕከላዊና በቃሊቲ ነው፡፡**
**– በእሥር ላይ እያለ የሚናፍቁት ልጁና ባለቤቱ ነበሩ፡ ፡**

በኢትዮጵያ የነፃ ፕሬስ ታሪክ ከፍተኛ የሆነ ሙያው ተጋድሎ ካደረገው፣ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ መብቶቹ መከበር የሚያደርገውን ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ማቋረጥ አይኖርበትም» በሚለው ዕምነቱ በመጽናት፤ ወደፊትም ትግሉ የግድ በሚለው አቅጣጫ በአስተውሎት እንደሚራመድ ከገለጸልን እና ሐሣብን በነፃነት በመግለጽ ዓርበኝነቱ በኢትዮጵያም ይሁን በዓለም ደረጃ ዕውቅናን ካተረፈው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር ከወህኒ ከወጣ በኋላ ግዮን መጽሔት የሚከተለውን ቆይታ አድርጋለች፡፡

**ግዮን፡- በተያዝክበት ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ብትገልጽ ልን?**

እስክንድር፡- መስከረም 3 ቀን 2004 ልጄን ከትምህርት ቤት በመኪና ይዤው በመመለስ ላይ እያለሁ፤ የአንዷለም ጓደኛ ደውሎ «እስክንድር አልተያዝክም እንዴ? አንዷለም አራጌን ዕኮ አሁን ያዙት!» ይለኛል፡፡ «ኧረ ወደ እኔስ አልመጡም» የሚል መልስ ሰጠሁትና መኪናዬን ከፒያሳ ወደ ደጃች ውቤ ሠፈር አቅጣጫ ነዳሁ፡፡ መኪናዋን ከባለቤቴ እናት መኖሪያ ሠፈር አቅራቢያ በማቆም ላይ እያለሁ፤ ዓይኔ ከአንድ አጠር፣ ወፈር፣ጠቆር ያለ የጸጥታ ሠራተኛ ጋር ተገጣጠመ፡፡ ያም ሰው ወደ እኔ በአትኩሮት እየተመለከተ በእጅ ስልኩ ለባልደረቦቹ መልዕክት በማስተላለፍ ላይ ነበር፡፡ እኔ የዚያ ሰው ድርጊት ምን እንደሆነ በገባኝ በዚያ ቅጽበት በየሥርቻው የጦር መሣሪያ ይዘው የተደበቁት ወታደሮች አካባቢውን ተቆጣጠሩት፡፡ ያኔ ልጄ ሁኔታውን ተመልክቶ ይደነግጥብኛል በሚል የተረበሸ መንፈስ ውስጥ ሆኜ ለባለቤቴ ሠርካለም ልጃችንን መጥታ እንድትወስደው ስልክ ደወልኩላት፡፡ እሷ ወዳለንበት እስክትመጣም ወታደሮቹ እኔና ልጄ የነበርንባትን መኪና ዙሪያዋን ከበቧት፡፡ አንድ ሲቪል የለበሰ ፖሊስም ወደ እኔ ቀረብ ብሎ ከመኪናዬ እንድወርድ ጠየቀኝ፡፡ «ልጄ እያለ እንዴት እወርዳለሁ? እናቱ ትወስደዋለችና እሷ እስከትመጣ አንድ አፍታ ታገሰኝ» አልኩት፡፡ ለደግነቱ ብዙም ሳትቆይ ሠርካለም መጣች፡፡ እንደመጣች ልጃችንን ሰጧት፡፡ ከመኪናዬ ወርጄ ፖሊሶቹ ወዳዘጋጁልኝ ሚኒባስ ውስጥ ገባሁ፡፡ ወዲያው ይወስዱኛል ብዬ ስጠብቅ መኪናዬን በመፈተሹ ተግባር ተጠመዱ፡፡ የፖሊሶቹን ድርጊት እየተመለከትኩ በነበረበት ሰዓት ልጄ ናፍቆት ከእናቱ እጅ አምልጦ እኔ ወዳለሁበት ሚኒባስ እየሮጠ መጣ፡፡ እንደደረሰም እያለቀሰና እልህ እየተናነቀው የመኪናውን ተንሸራታች መዝጊያ በኃይል ዘጋው፡፡ መዝጊያው ሲከረቸም ያሰማው ጩኸት በዚያ የአምስት ዓመት ልጅ ጉልበት የተዘጋ አይመስልም ነበር፡፡ በሩን ከከረቸመው በኋላ እዚያው በሩ ሥር ሆኖ በጣም አለቀሰ፡፡ ትንሽ ቆይቶም ወደ እናቱ ተመለሰ፡፡ በእናቱ እቅፍ ውስጥ ሆኖም እንባው እርግፍ እርግፍ ይል ነበር፡ ፡ በአባቱ ላይ መጥፎ ነገር የደረሰ መሆኑ በደንብ ገብቶታል፡፡ በአጭሩ በተያዝኩበት ጊዜ የነበረው ሁኔታ የሚመስለው ይህን ነው፡፡

**ግዮን፡- በቅድሚያ ወዴት ወሰዱህ? ቀጥሎስ የገጠመህ ሁኔታ ምን ይመስላል?**

እስክንድር፡- ወደ ማዕከላዊ ነው፡፡ ያም ሥፍራ በተደጋጋሚ የታሠርኩበት ስለሆነ ብዙም እንግዳ ነገር አላየሁበትም፡፡ አስቀድሞ ለሰባት ጊዜ ያህል ጎብኝቼዋለሁ፡፡ ብዙ ስቃይ የተቀበልኩበት ቦታ ነው፡፡ እንደማስታውሰው ከነፃው ፕሬስ ባልደረቦች «ኢትዮጲስ» በተባለችው ጋዜጣዬ ምክንያት በማዕከላዊ የመጀመሪያውን አደገኛ ጥፊ የቀመስኩት እኔ ነበርኩ፡፡ ያም ጥፊ በዚያም ጊዜ ሆነ ከዚያም በኋላ ወደ ካልቾ አድጓል፡፡ እንደገናም ደግሞ «ሃበሻ» የተሰኘውን ጋዜጣ እያዘጋጀሁ በነበረበት ጊዜ ወደዚሁ ማዕከላዊ ተወስጄ እጄ እስኪወልቅ ድረስ ተደብድቤአለሁ፡፡ ገልብጠውም ገርፈውኛል፡፡ ብቻዬንም በጨለማ እና በቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ አሥረውኛል፡፡ የዚያ ሁሉ ስቃይ ትዝታ በነበረበት ሁኔታ፤ እንደገና መስከረም 3 ቀን ለስምንተኛ ጊዜ ማዕከላዊ ገባሁ፡፡ እንደገባሁ «በቃ ብቻዬን ነው የሚያሥሩኝ» የሚል ግምት ነበረኝ፡፡ ግን አንድ «ስምንት ቁጥር» ወደምትባልና አራት የተለያዩ ክፍሎች ወዳሏት የማሠሪያ ቤት ወሰዱኝ፡ ፡ አንደኛዋ ክፍል ወርዷ 1 ሜትር፣ በቁመት 2 ሜትር ያህል ነች፡፡ በውስጧ ጨለማ ቢሆንም በመተላለፊያዋ ላይ መብራት ነበር፡፡ ደግሞ ወደ ውጭ መመልከት የሚቻልባት ትንሽዬ ቀዳዳ አላት፡፡ እኔን የሚመለከተውን ፍተሻ እንደጨረሱ በዚያች ክፍል አስገብተው ዘጉብኝ፡፡ በዚያ ጊዜ በሦስቱ አጎራባች ክፍሎች ውስጥ ምንም ታሣሪ አልነበረም፡፡ በመተላለፊያው ላይ የምትበራው አምፖል ብርሃን በትንሽቱ ቀዳዳ ውስጥ አልፋ አንድ ጥግ ላይ ብቻ ነጸብራቋ ይታያል፡፡ በተረፈ አንድ እጅን ትንሽ ወደላይ እንኳ ከፍ ቢያደርጉ መልሶ ማየት የማይቻልበት ድቅድቅ ጨለማ ነው፡፡ የእኔ ቁመት 1ሜትር ከ 78 ሴንቲ ሜትር ስለሆነ፤ በምተኛበት ጊዜ እግሮቼ ከግርግዳው ጫፍ ለመጠጋት የሚቀራቸው 22 ሴንቲ ሜትር ብቻ ነው፡፡ ያቺም ቀሪ ሥፍራ በትራስና በምንጣፍ ስለምትሸፈን እግሬ ሲዘረጋ በቀጥታ ግርግዳው ላይ ያርፋል፡፡ በዚያች ክፍልም ለስድስት ቀናት ብቻዬን ቆየሁ፡፡ ከዚያም ከክፍሏ አውጥተው ወደ ሌላ የእሥር ክፍል አዛወሩኝ፡፡ ደስ የሚለው ነገር ለስምንተኛ ጊዜ ወደ ማዕከላዊ ስገባ ምንም ዓይነት ግልምጫም ይሁን ስድብ አልገጠመኝም፡፡ ጫፌንም የነካኝ የፖሊስ ወይም የምርመራ ቡድን ባልደረባ አልነበረም፡፡

**ግዮን፡- የመጀመሪያ ጥያቄያቸው ምን ነበር?**

እስክንድር፡- ያቀረቡልኝ ፈፅሞ ያልጠበቁትን ጥያቄ ነው፡፡ በሽብርና በሽብርተኝነት ላይ ያተኮረ የምርመራ ጥያቄ፡፡ ያልገመትኩት ነበርና በጣም ተገረምኩ፡፡ ያም ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በሽብርተኝነት ወንጀል እንደተከሰስኩ ያወቅኩት በዚያ የምርመራ ጊዜ ሳይሆን ፍ/ቤት አንድ ብለው የወሰዱኝ ዕለት ነው፡፡ ቀዳሚውን የጊዜ ቀጠሮ በጠየቁብኝ ቀን «በሽብር ወንጀል ተጠርጣሪ የሆነ ሰው ነው…» ብለው ቃላቸውን በፍ/ቤት አሰሙ፡፡ «ሽብርተኛ…» መባሌን ስሰማ ሳቅሁ፡፡ ያለጠበቁት በመሆኑና ቀልድም ስለመሰለኝ ከመሳቅ ያለፈ አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ግን ጉዳዩ በዚያ አላበቃም፡፡ ጭራሽ በህልሜም ይሁን በውኔ ያልጠረጠርኩት ጉዳይም ተከተለ፡፡ ያውም «የግንቦት ሰባት አመራር አባል» ተባልኩ፡፡ በሳቅሁበት የሽብር ወንጀል ተጠርጣሪ ልሆን ብችልም «የግንቦት ሰባት አመራር ነው» መባሌ ግን ከቶውንም ያልተዋጠልኝ ነበር፡፡ ከዚያ በማዕከላዊ አንድ ወር ከተወሰኑ ቀናት ቆየሁና ወደ ከርቸሌ ወረድኩ፡፡ እነሱ የተከሰስንበት «ወንጀል» የተባለ ድርጊት ያው የፈጠራ መሆኑን ልቦናቸው የሚያውቀው በመሆኑ ከባድ የምርመራ ሥራ በእኛ ላይ ለመሥራት አልፈለጉም፡፡ በማዕከላዊ አንድ ተጠርጣሪ አራት ወራትና ከዚያም በላይ ለሆነ ጊዜ የሚቆየው ከባድ ምርመራ የሚያስፈልገው ጥፋት

ፈጽሟል ተብሎ ሲታሰብ ወይም ሲገመት ነው። በእኔ ዕምነት የእኛ ክስ ግን የፈጠራና የውሸት ነው። ስለዚህ በዚያ የምርመራ ማካሄጃ ቦታ ለለብ ለብ የምርመራ ሂደት. ካልሆነ በቀር የምንቆይበት ምክንያት አልነበረም።

**ግዮን፡- ቃሊቲ ከወረድክ ከጥቂት ወራት በኋላ የመለስ ዜናውን ዜና እረፍት ስታደምጥ ምን ተሰማህ? በመሞታቸው ምክንያት ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብለህስ አስበሃል?**

እስክንድር፡- ሰው እንደመሆኔ መጠን ማንም አምሳያዬ የሆነ ፍጡር ‹‹ሞተ›› ሲባል፤ ልደሰት የምችልበት ሁኔታ የለም። ሞራሌም፣ የኃይማኖቴም ሁኔታ በሰው ሞት እደሰት ዘንድ አይፈቅድልኝም። በመሆኑም በግለሰብነቴ ደረጃ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት አዝኛለሁ። በዚህ ምድር ባሉበት ጊዜ ምንም ሠሩ ምን በሰማይ መልካሙ ነገር እንዲገጥማቸው እመኛለሁ። ከዚህ ባለፈ ግን በሳቸው ሞት የተነሳ ‹‹ኢትዮጵያ አንድ ዴሞክራት መሪ አጣች›› የሚል ዕምነት የለኝም። መለስ በመሞታቸው የተቀነሰብን አንድ ዴሞክራት የለም። መለስ ዴሞክራት እንዳልነበሩ ጠንቅቄ አውቃለሁ። እንዲያም ሆኖ በእሳቸው ሕልፈት ምክንያት ሀገራችን ወደለውጥ ሂደት ልታልፍ እንደምትችል ግምት ወስጄ ነበር። ሆኖም በጠበቅኩት ፍጥነት ወደ ለውጥ አልገባችም። ግን ደግሞ በአዝጋሚ መልኩም ቢሆን ኢትዮጵያ ወደ ለውጥ ሂደት ውስጥ ገብታለች። አሁን በሀገራችን የምናስተውለው ሁኔታም መለስ ባለመኖራቸው የመጣ ነገር ነው የሚል አስተያየት አለኝ።

**ግዮን፡- ከእሥር ተፈተህ ባለቤትህንና ልጅህን በስልክ እንዳገኘህ ምን ተነጋገራችሁ?**

እስክንድር፡- እዚህጋ ቀዳሚው የባለቤቴ ሠርካለም ታጋይነት ነው። ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ታግላለች። በነፃው ፕሬስ የሕልውና እና የፈተና ጊዜያቶችም አብራኝ ነበረች። የነፃው ፕሬስ አባላት በተያዝንበት ወቅት ሊያውም ነፍስ-ጡር ሆና ድብደባ ተፈጽሞባታል። ልጃችንን የወለደችውም በእሥር ቤት ነው። እሥር ቤት በነበርኩበት ጊዜ ያ ‹‹ፈርሙ!... አትፈርሙ›› የሚለው ነገር ሲመጣ፤ ለዘለዓለም ልቤ ውስጥ የመቅረት አቅም ያላቸውን ቃላቶች በመጠቀም ‹‹በምድር ላይ የሰጠሁህን አደራ በሰማይ ቤት እጠይቅሀለሁና እንዳትፈርም!›› የሚል መልዕክት ልካብኛለች። በዚህ ረገድ የራሴ ብቻ ሳይሆን የሷም አደራ ነበረብኝ። እና የሞራል አልኝታዬ የነበረችውን ባለቤቴን ያገኘኋት በከፍተኛ ጉጉት ነው። ሌላው ይህ ሁሉ ሊገባው አይችልም የምለውና አባቱን ብቻ የሚፈልገው ልጃችን ከእሷ አጠገብ መሆኑ፣ የእሱንም ሆነ የእሷን ድምፅ ለመስማት መጓጓቴና እየሰማሁም ባለሁበት ሰዓት የሚሰማኝ የአባትነቴ፣የባለቤቴ የሕይወት ክፋይ የመሆኔ፣ ሰው ሆኜ የመፈጠሬ ልዩ ስሜት ደግሞ ይኖራል። በተለይ ከልጄ ጋር የተነጋገርኩት በኃዘንና በደስታ ድብልቅልቅ ስሜት ውስጥ ሆኜ ነበር። በዚያ ዓይነት ድብልቅልቅ ስሜት ውስጥ ሲኮን ደግሞ የንግግር ቅደም-ተከተል፣ ዐበይት የሚባሉትን ጉዳዮች ቦታ የማስያዝ ዝግጅት ሊኖረኝ አይችልም። በደፈናው የባለቤቴንና የልጄን ድምፅ ለመስማት መቻሌ በእኔነቴ ውስጥ በፈጠረው ሰዋዊ ስሜት እየተመራሁ፣ እነሱ ከወህኒ በመፈታቴ የተሰማቸውን የደስታ ቃል ስልት እየተከተልኩና ለፈጣሪዬ ምስጋና እያቀረብኩ የምናገረው ነገር ነበረኝ።

**ግዮን፡- በእሥር ጊዜህ በወህኒ ቤቶች የእሥረኞች አያያዝ፣ የተጠርጣሪ ዜጎችን ክሶች በመመልከት ሂደትና በተያያዥ ሁኔታዎች ላይ ያስተዋልከው ለውጥ አለ?**

እስክንድር፡- እንዲህ ነው ብዩ ልገልጸው የሚቻለኝ፤ ጥሩና የተሻለ ነው የምለው ለውጥ አላየሁም። እኔን በተመለከተ ግን ከዚህ በፊት ለሰባት ጊዜ በተያዝኩበትና በታሠርኩበት ጊዜ ያጋጠሙኝ ከስድብና ጥፊ እስከ መገረፍ ድረስ የነበሩ በደልና እንግልቶች፣ እንዳይደገሙ የምፈልጋቸው ከመሆናቸው አኳያ ከቶውንም የማልረሳቸው እኔን የማሰቃየት ተግባሮች፤ በስምንተኛው የእሥራት ጊዜዬ በፍፁም አልገጠሙኝም። ያም ሆኖ በዚህኛው የእሥር ጊዜዬ እጅግ ቅር የተሰኘሁበትና ተፈጽሞብኛል የምለው ትልቅ በደል ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ እንደላነብ መከልከሌ ነው።

**ግዮን፡- ከመታሠርህ በፊት አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ባዘጋጀው አንድ መድረክ ላይ ያቀረብከው ጥናታዊ ጽሑፍ ለመታሠርህ ምክንያት ሆኗል?**

እስክንድር፡- በወቅቱ ግብፅ ውስጥ ሕዝባዊ አብዮት ተቀጣጥሎ፤የታሂሪር አደባባይ ንቅናቄ ትልቅ ዓለም አቀፍ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። እናም ‹‹የግብፅ አብዮት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል። ወደተቀሩት የጥቁር አፍሪካ ሀገሮች ይዛመታል። ወደዚያ መዛመቱ የማይቀር ከሆነ ደግሞ መግቢያ የምትሆነው ኢትዮጵያ ነች›› የሚል ትንታኔ ያለው ጽሑፍ ማቅረቤ እውነት ነው። ያ ትንታኔ በፈረንጆቹ በኩል አስቀድሞ የቀረበ ቢሆንም እኔም የምገራው ነበር። በዚያን ሰሞን በአፍሪካ ጉዳዮች ጥልቅ ትንታኔ የሚያቀርቡና ‹‹ያቀርባሉ›› የሚባሉትም ወገኖች እኔ በአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ መድረክ ያቀረብኩትን ዓይነት ሐሣብ አጉልተው እያነሱት ነበረ። መንግሥት በበኩሉ አብዮቱ ወደ ኢትዮጵያም ያልፋል የሚል ስጋት ነበረው። እኛም ደግሞ ያ ተስፋ ነበረን። ነገሩን በሦስት አቅጣጫ ልንመለከተው እንችላለን። አንድ ተንታኞቹ ያን ዓይነት ግምት ነበራቸው። መብታችን የተገፈፈው፣ የተጨቆነው እኛ ዴሞክራቶቹ፤ የለውጡ ተስፋ ነበረን። አምባገነኖቹ ደግሞ የራሳቸው ስጋት ነበራቸው። እና በጊዜው ሦስት ነገሮች ተገጣጥመዋል። በዚህ ዓይነት ስሜቶች መሀል ነበር ወደ አንድነት ፓርቲ መድረክ ሄጄ ጽሑፍ ያቀረብኩት። ጽሑፉም ወቅታዊነት በነበረው ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር። በዚያ ጽሑፍ መደምደሚያ ‹‹በቃ ሰላማዊ ትግላችን በሰላማዊ መንገድ መልስ የሚያገኝበት መቋጫ ላይ ደርሷል። ስለዚህ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ወደ መስቀል አደባባይ ወጥተን፤ ለዴሞክራሲ ድምፃችንን ማሰማት አለብን›› የሚል ጥሪ ነው ያቀረብኩት። በዚያ ሰዓት የነበረኝ አቋም፣ ያለሁበት ደረጃ ያ ነበር። ያን ለማድረግ ደግሞ

> **…በየሥርቻው የጦር መሣሪያ ይዘው የተደበቁት ወታደሮቹ አካባቢውን ተቆጣጠሩት። ያኔ ልጄ ሁኔታውን ተመልክቶ ይደነግጥብኛል በሚል የተረበሸ መንፈስ ውስጥ ሆኜ ለባለቤቴ ሠርካለም ልጃችንን መጥታ እንድትወስደው ስልክ ደወልኩላት። እሷ ወዳለንበት እስክትመጣም ወታደሮቹ እኔና ልጄ የነበርንባትን መኪና ዙሪያዋን ከበቧት…**

ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር የሚያገናኝ ነፃ የሆነና የሲቪክ ማኅበረሰቦችን አሳታፊ የሆነ ኮሚቴ የመቋቋም ሂደት ጀምረን ነበረ። እና በዚያች ወቅት ያቺ እኛ የምንፈልጋት ሰላማዊ ሰልፍ እንዳትጠራ፤ ኢሕአዴግ ይታገል ነበር። ግን ለመታሠሬ ምክንያት የሆነው እሱ ብቻ አልነበረም። እኔን ለመያዝ ሌሎች የተጠራቀሙ ምክንያቶች ነበሩ። በመጀመሪያ በፕሬስ ውስጥ የሠራነው ሥራ ነበር። ሁለተኛ ብቸኛውና ምናልባትም ቀዳሚው ጉዳይ መንግሥትን የሚቃወም የመረጃ መረብ ጸሐፊ ሆኜ ለአንድ ዓመት ያህል ሠርቼአለሁ። እጽፍ የነበረውም አልፎ አልፎ ሳይሆን ዘወትር ዓርብ ዓርብ ነበር። እና እነዚህም ሁኔታዎች ለመታሠሬ ግፊት ያደረጉ ናቸው የሚል ዕምነት አለኝ።

**ግዮን፡- ወደፊት በቀደመ ዕምነትህ፣ ዓላማህ፣ ሙያህና ፍላጎትህ መሠረት የመቀጠል ፍላጎቱ አለህ? ወይስ ሊገድበኝ ይችላል የምትለው ችግር ይኖራል?**

እስክንድር፡- አሁን ልፍራ ብል ሀገራዊ ሁኔታው በራሱ የሚፈቅድልኝ አይመስለኝም። አይደለም ዛሬ ያኔ ብዙኃኑ ዝም ባለበት ጊዜ፤ ብቻቸውን ከሚጮኹት ጥቂት ሰዎች መሀል አንደኛው ነበርኩ። አይደለሁም እኔ ዛሬ ሲፈራ የነበረው ወገን ልጓሙን በጥሷል። የፍርሃት ፋሽኑም እያለፈበት ነው። ራሴን ከግዜው ሀኔታ ጋር ከማራመድ ውጭ የፍርሃትን አቅጣጫ ልከተል የምችልበት ምርጫ አይኖረኝም። በአጭሩ መፍራት አልችልም። በዚህ ላይ እስካሁን ከፍተኛ መስዋዕትነት ተከፍሏል። ስለዚህ ሰላማዊ ትግሉ የግድ በሚለው አቅጣጫ በአስተውሎት መራመዴ የማይቀር ነው።

**ግዮን፡- የስድስት ዓመት ከስድስት ወራቱን የእሥራት ጊዜ እንዴት አሳለፍከው? አንዳርጋቸው ጽጌን የማየት ዕድልስ ገጥሞሀል?**

እስክንድር፡- የመጀመሪያዎቹን ሁለት ዓመት ተኩል የሚሆኑ ጊዜያቶችን ያሳለፍኩት ከአብዛኛው ታሣሪ ጋር ነው። እዛ እያለሁም አንድ ሁለት ያህል ጽሑፎች ጻፌ፤ አንደኛው ዘ ጋርዲያን ላይ፣ አንደኛው ደግሞ ኒዎርክ ታይምስ ላይ ወጥቶ ነበረ። የጽሑፎቹን መውጣት ያወቀው መንግሥትም ‹‹መጻፍሕን አቁም፣ አሁን ነፃነትህ የተገደበ ሰው ነህ፣ የታሠርከው እንደዚህ ዓይነቱን ነገር እንዳትፈጽም ተብሎ ነው›› አለኝ። ‹‹መጻፌን አላቆምም። ወደዚህ ዓለም የመጣሁትም ለመጻፍ ነው። የታሠርኩትም ብዕሬን አላስቀምጥም ብዬ ነው›› የሚል መልስ ስሰጣቸው፤ ከብዙኃኑ እሥረኛ ለዩኝ። ጥብቅ ጥበቃ የሚደረግባቸው እሥረኞች ወደሚገኙበትና ‹‹ኋይት ሐውስ›› ወደሚባለው ክፍል ወሰዱኝ። ያ ኋይት ሐውስ ሁለት ክፍሎች ነበሩት። ታምራት ላይኔ እና ስዬ አብርሃ ታሥረውበት በነበረው አንደኛ ክፍል፤ እኔ፣ አንዷለም አራጌና ሌሎች ሦስት እሥረኞች ገባን። በሌላው ክፍል ደግሞ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና ሌሎች እሥረኞች ነበሩበት። እኛ በዚያ የእሥር ክፍል ብዙ ከቆየን ወዲህ አንዳርጋቸው መጣ። አንዳርጋቸውን ይዘውት ሲመጡ ከእኛ ጋር ቀላቅለው ማስቀመጥ አልፈለጉምና እዛው ኋይት ሐውስ ውስጥ ሦስተኛ ቤት ሠሩ። እኛንም እነ ታምራት ላይኔ ከታሥሩበት ክፍል አውጥተው ወደ አዲሱ ቤት በማስገባት አንዳርጋቸውን እኛ የነበርንበት ክፍል ውስጥ አስቀመጡት። ከእሱም ጋር ሁለት በነፍስ ማጥፋት ወንጀል የተከሰሱ ታሣሪዎች አብረውት እንዲሆኑ አድርገዋል። በዚያም ሁኔታ ባለ ሁለት የነበረችው ኋይት ሐውስ ባለ ሦስት ክፍል ሆነች። በሂደት ደግሞ እኔና አንዷለም አንድ ላይ እንድንሆን ባለመፍቀዳቸው ለያዩን። በአንድ ቦታ ውስጥ ሦስት ክፍል/ግቢ ካለው ኋይት ሐውስ ውስጥ በስተመጨረሻ እኔ የታሠርኩበት ሰፋ ያለና አንዳርጋቸው ጽጌና አንዷለም ከሚገኙባቸው ግቢ/ክፍሎች የተሻለ ነው። እኔ የነበርኩባት ሦስት ሜትር ስፋት በዘጠኝ ሜትር ከፍታ/ቁመት ነች። እንዲያም ሆኖ አንዳርጋቸው እኛን ማየት አይችልም። ግን በሳምንት አንድ ጊዜ ዘመዶቹ ሊጎበኙት ሲመጡ በሚወጣበት ጊዜ እና በቀዳዳ እናየው ነበር። በአጭሩ የስድስት ዓመታት ከስድስት ወሩን የእሥራት ጊዜ ከእግዚአብሔር እገዛና ጠባቂነት ጋር በጽናት፣ በተስፋና በነበረኝ ጠንካራ የትግል መንፈስ አሳልፌዋለሁ።

**ግዮን፡- የምታስተላልፈው መልዕክት ካለህ?**

እስክንድር፡- ወገኔ በሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ የመተማማን መንፈስ አለኝ። አንብቤም ቢሆን ታሪኩን በተወሰነ ደረጃ አውቀዋለሁ። ለባሕሉም ታላቅ እክብሮት አለኝ። ስለዚህ ይህ ሕዝብ እጅግ ወደሚያስጨንቅ የሥርዓት አልበኝነት ጎዳና ያመራል ብዬ አላስብም። ሕዝቡ የተሻለ ነገር ያመጣል ብዬ አምናለሁ። እኛ ባዋለድናቸው የአፍሪካ ሀገሮች መበለጥ የለብንም። ስለዚህ በአፍሪካ ሞዴል ሊሆን የሚችል ዴሞክራሲያው ሥርዓት ልንገነባ የምንችልበትንና አሁን የሚስተዋለውን ዕድል ተጠቅመን፤ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ በመታገል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ይቻለናልና፤ የማከብረው ሕዝብ በዚሁ የትግል መስመር እንዲቀጥል ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ይህን ሰዓት ልናሳልፈው አይገባም። ከመርህም ይሁን ከታክቲክ አኳያ ከመቼውም ጊዜ በላይ በሰላማዊ ትግላችን የምንቀጥልበት ነው።

# ኢህአዴግ

## በቁልቁለት ወይስ በለውጥ መንገድ ላይ?

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ የደርግን መንግስት ከስልጣን አስወግዶ ሃገሪቱን መምራት ከጀመረበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 27 ዓመታት ብዛት ያላቸው ህዝባዊ ተቃውሞዎችን አስተናግዷል፡፡ ለነጻ ሃሳቦች በር መክፈት ባለመቻሉና በተለይም በህገመንግስቱ የተቀመጡ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶችን ባለማክበሩ ከሚመራው ህዝብ ጋር በሃሳብ እንዳይስማማ እና በተለያየ አቅጣጫ እንዲጓዝ አድርጎታል የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ኢህአዴግ ዛሬ በጥልቅ ታድሼ ስህተቴን አርሜ ህዝቡን ክሼ ሀገር እመራለሁ ብሎ ዕቅድ ይዞ ደፋ ቀና እያለ ቢገኝም ፓርቲው በእስከዛሬ ዘመኑ የህዝብን ጥያቄ ለማፈን የተጓዘበት ርቀትና ይዞት የዘለቀው ግትር ባሕሪ የዛሬ መንገዱን ቁልቁለት አድርጎበታል የሚሉ ታዛቢዎች ብዙ ናቸው፡፡ የወቅቱን የፖለቲካ አዝማሚያ የሚተነትኑ ወገኖች እንደሚሉትም ድርጅቱን ለቁልቁለት መንገድ የዳረጉትን የገዛ ራሱን ተፈጥሮአዊ መገለጫዎች አስተካክሎ ለመቀጠል ቁርጠኝነት ቢኖረው እንኳን ይህን ለማድረግ ጊዜው ረፍዷል ብለውም ይከራከራሉ፡፡

### "የኃይልና የኃይል ብቻ" መንገድ !

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ሀገሪቱን መምራት ከጀመረበት ካለፉት 27 ዓመታት ጀምሮ አንዳንዴም እየላላ አንዳንዴም እየከረረ ከፊቱ የሚገጥመውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ለመፍታት የሞከረበት መንገድ ተመሳሳይ ነው፡፡ ኃይል ብቻ!

በፓርቲው መዋቅራዊ ባህሪ ላይ ጥናት በማድረግ ላይ መሆናቸውን የሚገልጹትና ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት የፖለቲካል ሳይንስ ምሁር እንደሚናገሩት ወደዚህች ሀገር ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን አምጥቻለሁ የሚለው ፓርቲ ውጪው በሕዝባዊነትና በዴሞክራሲያዊነት ስም የታጠረ ቢሆንም አብዛኛው ባሕሪው ከአብዮታዊነት ያልተላቀቀ፣ በተለይም የሕዝብን ጥያቄ ለመፍታት የተጓዘበት መንገድ ደግሞ ውስጡ ከ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ባሕሪ የተዋቀረ መሆኑን ይመሰክራል ይላሉ፡፡

እኚሁ ምሁር እንደሚያብራሩት ኢህአዴግ እስካሁን ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የተጓዘበት መንገድ ከማቅረብ ይልቅ በማሳደድ፣ ከማግባባት ይልቅ በማስፈራራት፣ መልስ ከመስጠት ይልቅ በማሰር ባስ ሲልም በጥይት መሆኑ የፓርቲውን አምባገነናዊና እልኸኛ ባሕሪ የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡

ላለፉት 27 ዓመታት ኢህአዴግ በደህንነት መዋቅሩ አፍኖ ካኮላሻቸው አደባባይ ያልወጡ ተቃውሞዎች የተረፉ በቁጥር ብዛት ያላቸው ህዝባዊ ተቃውሞዎችን አስተናግዷል፡፡ እነዚያ ተቃውሞዎች ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ የቀረበባቸው ቢሆኑም ፓርቲው ግን ለጥያቄዎቹ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በሰላማዊ ሰልፎችና የተቃውሞ ስብሰባዎች ላይ የተፈጠሩ (ብዙዎች ሰርገው የገቡ የፓርቲው ሰዎች ሆን ብለው እንደፈጠሯቸው የሚገምቷቸው) ችግሮች ላይ በማትኮርና እነርሱን ሰበብ በማድረግ የተቃውሞ ስብሰባውን ያስተባበሩ አካላትን ለመክሰስ እና ወደእስር ቤት ለመላክ ሲጣደፍ ነው የኖረው፡፡

ገዢው ፓርቲ እነዚያን ሕዝባዊ ተቃውሞዎች የፈታበት መንገድ አንድም ኃይል የተቀላቀለበት አለያም "አለባብሰው ቢያርሱ" ዓይነት ለችግር መሰረታዊ መፍትሄ ያላመጣ አካሄድ መሆኑ ድርጅቱ የህዝብ ጥያቄዎችን የሚያይበት መነጽር የተንሸዋረረ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደረስ አድርጓል፡፡

በሀገራችን ብዛት ያላቸው የተቃውሞ ፓርቲ አመራሮች ከዚህ አይነት ክስተት ጋር በተያያዘ ሲታሰሩና ሲፈረድባቸው ቆይተዋል፡፡ ገዢው ፓርቲ ህዝብ ተቃውሞውን ሊገልጽባቸው እና ጥያቄዎቹን ሊያቀርብባቸው የሚችልባቸውን መስመሮችን በሙሉ በመዝጋት በራሱ ሕገመንግሥት የደነገጋቸውን ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ እና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ጭምር ከልክሎ ቆይቷል፡፡ ይህ ደግሞ ብዙዎች እንደሚስማሙበት የህዝብ ጥያቄ እና ብሶት ታፍኖ እንዲቆይ ኋላም ሊቆጣጠረው ባልቻለው መጠን እንዲፈነዳ ምክንያት ሆኗል፡፡

ፓርቲው ለህዝብ ጥያቄ አፋጣኝና ተገቢ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በተገላቢጦሽ የሕዝብን መንገድ ስህተት ፣ የራሱን መንገድ እውነት አድርጎ በማቅረብ የመብት ጥያቄዎችን ከርሱ ዘላቂ የመግዛት ፍላጎት አንጻር ብቻ መመልከቱ አንድ ጥፋት ሆኖ ይህንን አካሄድ ለመቀየር የተጓዘበት ርቀት ዜሮ መሆኑ ደግሞ ብዙኃኑን ኢትዮጵያዊ "ፓርቲው ለለውጥ ዝግጁ አይደለም" የሚል ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል የሚሉ አስተያየት ሰጪዎችም አሉ፡፡

### ገሃድን የመካድ መንገድ

የሀገሪቱን የፌዴራል እና የክልል ማረሚያ ቤቶች መዛግብት ከምርጫ 97 በኋላ ያጣበበው በውስጣቸው ያጎሯቸው የፖለቲካ እስረኞች ስም ዝርዝር ነው፡፡ ኢህአዴግ በየወቅቱ ለሚገጥሙት ተለዋዋጭ የሕዝብ ተቃውሞዎች አሳሪና ጨምዳጅ ሕጎችን እያዘጋጀና እያጸደቀ በሥራ ላይ የሚያውል ድርጅት በመሆኑ በተቃውሞ ሰልፍም፣ በህዝባዊ ሰብሰባም፣ በፕሬስ ስራዎችና ተሳትፎዎችም 'አጠፉ' ያላቸውን እየያዘ በነዚያ ሕጎች ሰበብ ወህኒ ማውረድን የዓመታት ችግር መፍቻ መንገድ አድርጎት ቆይቷል፡፡

የጸረ ሰላም ፣ ጸረ ልማት በቅርቡ ደግሞ አሸባሪ የሚል ታፔላ በስማቸው ላይ የሚለጥፍላቸው ዜጎች ሙሰኞች አለያም ሰርቆ በላዎች ሳይሆኑ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከመብት ጥያቄዎች እና ከዴሞክራሲ መከበር ጋር ተያይዞ ጥያቄ ያነሱ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ኢህአዴግ ለእነዚህ ተቀጥላ ስም ለጥፎ ወደማረሚያ ቤት ለሚጨምራቸው ዜጎች መክሰሻ ቃላት አላጣም፡፡ "ሕገ መንግስቱን በኃይል ለመናድ...፣ በሽብር ተግባር በመሰማራት... የህዝብ ሰላምና ጸጥታ በመንሳት ወዘተ፣ የሚሉት ከሳሽ ቃላት በየባለስልጣናቱ አፍ፣ በየፍርድ ቤቱ እና በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ዘወትር ሲዘመሩ የምንሰማቸው የዘመኑ ቃላት ሆነው ከርመዋል፡፡

ኢህአዴግ የፖለቲካውን ምህዳር ለማጥበብ ያወጣቸውን እንደጸረ ሽብር ያሉ አሳሪ ሕጎች በመጠቀም በፖለቲካው የነቃ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች ሲከስስ፣ እንዲሁም ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ህገመንግስታዊ መብቶቻቸውን ተንተርሰው የፓርቲውን ፖሊሲ አምረርረው የተቹ የፕሬስ ሰዎችን "ቀይ መስመር" አልፋችኋል ብሎ ወደ እስር ቤት ሲልክ ሁሉንም በጅምላ "ሕግ ተላላፊዎች ወይም ወንጀለኞች ናቸው" ብሎ ሰየመ እንጂ አንድም ጊዜ "በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኛ አለ" ሲል ተሰምቶ አያውቅም፡፡ በዓመታት አቋሙ ሀገሪቱ የፖለቲካ እስረኛ የሌላት መሆኑን በጽናት ሲናገር የቆየው ኢህአዴግ ለራሱ እንኳን በማረሚያ ቤት ያጎራቸው የፖለቲካ እስረኞች መኖራቸውን ሲክድ ኖሯል፡፡ "ማንንም በፖለቲካ ተሳትፎው እና በጋዜጠኝነቱ አላሰርንም፣ ያሰርነው ካለ የሀገሪቱን ሕጎች ተላልፎ የተገኘውን ብቻ ነው" በማለት ከዓለም አቀፍ እና ሀገር ውስጥ የተነሱበትን ተቃውሞዎች ለማርገብም ሲጥር ቆይቷል፡፡

ያም ሆኖ መንግሥት በዘመን መለወጫ እና በሌሎች የተለያዩ አጋጣሚዎች ብዙ ታራሚዎችን በምህረት ሲለቅቅ በፖሊሲውና አስተዳደሩ ብልሹነት ተቃውሞ ፈጥረው የተቹትንና እንዲህ ባለ መልኩ በወንጀለኝነት ያሰራቸውን ዜጎች ግን ከምህረት እድሉ አርቆ "ይለፋቸው" እያለ በእስር ቤት ከርችሞ አቆይቷቸዋል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በየእስር ቤቶች የታጎሩ የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞችን እንዲፈታ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚደርስበትን ውግዘት ጆሮ ዳባ ልበስ ከማለት አልፎ "እጃችንን ጠምዝዘው ያስፈጽሙን እንደሁ እናያለን" እስከማለት ደርሶም ነበር፡፡

በመጨረሻ ያ ሁሉ የተጠራቀመ ብሶት ሲጦዝ ፓርቲውም መውጫ መንገድ ለማመቻቸት ነገሮችን በጥሞና መመልከት ጀመረ፡፡ በሀገሪቱ የተፈጠሩትን ከባድ የሚባሉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ተከትሎ እንዲሁም በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል እንደተፈጠረ ሲናፈስ የኖረውን ልዩነት ለማስታረቅ በሚመስል መልኩ የኢህአዴግ ስራ አስጻሚ ምክር ቤት 17 ቀናት የፈጀ ጥልቅ ግምገማ ላይ ሰንብቶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በዚያ ግምገማ ላይ በኢህአዴግ ውስጥ ከዚህ ቀደም ታይተው የማያውቁ (በፓርቲው ቋንቋ አፈንጋጭ የሆኑ ) አስተሳሰቦች በአባል ድርጅቶች ተንጸባርቀው እንደነበርና የተበታተኑትን አስተሳሰቦች ወደ አንድ ለማምጣት እልህ አስጨራሽ ጥረት ጠይቆ እንደነበር ውስጥ አዋቂዎች ሲጠቋቁሙ ሰንብተዋል፡፡ ያ ስብሰባ አንተ አንቺ ተባብለው የተገማገሙበት ስብሰባ እንደነበርና ሁሉም የፓርቲው አመራሮች ጥፋታቸውን አምነው ህዝብ ጋር ለመቅረብ ራሳቸውን አዘጋጅተው መምጣታቸውንም በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ በቡድንም በተናጥልም በሰጡት መግለጫ ላይ ተናግረውታል፡፡

በከፍተኛ ምስጢራዊነትና በዝግ የተካሄደው ይህ ስብሰባ ከተቋጨ በኋላ የአራቱም ብሄራዊ ድርጅቶች ሊቃነመናብርት ለመንግስት መገናኛ ብዙኃን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ በመግለጫው ኢህአዴግ ጥፋቱን ለማስተካከል እወስዳለሁ ካላቸው እርምጃዎች አንዱም "ለጋራ ሀገራዊ መግባባት እንዲጠቅም" ብሎ የወሰነው በየማረሚያ ቤቱ ያሉ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ የታሰሩ ዜጎችን ክስ ማቋረጥና ከእስር መፍታት እንደነበር ይታወሳል፡፡ በዚህ መግለጫ ለየት ብሎ የወጣው ቃል ባለፉት 27 ዓመታት ድርጅቱ ሲክደው የኖረው "የፖለቲካ እስረኞች" የሚል ቃል ነው፡፡ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ኃይለማርያም ደሳለኝ ፓርቲያቸው ከስብሰባው በኋላ ያሳለፈውን ከእስር የመፍታት ውሳኔ በተመለከተ በሰጡት መግለጫ ውስጥ " የፖለቲካ እስረኞች ይፈታሉ" ነበር ያሉት፡፡

ብዙዎች ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ከዚህ ፓርቲ ጋር ሲጨቃጨቁበት የኖሩት እንዲሁም

ፓርቲውን ሲወቅሱበትና ሲከስሱበት የከረሙበት፣ ነገር ግን ፓርቲው ፍጹም አልቀበለውም ብሎ የካደው ዜጎችን በፖለቲካ አመለካከታቸው የማሰር ተግባር በርግጥም መፈጸሙን "የፖለቲካ እስረኞችን ለመፍታት ውሳኔ ላይ መደረሱን " በመናገር የራሱ የድርጅቱ ሊቀመንበር ቃል በቃል አረጋግጠውታል::

መግለጫውን ተከትሎ ብዙዎች በሰጡት አስተያየት "ኢህአዴግ እስከዛሬ አይኔን ግንባር ያድርገው" ብሎ ሲክደው የኖረውን የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ ማመኑ ወደ ለውጥ የማምራቱ ምልክት ይሆን ?" ብለው እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል:: "መሳሳት ችግር ሲሆን ስህተትን አለማመን ደግሞ የበለጠ ችግር ነው" እንደሚለው ብሂል ኢህአዴግ ለረጅም ጊዜ ሲሳሳት ቢኖርም ስህተቱን አንድም ጊዜ አምኖ አለማወቁ ግን በህዝቡ ዘንድ ፓርቲው ለመታረም ዝግጁ አለመሆኑን ያሳየበት ነው የሚሉ ድምዳሜዎች ላይ እንዲደረስም አድርጎታል::

## ስህተትን ያለማመን መንገድ

ለሰላሳ ዓመታት በሩሲያ ሰፍኖ የነበረው የጆሴፍ ስታሊን አስተሳሰብ "መሪው ፓርቲና የፓርቲው ዋና ፀሐፊ በፍፁም አይሳሳቱም" የሚል ነበር:: ይህ እምነት ስህተት፣ ብሎም ወንጀል መሆኑ የተጋለጠው በ1954 በተካሄደው 20ኛው የፓርቲው ጉባኤ ላይ ነበር:: መንግሥት የመላዕክት ስብስብ፣ ግለሰብም መልዓክ አይደለምና መሳሳታቸው አይቀርም:: ስታሊን ይህንን 'ከሰው ስህተት ክብረት ዝገት አይጠፋም' ብሒል ጥሶ ነው 'ፓርቲውም መሪውም አይሳሳትም' ያለው:: በዚህ ሳቢያ ፓርቲውም ይሁን ራሱ ያጠፋቸው ብዙ ጥፋቶች በወቅቱ "ትክክል ናቸው" ተብለው ታልፈዋል:: የታሪክ ተወቃሽነት ያመጣውም ይኸው ነው::

በአገራችንም የስታሊኒዝም መርህ የሆነው ይህ የአልሳሳትምና በጥፋት አልጠየቅም ባህሪ ከዚህ ቀደም በነበሩት መንግሥታት ላይ በግልጽ ይታይ የነበረ ቢሆንም በኢህአዴግ መንግሥት ላይ ግን ጠንክር ብሎ መከሰቱ፣ ለተመሳሳይ ጥፋቶችም ምንጭ ሆኗል::

ኢህአዴግ ተደጋግሞ እንደሚባለው የመላዕክት ስብስብ አይደለም:: ስለሆነም ስህተቶችን ይሰራል:: ያም ሆኖ ለዛሬ የውድቀት ጫፍ ያደረሰው መሳሳቱ ሳይሆን ስህተቱን አለማመኑ ወይም የሰራው ስህተት ልክ እንደሆነ አድርጎ መቀበሉ ነው:: ኢህአዴግ ግዙፍ በሚባል ደረጃ ከተሳሳተባቸው አጋጣሚዎች አንዱና ዋናው ምርጫ 1997 ነው:: በዚያን ወቅት የተሳሳተው አንድ መሰረታዊ እውነት ህዝብ በምርጫ ካርዱ ስልጣን የነፈገው መሆኑን እያወቀ ለመቀበል አለመፈለጉ ነው:: ከዚያ በኋላም ብዙ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ቢደርሱበትም "ከምርጫ 97 ወዲህ ኢህአዴግ ካስተናገዳቸው ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ሁሉ የዘንድሮው ተቃውሞ ፓርቲው ራሱን ከመሠረቱ እንዲመለከትና ጥገናዊም ቢሆን የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስድ የገፋው ነው" የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች ይበረክታሉ:: ብዙዎች ደግሞ ፓርቲው ችግሩን በጥልቀት ማየቱንና ይህንንም ለማስተካከል ቆርጦ መነሳቱን በመግለጫው ቢናገርም "ኢህአዴግ ማባበያዎችን ከፊት በማስቀደም የህዝቡን ትኩረት ለማስቀየስ ስልት ነደፈ እንጂ ሥልጣኑ ላይ ባነጣጠሩትና መሰረታዊ በሚባሉት የህዝብ ጥያቄዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት ግን ዝግጁነቱን አላሳየም" ብለው ይተቻሉ::

ከዚህ በተጨማሪም ካለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት ጀምሮ ኢህአዴግ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የተከሰቱትን ብሄር ተኮር ግጭቶችና ተቃውሞዎችን ከኃይል ባለፈ ያስተናገደበትና ምላሽ የሰጠበት መንገድ ካለፈው ያልተለየ ነው:: እንደ ኢህአዴግ አሳብ "ሕዝብ የሚቃወመው በመሰረታዊ ፍላጎት ፓርቲውንና ፖሊሲውን ጠልቶ ሳይሆን የመልካም አስተዳደር እጦት ገጥሞት ነው" :: ኢህአዴግ ሁሉንም የህዝብ ቃውሞዎች ከውጭ ኃይሎች ሴራ ጋር በማያያዝ ተጠምዶ በመኖሩ በውስጡ ለዚህ ችግር መከሰት ምክንያት የሆኑ የፖሊሲም ሆነ የአፈጻጸም ችግሮችን ለመዳሰስ ሙከራ ሲያደርግ አልተስተዋለም::

ቻይናን ለዘመናት ሲመራት የቆየው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ "How CPC works in china" በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ሊዩ ሺያን የተባሉ የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የተናገሩትን እዚህ ላይ መጥቀስ ተገቢ ይሆናል:: "ኮሙኒስት ፓርቲያችን ከሕዝባችን ጋር አንድ መሆኑን አረጋግጦ እንዲቀጥል ከፈለግን የቻይና ሕዝብ ቅር የሚሰኝባቸውን ድርጊቶች ማረም ይገባናል:: የሕዝባችንን ሙሉ ተቀባይነት አግኝተን ቻይናን ኃያል ሀገር ለማድረግ እቅዳችንን ለማሳካት የግድ ከሕዝባችን ጋር መስማማት አለብን:: ለዚህ ቁልፉ ዘዴ ደግሞ የሰራናቸው ስህተቶችን ሕዝብ ሲነግረን ማመንና ለመታረም ዝግጁ መሆን ነው:: እንደከዚህ ቀደሙ ችግሮቻችንን በሌላ ሦስተኛ ወገን ላይ እያላከክን መቀጠል የለብንም" ነበር ያሉት::

ቻይና ኢ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ብትሆንም ህዝቡን ጥያቄ በመመለስ ረገድ ግን ከህዝቡ ብዙም ያልራቀ አካሄድ ተከትላ ቢያንስ ዛሬ ሀገራዊ መግባባትን መፍጠር የቻለችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገር መሆን ችላለች:: የቻይናን ዕድገት በቅልውጫ የሚመለከተው ኢህአዴግ አምባገነን ነው የሚባለው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ያህል እንኳን ለመውሰድ ሲያዳግተው ኖሯል:: ይህም በሕዝብ ዘንድ እምነት እንዲያጣ ብቻ ሳይሆን የጀመራቸው የልማት ስራዎች እንዳይሳኩ እንቅፋት ፈጥሮ ከሁለት ያጣ አድርጎታል ይላሉ ተንታኞች::

## የራስ ችግሮችን ወደ ውጭ የመግፋት መንገድ

ፓርቲው ከሕዝብ ጋር ደም ከተቃባባቸው ክፉ አጋጣሚዎች አንዱ የነበረው የ1997 ዓ.ም ክስተት ሲያልፍ የጸጥታ ኃይሎቹ የገደሏቸውን ዜጎች በተመለከተ ይቅርታ አልጠየቀም:: በምርጫው ላይ ስለተፈጸመው እንከን ላይ በዓለም አቀፍም ይሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲቀርብበት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አልፎታል:: በየቀበሌው ወርዶ 'የአዲስ አበባን ሕዝብ ምን አስቀየምን?' ብሎ ሲጠይቅ ሕዝቡ እስከዶቃ ማሰሪያው ድረስ አባላቱ የሚሰሩትን ከመስመር የወጣ ግፍና ሕገወጥ ድርጊት ሲነግረው ሰምቶ ዝም አለ እንጂ በይፋ ይቅርታ አልጠየቀም:: ለመታረም ዝግጁነቱንም አላሳየም:: የወቅቱ የክስ ሰነዶች እንደሚያመለክቱት ከምርጫ ማግሥት ብጥብጡ ጀርባ አሉ ያላቸውን የኤርትራ ኃይሎች መክሰስ፣ የኢትዮጵያን ሰላም የማይፈልጉ ቡድኖች ያደራጁት ሀገር የማተራመስ ድርጊት ነው ብሎ መክሰስ፣ ጋዜጠኞችን ሰብስቦ በሀገር መክዳት ወንጀል መክሰስ በአጠቃላይ በራሱ ላይ የነበሩትን ጥፋቶች ሁሉ ወደውጭ በመግፋት ራሱን ንጹህ ለማድረግ መሞከር ነው የጀመረው::

የኢህአዴግ ያለመጠየቅ ፖሊሲ (ፖሊሲ ኦፍ ኢሚውኒቲ) አንዱ መገለጫ ለሚሰራቸው ጥፋቶች እራሱን ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ በውጪ ኃይሎች ላይ ማላከክና አሊያም ለፓርቲው የፖሊሲ ስህተቶች የውጭ ኃይሎች ተጠያቂ የማድረግ አካሄዱ መሆኑን ብዙዎች ይተቻሉ::

## የ "እኔ ብቻ አውቃለሁ" መንገድ

"Situational analysis on Public political participation and activism" በሚል ርዕስ ኦስትሪያ ቪየና ላይ በ2011 በተዘጋጀ ዓለም አቀፍ ውይይት ላይ በሁለት ሀገራት ላይ ያተኮረ ጥናት ያቀረቡት ኖርዌጂያኑ ፕሮፌሰር የንስ ፒተር ሼል (JENS PETER CHELL) እንዳሉት "ሕዝብ ከማንኛውም መንግሥት ሀገር የመምራት እውቀት በላይ የተከማቸ ጥልቅ ግንዛቤ አለው:: በየትኛውም ዴሞክራሲያዊና አምባገነን መንግሥታት ባሉበት ሀገር ሕዝብ ሁሌም ዓለቃ ነው:: ልዩነቱ ዴሞክራሲያዊው መንግሥት ይህንን እውነት መቀበሉና አምባገነን መንግሥታት ደግሞ መካዳቸው ብቻ ነው:: እንደጥናት አቅራቢው ጽሑፍ ከሆነ "ሕዝብ እንደማያስብ አድርጎ መቁጠርና ዳኝነቱን መናቅ የሚያደርጋቸውን ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች አፍራሽ እና ዝቅ ያለ አድርጎ ወደማየት እንዲሁም 'በርሱ ችሎታና አቅም ይህን አያደርግም' ወደሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ይወስዳል:: ከኋላ የሚመሩት ጠላቶቼ ናቸው የሚል አስተሳሰብ በመንግሥት ውስጥ ይፈጠራል:: አላስፈላጊ ዒላማ ፈጥሮ መተኮስም ይከተላል:: ይህንን የሚያደርጉ መንግሥታት የሕዝብን ነገሮችን የመረዳትና የመመዘን እንዲሁም የመቃወምና የመደገፍ ሚዛናዊነት ዝቅ አድርገው ሲያዩ በተዘዋዋሪ ይህንን ሕዝብ 'እንዳያስብ አድርገን ያስቀመጥነው እኛ ነን' የሚል ትርጉም እየሰጡት መሆኑን አልተረዱትም:: ይህ ዛሬ በብዙ የዓለማችን ሀገራት ተደጋግሞ የታየ ችግር ነው" ብለዋል::

ኢህአዴግ በሀገሪቱ የሚያከናውናቸው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊም ይሁኑ ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች በአብዛኛው የሕዝብ ስምምነት ያልተጠየቀባቸው ብቻ ሳይሆኑ ህዝብ ስለጉዳዩ የማያውቅባቸው ናቸው:: ፓርቲው እንደገዢ ፓርቲ ሀገር ለማስተዳደር በተቀመጠበት የስልጣን እርካብ ላይ ሆኖ የሚያከናውናቸው ማናቸውም ተግባራት ከህዝብ አይን እንደማይሰወሩ የታወቀ ነው:: ያም ሆኖ በሀገሪቱ ውስጥ ቢያንስ ዋና ዋና በሚባሉ ፖለቲካዊም ይሁን ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች የህዝብ ድምጽ ያልተጠየቀባቸውና ይሁንታ ያላገኙ መሆናቸው የፓርቲውን የእኔ አውቅልሃለሁ ባህሪ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች::

ኢህአዴግ በባሕሪው ምስጢራዊ ድርጅት በመሆኑ የዴሞክራሲያዊ አመራር አንድ መገለጫ የሆነው የአሳታፊነት ባህሪ ይጎድለዋል:: ፓርቲው ድብቅ በመሆኑም ብዙ ጊዜ የሚወስዳቸው ውሳኔዎች ለሕዝቡ ‹ሰርፕራይዝ› ናቸው:: ይህ በግርድፉ ሲታይ ህዝቡ የሚመራውን ፓርቲ አያውቅም ብቻ ሳይሆን ፓርቲውም የሚመራውን ሕዝብ አያውቅም ወደሚል መደምደሚያ ይወስዳል::

## የውሸት መንገድ

ዛሬ በኢትዮጵያ የሆነውም ይኸው ነው::እኚህ ሁሉ ምክንያቶች የኢህአዴግን መንገድ ቁልቁለት ያደረጉትም ግልጽ ካለመሆን ችግር ጋር ተያይዞ የመጡ ማለባበሶች እና በጊዜ ሂደት ሕዝቡ ልክ አለመሆናቸውን የተገነዘባቸው ስህተቶች ናቸው::

ዛሬስ ኢህአዴግ ከዚህ የቁልቁለት መንገድ ተርፎ ወደሕዝባዊነት ይመለስ ይሆን? ወይስ የገጠመውን ተቃውሞ በለመደው መልክ ተቋቁሞ በቀደመ መንገዱ ይቀጥላል ? ይህ ወደፊት የሚታይ ይሆናል::

> ኢህአዴግ ያለመጠየቅ ፖሊሲ (ፖሊሲ ኦፍ ኢሚውኒቲ) አንዱ መገለጫ ለሚሰራቸው ጥፋቶች እራሱን ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ በውጪ ኃይሎች ላይ ማላከክና አሊያም ለፓርቲው የፖሊሲ ስህተቶች የውጭ ኃይሎች ተጠያቂ የማድረግ አካሄድ መሆኑን ብዙዎች ይተቻሉ፡፡

# <<ባለፉት 27 ዓመታት የኖርነው አንድ ቀን ነው >>

## አሕመድ ሙስጠፋ (የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ጸሐፊ)



ወጣት አሕመድ ሙስጠፋ ሐቢብ ይባላል፡፡ የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ በሕዝብ የተመረጠው ኮሚቴ አባልና ጸሐፊ ነበር፡፡ አምስት ዓመት ከስምንት ወር ያህል ታስሮ በቅርቡ በምህረት ከተለቀቁ እሥረኞች አንዱ በመሆን ከማኅበረሰቡ ጋ ተቀላቅሏል፡፡ አሕመድ የመጀመርያ ዲግሪውን በቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ፣ ሁለተኛ ዲግሪውን ደግሞ በሥራ አመራር ተምሮ ሊመረቅ ቀናት ሲቀሩት ነበር ወደ ወህኒ የወረደው፡፡ ከጋዜጠኛ ሁሴን ከድር ጋር የእስር ቤት ቆይታውን በተመለከተ ያደረጉትን ምልልስ እንዲህ አቅርቦታል፡፡

**መች ነበር የታሰራችሁት?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- ‹‹የታሰርነው ሐምሌ 13 ቀን 2004 ነበር፡፡ የተፈታነው ደግሞ ከ2031 ቀናት በኋላ የካቲት 7 ቀን 2010 ዓ.ም ነው፡፡

**ክርክራችሁ ምን ይመስል ነበር?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- እኛ ከመከራከርም አልፈን ፍርድቤቱና መንግሥት ወደ ማፈግፈግ እንዲያመሩ ያደረገ ሕጋዊ ሙግት አድርገናል፡፡ መንግሥት የተከሰሰ እስኪመስል ድረስ ነበር በማስረጃና በምስክሮች ታጥቀን የተከራከርነው፡፡ ሙግታችን ለኢትዮጵያውያንም ሆነ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ንጹሕነታችንን ማሳየት እና ከሳሾቻችን እጅ ላይ የውሸት ማስረጃ እንኳ እንደሌለ ማሳወቅ በሚችልበት አቅም የተደረገ ነበር፡፡

**ለእሥር ስትዳረግ የነበረውን ሁኔታ ብታስታውሰን?**

ከአንድ ጓደኛዬ ቤት ነው የወሰዱኝ፡፡ እንደ ነገ የሚከታተሉን ደህንነቶች ለምን እንደ ሚከታተሉንና ልናናግራቸው ይገባል ብለን ኮሚቴዎቹ በስልክ ተነጋግረን ነበር፡፡ ይህንንም በስልክ ጠለፋ ሰምተዋል፡፡ ግን አዋርደው መያዝ ስለፈለጉ የነበርኩበትን ቤት በኃይል በመስበር የቤቱን ሰው በመሣሪያ አስፈራርተውና እኔን በሰደፍ፣በቦክስ፣በእርግጫ አዳክመው ነው የያዙኝ፡፡ ምን ያህል እንደመቱኝ በማላውቀው መጠን እየቀጥቀጡኝ ነው ወደ እሥርቤት የወሰዱኝ፡፡

**የጉዳት መጠንህን ማስታወስ አትፈልግም ማለት ነው?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- ቁስልን እየጫሩ መቆስቆሱ አሁን ምንም አይጠቅምም፡፡ የሀገሪቷን ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ላይ መነጋገሩ ይሻላል፡፡ ለሀገሬ ስል ሁሉንም ትቼዋለሁ፡፡ ሰውነቴ ላይ የቀሩ ጠባሳዎች ቢኖሩም ለሀገር እንደተከፈለ መስዋእትነት እቆጥረዋለሁ፡፡

**በእሥር ላይ ሆነህ አስከፊ የምትለው ጊዜ መች ነበር?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- በረመዳን የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት የደረሰብን መከራ ነበር፡፡ ጠዋት ሁለት ሰዓት ይወስዱኛል፡፡ ለፍጡር ይመልሱኛል፡፡ ማታ ሦስት ሰዓት ይወስዱኛል፡፡ ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ይመልሱኛል፡፡ በነዚህ ሁሉ ሰዓቶች ለተከታታይ ቀናት በድብደባና በምርመራ ይጠምዱኛል፡፡ እስከመጨረሻው ደብድበውኝ ማዳመጥ እያቃተኝ ሲመጣ አቆሙ፡፡ ድምጼ አልቆ ለራሴም የምለውን መስማት የማልችል ሆንኩ፡፡ ይህ ሁኔታ ለሰባት ቀን ያህል ቀጥሎ ድምጼ ሲጠፋበት መርማሪዬ እንደማልጠቀመው አውቆ መጨቃጨቁን አቆመ፡፡

**በቴሌቪዥን የተሠራጨው ‹‹ጅሃዳዊ ሀረካት›› ዶክመንተሪ እናንተ እያወቃችሁት ነው የተቀረጸው?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- አይደለም፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ ገርፈውን ሰውነታችን መለስ እስኪል ጠብቀው ነገሮች ሲረጋጉ ወደ ቀረጻቸው ገቡ፡፡ ካሜራውን ማየት ባልቻልንበት ሁኔታ ‹‹እውነቱን ካልነገርከኝ ወደ ድብደባው እንመለሳለን›› እያሉ ነበር የቀረጹት፡፡

**ከመታሰራችሁ በፊት የነበረውንና ከእስር ከተፈታችሁ በኋላ ያየኸውን ማኅበረሰብ እንዴት ታነጻጽረዋለህ?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- ማንኛውም ማኅበረሰብ የሚያልፍበት የዕድገት ደረጃ አለ፡፡ በታሪክ አንድ ሕዝብ ከፍ የሚልበትም ሆነ መውረዱ የሚለካበት መስመሮች አሉት፡፡ አንድ ማኅበረሰብ መውደቁ የሚታይበት የሕንጻ አለመኖር ወይም የመንገዱ መበላሸት ጉዳይ አይደለም፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ ውድቀት መገለጫው ሥነ-ልቦናው ነው፡፡ በፍርሃት ማቅ ውስጥ የገባ፣ የበታችነት የመሸነፍ ስሜት የተሰማው ተቃራኒውን አካል አግዝፎ የማየት ስሜት የተሰማው፣ በደልን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፣መሰል ማኅበረሰብ በቁስ ምን ቢራቀቅ፣የሚያማምሩ ሕንፃዎችን ቢሰራ ከሙት አይሻልም፡፡ እኛን ለእሥር የዳረገን ይህንን ጉዳይ ለመስበር መንቀሳቀሳችን ነው፡፡ የዚያን ጊዜው ማኅበረሰብ እምቢ ለጥቃት ባይ ሆነ፡፡ የእኛም እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ አንድ መስመር ተደርጎ፣ እርከን ወይም ኬላ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከእንቅስቃሴው በኋላ ሰዎች የሰበሩት ስሜት አለ፡፡ እራስን ሆኖ፣በደልን አብዮ፣ተከብሮ የመኖርን ስሜት ለማዳበር ትልቁ ደረጃ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ዕድገት፣ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት፣ሌላም ሌላም ይመጣል፡፡ በሞተ ሥነ-ልቦና ሀገር መሥራት ፣ታላቅ ለመሆን መጣጣርም አይቻልም፡፡ ቢቻልም ለፍቶ መና ነው፡፡ ስለዚህ ከዚያ በፊትና ከዚያ ወዲህ ያለው ማኅበረሰብ በሐገር አቀፍ ደረጃ ተለውጧል ብዬ አምናለሁ፡፡

**በተለይ የምታመሰግነው አካል ካለ?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- የማመሰግነው ብዙ ነው፡፡ የሕዝብና የመብት ጥያቄ ስታቀርብ ባለጉዳዩ ሕዝብ ተረድቶህ ከጎንህ የመሰለፉ ሁኔታ ርግጠኝነት በብዙ አገራት አስቸጋሪ ሲሆን ይታያል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ጉዳዩን ፊት ለፊት ሆነው ከሚያስተናግዱት ወይም ከሚመሩት በበለጠ፤ በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ ያላቸው፣የመምራት አቅም ያላቸው፣‹‹ያገባኛል›› የሚሉ ሰዎች ስሜት አለ፡፡ ይህ ሕዝብ ዘንድ ያለው የሞቀ ስሜትና ፍቅር እላይ ድረስ አለ ለማለት ይከብደኛል፡፡ ይህ ለአመራሮች ትልቅ ዕድል ነው፡፡ ግን ዳግም መገኘቱ የሚያጠራጥር ነው፡፡

ይህ በቀላሉ አልመጣም፡፡ የብዙ ሰዎች የረጅም ጊዜ ልፋትና በስንፍና የታጠረው የገዢው ቡድን እንቅስቃሴ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ እርምጃዎቹ፣የሚሄድበት መንገድ ሕዝቡ የሚያንገሸግሸው መሆኑ ከእጁ እንዲወጣ አድርጎታል፡፡ ሕዝብ የሚያስመሰግን ሥራ ነውና የሠራው ሊመሰገን ይገባል፡፡

በብሔርና በሃይማኖት ከፋፍሎ ለማቆረቋቆስ የተሰሩ ሥራዎች በርካታ ቢሆኑም ሕዝብ ያንን ሰብሮ ወጥቷል፡፡ ብዙዎቻችን የምናውቀው ላይ ላዩን ነበር፡፡ እሥር ቤት ከገባን በኋላ ግን የሰማናቸው ነገሮች አስደንጋጭ ሆነው ነው ያገኘናቸው፡፡ የኃይማኖት ግጭት ፈጥሮ ሕዝብን እርስበርስ ለማድረግ እጅግ የበዛ ሥራ ተሠርቶ ነበር፡፡ ብዙ ወረቀቶች ተሠርተዋል፡፡ የሰው ኃይልና በጀት ተመድቦ እንቅስቃሴ ተደርጎ ነበር፡፡

**ማንና ማንን ለማጋጨት? ይህንንስ እሥርቤት ሆነህ እንዴት ልታውቅ ቻልክ?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- የእስልምናና ክርስትና ዕምነት ተከታዮችን አንዱ በሌላው ላይ እንዲነሳበት ለማድረግ ነበር የታቀደው፡፡ እሥርቤት ሆነን ይህንን ጉዳይ በቅርብ ያውቁ ከነበሩ ሰዎች ነው መስማት የቻልነው፡፡ ለሙስሊሙ የተለየ ገጽታ በመስጠት ፖለቲከኞችንና ጋዜጠኞችን አመለካከታቸውን ለመበረዝ የተቀናጀ ሥራ ተሠርቶ እንደነበር ማወቅ ችለናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተሰበሩት ኅብረተሰቡ በነበረው ብስለት፣ግንዛቤ፣መልካምነት ጭምር ነው፡፡ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ጉዳያችንን ጉዳያቸው አድርገው በታሪክ ሊያስመሰግን የሚችል ውህደትና አንድነት በመፍጠር ሴራውን አክሽፈውታል፡፡ ውጥኑን ቀልብሰውታል፡፡ በተለይ ዲያስፖራው ፓትሪያርኩን ጨምሮ ቄሶችም፣መምህራኖችም ከኛ ጎን ተሰልፈው ትልቅ ሥራ ሰርተዋል፡፡ አይደለም ዛሬ ነገም በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ተግባር ነው ያከናወኑት፡፡ የሕዝባችን የሰለጠነ እንቅስቃሴ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ግርምትን የጫረ እንደነበርም ሰምተናል፡፡ ልናመሰግናቸው ይገባል፡፡ ከዚህም በላይ አሁንም ቢሆን ከነሱ እንጠብቃለን፡፡ የጉዳያችንን ትክክለኛ ገጽታ እንዲረዱልን አሁንም ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ በተለይ ኣለም አቀፍ የሃይማኖት መብት በተመለከተ ለሚንቀሳቀሱ አካላት፣የሰብዓዊ መብት ተቋማት፣ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች፡፡ ለዚህም ነው ተመስጋኞቹ ብዙ ናቸው ያልኩህ፡፡

**የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አሁንም አለንዴ?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- አለ፡፡ ይኖራልም፡፡ እንደውም ለቀጣዩ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ገጽታ ግንባታ ላይ የራሱ ሚና ይኖረዋል፡፡

**ስለወዳፊቷ ኢትዮጵያ መልካም መልካሙን በመመኘት እንሰነባበት፡፡ የኢትዮጵያ የወደፊት አዲስ ፊት ምን ይመስላል?**

አሕመድ ሙስጠፋ፡- በማኅበረሰብ ለውጥ ሳይንስ ሚዛን አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት ነጥብ በጣም ተስፋ ሰጪ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አንዲትን ሀገር ወደ ትልቅ ደረጃ ይመራሉ ተብሎ ከተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አብዛኞቹን አሟልታ ትገኛለች፡፡ መሪዎች ይፈጠሩበታል፣የሕዝብ ሽግግር ይደረግበታል፣ አዳዲስ ሁኔታዎች ይታዩበታል ከሚባሉ መስፈርቶች ውስጥ አብዛኞቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ታይተዋል፡፡ በጥልቀትና ሩቅ ማየት የሚችል መሪ ኖሮ ኢትዮጵያን ካሻገራት አሮጌ የችግር ታሪካችንን እየተረክን የምናላዝንበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ እስከዛሬ አንድን ቀን ብቻ ነው ስንደግም የኖርነው፡፡ 27ዓመት ኖርን እንጂ አንድን ቀን ነው ስንመላለስበት የኖርነው፡፡ ከአሁን በኋላ ግን አዲስ ቀን ይመጣል፡፡ ትናንት ያልሠራነውን የምንሠራበት አዳዲስ ቀኖችም ይመጣሉ፡፡



# አድዋ በጎሰኞች ዓይን

ክንኳን አደረሳችሁ፡፡ ለጾሙ ብቻ አይደለም፡፡ ለመፈታት ዜና፡፡

ዳንኤል ክብረት

ዛሬ ሰው በጣም በዝቷል ውጪም የቆመ ሰው አያለሁ እዚህም መሬት ላይ የተቀመጡ ብዙ ሰዎች አየሁ እና “ምንድን ነው?” ብዬ ስጠይቅ “የተፈቱት መጥተው ነው”ተባልኩ፡፡

የአድዋን በዓል ለማክበር ከየአካባቢው ከመጡ ልኡካን ጋር ስብሰባ ላይ ናቸው፡፡ ልኡካኑ ለስብሰባው የተጠሩት ምርጥ ጎሰኞች በመሆናቸው ነው፡፡ በርግጥ ብዙዎቹ ከአጀንዳው ይልቅ ውሎ አበሉ ወደ ስብሰባው አምጥቷቸዋል፡፡ ለአጀንዳው እንደሆነ ውይይቱ ሳይጀመር እነርሱ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል፡፡ የሚመጡትም ለመወያየት ሳይሆን አቋማቸውን ለመግለጥ ነው፡፡ ዋናው ነገር አቋምን መግለጥ እንጂ መወያየት አይደለም፡፡ ውይይትን ለውይይት ታክሲ ትተናል፡፡

የስብሰባው መሪ ‹‹የዛሬው ስብሰባችን የአድዋን በዓል የተመለከተ ነው፡፡ ይህንን ለመላው አፍሪካ ኩራት የሆነ ድል እንዴት ባለ ሁኔታ እናክብረው በሚለው ላይ ሐሳባችሁን ስጡ›› አሉና መነጋገሪያውን ዘጉት፡፡

አንዱ እጁን አወጣ፡፡

‹‹ወደ አከባበሩ ከመሄዳችን በፊት መመለስ ያለበት ጥያቄ አለ›› አለ ጉሮሮውን እየጠራረገ፡፡ ‹‹የአድዋ ተራራ ትግራይ ላይ እንዲሆን የተደረገው ለምንድን ነው? ሁሉም ነገር ትግራይ ላይ መሆን አለበት ወይ? ለምንድን ነው አማራ ክልል ወይም ኦሮምያ ክልል ወይም ደቡብ እንዲሆን ያልተደረገው? ይኼ የበላይነትን እያስከተለ ስለሆነ ተራራው የት መሆን አለበት? በሚለው ላይ መጀመሪያ መወያየት አለብን፡፡›› አንዳንዶች ራሳቸውን ነቀነቁ፡፡

‹‹ለመሆኑ አድዋ እዚያው በቅሎ ነው ወይስ ተወስዶ ነው? የሚለው ጥያቄ የፖሊሲ መልስ ይፈልጋል፡፡ ዋናው ሕገ መንግሥቱ ነው፡፡ ለመሆኑ አድዋ የት ነው መሆን ያለበት የሚለው በሕገ መንግሥታችን ምን ይላል? የጎሳ መሪዎች ይመልሱልን›› የስብሰባው መሪ ደነገጡ፡፡ አሁን ተራራው ወደ ደቡብ ወይም ወደ ኦሮምያ ይምጣ ቢባል ምን ያደርጋሉ? ጉድ ነው መቼም ዘንድሮ፡፡

‹‹ከዚያ በፊት የሚቀድም ነገር አለ?›› አለ አንዱ አፉ ከእጁ የቀደመ ተሰብሳቢ፡፡

‹‹አድዋ - የሚለው ስም ከምን እንደመጣ ታውቃላችሁ?›› አለና ተሰብሳቢዎችን ገረመማቸው፡፡ ታሪካዊ አመጣጡን ከመሬት ዝቆ የሚያወጣው ይመስል አሥር ጊዜ ጣቱን ዘርግቶ ከወደ ታች ያፍሰዋል፡፡ ‹‹መጀመሪያ ታሪካዊ አመጣጡን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ታሪካዊ አመጣጡን ባለማወቅ ብዙ ታሪካችንን ተዘርፈናል ጎበዝ፤ አድዋ - የሚለው ቃል - ዷ - ካለው የአማርኛ ቃል የመጣ ነው፡፡ በአድዋ ጦርነት ጊዜ ብዙ መድፍ - ዷ ማለቱን ታሪክ ያስረዳናል፡፡ ለዚህም፤

ዷ- ዷ -ዷ -ዷ ! ሲል ሲደባለቅ

## ሳንጃ ለሳንጃ ሲሞሻለቅ

የሚለው ግጥም ዋና ማስረጃ ነው፡፡ አድዋ የሚለው - ዷ - ከሚለው መምጣቱን በዚህ በሚገባ ካረጋገጥን ደግሞ መጀመሪያ በአድዋ ላይ የሠፈረው የእኛ ክልል ሕዝብ ነበር ማለት ነው፡፡ እንደዚያ ባይሆንማ - ዷ - የሚለውን ቃል መፍጠር ከዚያም ቦታውን ‹አድዋ› ማለት አይቻልም ነበር፡፡››

‹‹እርማት›› አለ አንደኛው ስሕተቱ በየሰው ጆሮ ከመግባቱ በፊት ከበር ለማስቀረት ያሰበ ይመስላል፡፡ የስብሰባው መሪ እስኪፈቅዱለት አልጠበቀም፡ ፡ በአሁኑ ጊዜ መሪን ማን ይጠብቀዋል፡፡ ‹‹እርማት አለ፡፡ አድዋ የሚለው ቃል የመጣው ‹ደዋ› ከሚለው የኦሮምኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ‹መድኃኒት› ማለት ነው፡፡ የአድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን መድኃኒት በመሆኑ ምክንያት ጥንት አባቶቻችን ያወጡት ስም ነው፡፡ ይህም እዚያ አካባቢ ከዘመናት በፊት ማን እንደነበር የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ተራራው ራሱ መቼ ወደዚያ እንደሄደ መጠናት አለበት›› አለና ለራሱ ሐሳብ ራሱ አጨብጭቦ ተቀመጠ፡፡

‹‹አንዳንዴ ነገሮችን በዝምታ የምናይበት ሁኔታ የመሥመር ስሕተት እያስከተለ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው›› አለ አንድ ሌላ ተሰብሳቢ፡፡ ‹‹ከሁሉም በፊት መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ‹ምኒልክ ካላጡት ቦታ ለምን አድዋ ላይ ለመዋጋት ፈለጉ?› የሚለው ነው፡፡ ተራራ ጠፍቶ ነው? ለምን እንጦጦ ላይ፣ ለምን ዝቋላ ላይ፣ ለምን ባቱ ላይ፣ ለምን ጉና ላይ አልተዋጉም? ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ተራራ አድዋ ብቻ ነው? የጦርነቱን ቀጠና ትግራይ ላይ ማምጣት ለምን ተፈለገ? እኛ ይኼንን ነገር የምንመለከተው ያለ ከነፍጠኛው ሥርዓት ጋር አያይዘን ነው፡፡ ነፍጠኛው ለምን እዚህ ድረስ ለመዋጋት መጣ? ለምን ጣልያን ባቱ ተራራ ድረስ እስክትመጣ ጠብቆ እዚያው አይዋጋም? ይኼ ነው መመለስ ያለበት ጥያቄ፡፡ የመሥመር ጥያቄዎች ካልተመለሱ በመሥመር መንገዝ ቀርቶ በመሥመር መዝራትም አይቻልም፡፡››

‹‹ይህንንማ ካነሣኸው›› አለ ሌላኛው ተሰብሳቢ፡፡ ሐሳብ የሚሰጥ ሳይሆን ቦንብ ለመወርወር የተዘጋጀ ነበር የሚመስለው፡፡ ‹‹ለመሆኑ አድዋ ላይ በብዛት የዘመተው ማን ነው? ይኼንን በመረጃ መተንተን ያስፈልጋል፡፡ እኔ በቀደም በፌስ ቡክ ተጽፎ እንዳገኘሁት በብዛት የሞተው የክልላችን ዘማች ነው፡፡ እንግዲህ ከፌስ ቡክ በላይ መረጃ ከየት ይመጣል? ሌላ ሌላውን ስናቀርብ ኋላ ቀር፣ ባህላዊ ትሉናላችሁ፡፡ ይኼው ዘመናዊ የሆነውን የፌስ ቡክ ማስረጃ ጠቀስንላችሁ፡፡ እንግዲህ ምን ትሆኑ? ደግሞም ሰዉ ብቻ ሳይሆን ከብቱም ያለቀው ከክልላችን ሄዶ ነው፡፡ አብዛኛውም ስንቅ የተጓጓዘው ከክልላችን ነው፡፡ ይኼን ሁሉ ከፌስ ቡክ መረዳት ትችላላችሁ፡፡

‹‹እሺ አሁን ጥያቄህ ምንድን ነው?›› አሉት ሰብሳቢው፡፡ ጥያቄ እንደዚህ ቀን ናፍቋቸው አያውቅም፡፡ መድረክ ላይ ቁጭ ብሎ እየተጠየቁ መመለስ ድሮ ቀረ፡፡ ዛሬ ሁሉ እሳት ሆኖ፡፡

‹‹አሁን እኛ የምንጠይቀው የታሪክ ጥያቄ አይደለም፤ የአካባቢያችንን ታሪክ እንዲያጠና በአካባቢያችን ዩኒቨርሲቲ ተቋቁሞልናል፡፡ እኛ የምንጠይቀው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ነው፡፡ በአድዋ ጦርነት የክልላችን ዘማች በብዛት በመሠዋቱ፤ የቀንድና የጋማ ከብቱ በብዛት በማለቁ የተነሣ፣ በሕገ መንግሥቱ ላይ በአድዋ ላይ የክልላችን ልዩ ጥቅም እንደሚከበር፣ ዝርዝሩም በሕግ እንደሚወሰን ይቀመጥልን››

ሰብሳቢው እየሰበሰቡ ሳይሆን እየበተኑ መሆናቸው ታውቋቸዋል፡፡ በዚህ ዘመን እንደመሰብሰብ ከባድ ነገር የለም፡፡ መሰብሰቢያው፣ መሰባሰቢያውና ማሰባሰቢያው ከተበላሸ በኋላ መሰብሰብ ከባድ ነው፡፡

‹‹መቼም ዛሬ ታላቅ ቀን ነው›› አለ አንደኛው ተሰብሳቢ፡፡ ቀይ አጀንዳ ይዟል፡፡ የአንድን ወረዳ የወጣቶች ሊግ ወክሎ የመጣ ነው፡፡ ‹‹አሁን የሚያዋጣን ሒሳብ ማወራረድ ነው፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚነግሩን ከክልላችን የዘመቱት ዘማቾች በአድዋ ጦርነት ጊዜ እንደ ኢትዮጵያዊ አልተቆጠሩም፡፡ ብዙ የአዝማሪ ግጥም ሊገጠምላቸውም አልቻለም፡፡ እነ አዝማሪ ጣዲቄ ሳይቀሩ በአዝማሪ ግጥም በደልና ጭቆና ሲያደርሱባቸው ነበር፡፡ እንዲያውም ከዚህ አልፎ የብሔር ጭቆና ይደርስባቸው ነበር፡፡ ብዙዎቹም በጣልያኖች ሳይሆን በምኒልክ ወታደሮች አድዋ ላይ ተገድለዋል፡፡ ባለፈው አድዋን ስንጎበኝ አንድ የመቃብር ሥፍራ አይቼ ነበር፡፡ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አስተካክሎ ከመሥራቱ በፊት የአርበኞቹ አጽም እዚህም እዚያም ወዳድቆ ነበር፡፡ ብዙዎቹን አጥንቶች ስመለከታቸው የራስ ቅላቸው ቅርጽ የኛን አካባቢ ሰዎች ራስ ቅል የሚመስል ነው፡፡ በራስ ቅሉ ላይ የሚታየው መሰንጠቅም በጎራዴ መሞታቸውን ያመለክታል፡፡ ጎራዴ ደግሞ ጣልያን አይዝም፡፡ ይህም የተገደሉት በምኒልክ ሠራዊት መሆኑን ያሳያል፡፡ ታሪክ ጸሐፊዎቹ ግን ስለ ምኒልክ ጀግንነት እንጂ ስለዚህ ግፍና ጭቆና አልጻፉም፡፡

‹‹እና ምን ለማለት ፈልጌ ነው፡፡ በአድዋ ተራራ ላይ በምኒልክ ሠራዊት በግፍ ለተገደሉ የአካባቢ ዘማቾች የተቆረጠ ራስ የሚያሳይ ሐውልት አድዋ ላይ በትልቁ ሊቆምላቸው ይገባል፡፡ ሒሳብ ማወራረድ ይሄ ነው፡፡››

ሰብሳቢው ሒሳብ ያልተማሩ እስኪመስላቸው ድረስ ተምታታባቸው፡፡ ሐሳብ ሳይኖር ሒሳብ ከየት ይመጣል፡፡

‹‹ኖ - ኖ - ኖ ዋናው ጥያቄኮ አልተጠየቀም፡፡ መጀመሪያውኑ የአድዋ ዘመቻ ነበር ወይ? ይኼ መመለስ አለበት›› የስብሰባው መሪ ራሳቸው ሲዞር ታወቃቸው፡፡ ‹‹አይ የዘንድሮ ጥያቄ›› አሉ በልባቸው፡፡ ‹‹እኛ ነን አሁን ጥያቄ መስማት የጀመርነው ወይስ ሰዉ ነው አሁን ጥያቄ መጠየቅ የጀመረው፤ እንዴት ያለ የፍርጃ ዘመን ነው›› አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ፡፡

‹‹የማንም ደብተራ የሚጽፈውን ታሪክ እየተቀበልን ለምን እንነዳለን? ምኒልክ የሚባል ንጉሥ፣ አድዋ የሚባል ዘመቻ፣ የካቲት 23 የሚባል ድል ነበረ? ምንድን ነው ማስረጃው? የሰፊውን ሕዝብ ታሪክ ላለመመዝገብ የተፈጠረ ነው፡፡ ታሪኩ እንደገና እየተመረመረ መጻፍ አለበት? የአድዋ ጦርነትስ ከነበረ ማነው የመራው? ምኒልክ? ዮሐንስ? አባ ጅፋር? ጦና? መጣራት አለበት? አድዋ ራሱ የእንግሊዝኛ ቃል ነው፡፡ ‹‹አድ ዋን›› ከሚሉት ሁለት የእንግሊዝኛ ቃላት የመጣ ነው፡፡ ‹‹አንድ ጨምር›› ማለት ነው፡፡ እዚያ አካባቢ ሠፍረው የነበሩት እንግሊዞች ናቸው ይህንን ስም የሰጡት፡፡ እንግሊዞች እዚያ ሠፍረው ከሀገሩ ሰው ዕንቁላል ሲገዙ ‹አድ ዋን - አድ ዋን፤ አንድ ጨምር፣ አንድ ጨምር› ስለሚሉ ሕዝቡ ይህን ይዞ ‹አድዋ› አለው፡፡ በቃ ይሄው ነው፡፡ የጣልያን እዚያ አካባቢ አልወረረም፣ አልተሸነፈም፡፡ ከዚህ በላይ ማስረጃ ከየት ይምጣ፡፡ ይህን ደግሞ መምህር እንትና በሚገባ ተንትነውታል፡፡ የድርጅታችንም አቋም ነው ይኼ፡፡ ታሪክ የሚጠናውና የሚነገረው በድርጅት እንጅ በታሪክ ጸሐፊ ወይም በታሪክ ተመራማሪ አይደለም፡፡ ዋናው ድርጅት ነው፡፡ አሁን እዚህ የምታወሪ ሁሉ ምን ድርጅት አለሽ? እናንተስ ይሄንን የተሰባሰባችሁት በምን ድርጅት ነው የተሰበሰባችሁት? ያለ ድርጅት ከሆነ ከባድ የመሥመር ስሕተት ብቻ ሳይሆን - መርሕ አልባ ግንኙነት እየፈጠራችሁ ነው ማለት ነው፡፡

መጽሐፍ፣ ጥናት፣ አርኬዎሎጂ፣ ሳይንስ፣ መረጃ፣ ማስረጃ ከድርጅት በላይ አይሆንም፡፡›› ሰውየዉ ተሰብሳቢ ሳይሆን ተቆጭ ነው የሆነው፡፡ ለካስ እዚህ ሀገር ከሰብሳቢ የሚበልጥ ተሰብሳቢ፣ ከጠቅላይ የሚበልጥ ተጠቅላይ አለ፡፡

‹‹በቃ፤›› አሉ ሰብሳቢው መርሯቸው፡፡

‹‹ከቁሮ የመጣ የለም?›› አሉ፡፡ የተወሰኑ ወጣቶች ብድግ አሉ፡፡

‹‹ባካችሁ እንደ በቀለ ገርባ አድዋንም አስፈቱትና ገላግሉን›› አሉ ሰብሳቢው፡፡



ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ

# “ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ድንገት ነው እጇ ላይ የወደቀችው ”

## ዶ/ር ታየ ንጉሴ

ዶ/ር ታየ ንጉሴ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ማህበረሰብ መምህር እና ማህበራዊ ሃያሲ ናቸው። በወቅታዊ የአገራችን ጉዳይ ላይ አነጋግረናቸዋል።



ግዮን፡- የኢትዮጵያ ወቅታዊው ፖለቲካ ለውጥ እያመጣ ነው ወይስ ራሱ ፖለቲካው እየተለወጠ ነው ማለት ይቻላል?

ዶ/ር ታየ፡- ሳይንሳዊ ትንተና መስጠት የሚቻለው ክስተቱ መደበኛ ሲሆን ነው። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ግን ከመደበኛው የፖለቲካ ክስተት ለየት ያለ ነው ። ያልተለመደ አካሄድ ነው ያለው። ለመተንተን ትንሽ ያስቸግራል።

ግዮን፡- ያልተለመደ የፖለቲካ አካሄድ ምን ማለት ነው?

ዶ/ር ታየ፡- ስርአቱ ጠቅላይ ወይም ለአምገባነናዊ ስርአት የተጠጋ ነው።

ግዮን፡- አምባገነናዊ ስርአት የይዘት ጉዳይ እንጂ እንደ ዴሞክራሲያዊ ሁሉ በመደበኛ ስርአት የሚመራ አይደለም ማለት ይቻላል ?

ዶ/ር ታየ፡- ልክ ነህ። ይህ ስርአት ግን ከሁለቱም የተለየ ባህሪ አለው። ለምሳሌ በጣም ያስገረመኝን ነገር ልንገርህ። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት መግቢያ “እኛ የኢትዮጵያ ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች…” ይላል። ይህችን ሃረግ ወስጄ ከተለያዩ አገራት ህገ መንግስቶች ጋር አስተያየሁት ። ማንም አገር ይህን ሃረግ ተጠቅሞ አላገኘሁትም። የኢትዮጵያን ህገ መንግስት ያረቀቁ ሰዎች ህገ መንግስቱ በአብዛኛው የሚቀርበው ለናይጄሪያ፣ ለህንድና ለአሜሪካ እንደሆነ ነው የሚናገሩት ። የሶስቱንም አገር ህገ መንግስቶች ሳይ አንዳቸውም ይህን ሃረግ አልተጠቀሙም። ለምሳሌ የናይጄሪያ ህገ መንግስት “እኛ የናይጄሪያ ህዝብ” ነው የሚለው ። አንድ የናይጄሪያ ህዝብ መሆኑን ነው የሚያመለክተው። እኛ የህንድ/የአሜሪካ ህዝብ ነው የሚለው። አንድነትን ነው በህገ መንግስታቸው የሚያሳዩት። እጅግ በጣም የገረመኝ ይህ አይደለም። ትናንት (በቃለ መጠይቁ እለት) የሶሪያን ግጭት በሚመለከት የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ የመንግስታቱን ቻርተር መግቢያ ሲገልፁ ደነገጥኩ። “ እኛ የተባበሩት መንግስታት ህዝብ” ነው የሚለው ። የአለም መንግስታት እንኳ ያልከፋፈለውንና “ህዝብ” ብሎ የሚጠራውን ነው የእኛ ሀገር ህገ መንግስት “ ሕዝቦች “ ብሎ የሚጠራው ።

ግዮን :- " ሕዝቦች " ማለት ችግር የሚሆነው ምኑ ላይ ነው ?

ዶ/ር ታየ፡- አባባሉ የብዙ ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ስብስብ እንጂ አንድ ኢትዮጵያ የለችም የሚል ትርጉም ነው ያለው ። ማን ነው ብሔር ? ማን ነው ብሔረሰብ ? ማንስ ነው ህዝብ ? ህገ መንግስቱ ለይቶ አላስቀመጠውም።

ግዮን :- የቀደመውን ጥያቄ አልመለስክልኝም ።

ዶ/ር ታየ :- የቱን ?

ግዮን፡- ወቅታዊው ፖለቲካ ለውጥ እያመጣ ነው ወይስ ራሱ ፖለቲካው እየተለወጠ ነው? የሚለውን ።

ዶ/ር ታየ፡- አሁን ያለው ስርአት ሳይወደው፣በግድ ወይም ሳያስበው በራሱ ጊዜ እየተለወጠ እየመጣ ነው። እያንዳንዱ የፖለቲካ ስርአት የራሱ የሆነ እድገት አለው። ይወለዳል፤ያድጋል ፤ ያረጃል፤ይሞታል። አሁን ያለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስርአት አርጅቶ ወደ መቃብር በመውረድ ላይ ነው ያለው። ይህ ውስጡ ባሉ ወይም በውጪ ሰዎች ሳይሆን ተፈጥሯዊ የሆነው ታሪካዊ ሂደት ያመጣበት ነው።

ግዮን፡- የተፈጥሮ ሂደት ራሱ እየለወጠው ነው ስንል ማሳያችን ምንድነው?

ዶ/ር ታየ፡- የተለያዩ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ስርአቱ ቅቡልነቱን በመሰረታዊነት አጥቷል። ስርአቱ ከመጀመሪያው ጀምሮ ራሱን ዲሞክራሲያዊ እንደሆነ አድርጎ ይጠራል። ዲሞክሪሲያዊ ስርአት ማለት ከህዝብ፣ በህዝብ፣ ለህዝብ ማለት ነው። አንድን መንግስት ዲሞክራሲያዊ ነው የሚያስብለው የምርጫው እለት ድርጊት ሳይሆን ሂደቱ ነው። ስርአቱ ቅቡልነቱን ለማጣቱ ከ1997 ውጪ ያሉትን ምርጫዎች በእለቱ ወጥተህ እያቸው ። ድንኳኖች ባዶ ናቸው። ህዝቡ ለመምረጥ አይወጣም። ይህም ሆኖ ውጤቱ ሲገለፅ 99 እና 100 በመቶ ይባላል። እንኳን እንዲህ በጥቂት አመታት ውስጥ ሁሉም ግድግዳዎች የተሰነጣጠቁበት ቀርቶ የቱም ተፈላጊ መንግስት መቶ በመቶ ሊያሸንፍ አይችልም። ቁጥሩ በራሱ የምርጫውን ተአማኒነት ያሳጣዋል። አሁን ያለችውን አገር ስታያት 2007 መቶ በመቶ ያሸነፈ የፖለቲካ ድርጅት የሚመራት ትመስላለች?

አሁን በአገሪቱ በሁሉም አቅጣጫ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመፅ የመንግስትን ቅቡልነት ማጣት ያሳያል። በየክልሉ የምታየው የተቃውሞ ሰልፎች የአንድ ጊዜ ብሶት ፍንዳታዎች አይደሉም። የተጠራቀሙ ብሶቶች ውጤት ነው። አመፅ የተጠራቀመ የረጅም ጊዜ የፍትህ መጓደል ውጤት ነው።

ግዮን፡- በአገራችን “ተበዳይ” የሚባል ህዝብ አለ። ነገር ግን ትናንትም ሆነ ዛሬ “በዳይ” የሚባል ህዝብ አለ?

ዶ/ር ታየ፡- ይህ ነው ትልቁ የዚህ ስርአት ችግር። ስርአቱ በዳይና ተበዳይ ብሎ የከፈላቸው ህዝቦች አሉ። ማን ነበር በዳዩ ህዝብ? ለጊዜው በዳይነትን በአንድ ህዝብ ላይ ጭኗል ። ተበዳይነትን ደግሞ ለተቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰጥቷል። ሙሉ ለሙሉ ሁሉ የተሟላለትና ድህነት የማይነካው ደሴት ላይ የሚኖር ህዝብ አለ እንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ? ይህ ስርአቱ የፈጠረው የህልም ዓለም ነው።

ግዮን፡- ስርአቱ ሌላን የህብረተሰብ ክፍል መፈረጇ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ደግሞ ዛሬ የተቀናጣ፣ ምንም ያልጎደለበት ጨቋኝ ህዝብ እንዳለ አድርገው አንድን ብሔር የነጠለ የጥላቻ ስሜትን ሲያራግቡ ይታያል። በአሁኑስ ወቅትስ ቢሆን በተለየ ሁኔታ ተጠቃሚ የሆነ ህዝብ አለ?

ዶ/ር ታየ፡- አንድ ህዝብ ሙሉ ለሙሉ ገዢና ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም። በውስጡ የተወሰኑ ሰዎች ተጠቃሚና ገዥ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ተግባራዊ ሳይሆን ምናባዊ ነው ። በየትም ሃገር ገዥ የሆነ ህዝብ አልታየም። በእኛም አገር ያለው እውነታ ይህ ነው ። ትናንትም ሆነ ዛሬ ገዥ የሆነ ህዝብ የለም።

ግዮን፡- ብሔርን መሰረት ባደረጉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከመመስረቱ ጋር ተያይዞ “ኢሕአዲግ” የሚለው ምህፃረ ቃል ወይም “የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር” የሚለውን ስያሜ የማይቀበሉና ግንባሩ በስያሜ ካልሆነ በተግባር ሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች የሚወክል አይደለም (ከአራቱ ውጪ) የሚሉ አሉ።

ዶ/ር ታየ፡- አዎን እኔም እሱን ነው የምቀበለው፡ ፡ ግንባሩ አወቃቀሩም ሆነ አካሄዱ አሁንም ቢሆን መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚነሱበት ነው። የተወሰኑ የህብረተሰቡ ክፍሎችን ያቅፋል እንጂ እንደውም በሚገርም ሁኔታ ዳርቻ ላይ ያሉትንና ከዚህ በፊት “ተገፍተዋል ፤ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረዋል” ያላቸውን እንደ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል፣

ሶማሌ ክልሎችን በግንባሩ ውስጥ አላካተታቸውም። ኢሕአዴግን እኔ የማየው አጋጣሚ፣ታሪክ የወለደው ነው ። ኢትዮጵያ የምትባለው አገር ድንገት ነው እጁ ላይ የወደቀችው።

ግዮን፡- ለምን ድንገት? ለ17 አመታት ታግሎና በርካታ የህይወት መስዋዕትነት ከፍሎ ነው እንጂ ።

ዶ/ር ታየ፡- እሱ ልክ ነው። እኔም ሀቁን አልክደወም። በኢሕአዲግ ውስጥ ትግሉን የጀመርነውና ለረጅም ጊዜ ከደርግ ጋር ሲዋጋ የነበረው ሕወሓት ነው። ሕወሓት ኢሕአዲግ የሆነው ወዶ ነው ወይስ ታሪክ አስገድዶት ነው ። ድርጅቱ ኢትዮጵያን ከወታደራዊ ስርአት ለማላቀቅ ሳይሆን የትግራይን የፖለቲካ ጥያቄ ለመመለስ የተቋቋመ መሆኑን ስሙ ራሱ ያመለክታል። ስሙ "ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ" ነው የሚለው። ለትግራይ ሓርነት ወይም ነፃነት ተመስርቶ ሳለ ከትግራይ አልፎ መላውን አገር ማስተዳደር ስለማይችል ለይስሙላም ቢሆን ኢሕዴን (ብአዴን) እና በመጨረሻ ላይም ኦህዴድ የሚባሉ ድርጅቶችን ተፈጥረዋል። ይህ ጊዜያዊ የፖለቲካ ታክቲክ ነው ። ሕወሓት ከጥንስሱ "ኢትዮጵያ" የሚል የፖለቲካ አጀንዳ አልነበረውም። ኢትዮጵያ የሚለውን አጀንዳ ማስተጋባት የጀመረው በታሪክ አጋጣሚ ኢትዮጵያ እጁ ላይ ስትወድቅ ያንን ለማስተናገድ የተፈጠረ አወቃቀር ነው ። ኢሕአዴግ ዛሬም ድረስ በየጊዜው የሚለዋወጠውና ወጥነት ያጣው ለዚህ ነው።

ግዮን፡- በአገሪቱ እዚህና እዚያ የተቀጣጠሉት ህዝባዊ አመፆች ብቻ ሳይሆኑ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ሶስት ከፍተኛ አመራሮች በፈቃዳቸው ስልጣናቸውን ለመልቀቅ ደብዳቤ አስገብተዋል። በቀደመው የድርጅቱ የፖለቲካ ዲሲፕሊን "ድርጅቱ ካዘዛቸው ሊስትሮም ሆነ ምንም ሆነው እንደሚሰሩ " ሲገልፁ ነበር የሚሰሙት። ይህ ሁኔታ ግንባሩ መገፋቱን ብቻ ሳይሆን ራሳቸው አባላቱም ፊት እየነሱት መምጣታቸውን ያሳያል ማለት እንችላለን ?

ዶ/ር ታየ፡- የቀድሞዎቹ የእህት ድርጅቶች አመራሮች በአመዛኙ ከእናት ድርጅታቸው ይልቅ ለሕወሓት ታማኞች ነበሩ። በተለይ በኦህዴድና ብአዴን ውስጥ ያሉ አዲሶቹ ትውልዶች ግን የነበረውን ታማኝነት መግፋትና መቃወም ጀመሩ። ስለዚህ በግንባሩ ውስጥ የትውልድ ክፍተት ተፈጥሯል። የሶስቱ አመራሮች ከድርጅቱ "እንለቃለን" ማለት ብዙም ትርጉም የሚሰጥ አይደለም። አዲሱ ትውልድ ለሕወሓት ያለውን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ሲያስገባው ነው "እንለቃለን" ያሉት። ግን እነዚህ ሰዎች እንዳሉትም ለቀዋል? ሁለቱ ተመልሰው ገብተዋል። እነዚህ ሁለት አመራሮች ሕወሓትን ከሌሎቹ እህት ድርጅቶች ጋር የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው። እነሱ ወጥተው ድልድዩ እንዳይሰበርም ነው የተመለሱት።

ግዮን፡- ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ ኦህዴድና ብአዴን የተለየ ቅርበት የመፍጠር አዝማሚያ እያሳዩ ይገኛሉ። ይህ የምን ምልክት ይመስልሃል?

ዶ/ር ታየ፡- ይህም የአዲሱ አመራር ራሱን የመቻል ውጤት ነው። የአማራና ኦሮሞ ህዝቦች እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ እጅግ የተከበረ ህዝብ ነው። ባለፉት 26 አመታት እንደተሰበከው ጥላቻ ቢሆን፣ አማራው ታሪካዊ በዳይ፣ ኦሮሞው ተበዳይ ተደርጎ እንደተቀነቀነው ቢሆን ሁለቱ ህዝብ ገና ድሮ በተጫረሰ ነበር። ግን የታሰበው አልሆነም። ሁለቱን ህዝብ እንደበዳይና ተበዳይ ተደርጎ ከመሰብኩም በላይ ጥላቻና ጥርጣሬው መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ ሃውልት እስከማቆም ተደርሷል። አሁን የሚታየው " ወንድማማቾች ነን" ማለቱን ነው። ከፍተኛ የሆነ የምልክት መልዕክት አስተላልፈዋል። "ጣና ኬኛ ( 'ጣና የእኔ ነው') " የሚለው የኦሮሞ ወጣቶች የባህር ዳር ጉዞ "ምንም እንኳን በመካከላችን የጥላቻ ግንብ ቢገነባም እሱን አፍርሰነዋል" የሚል መልዕክት ነው ያስተላለፈው ። የጥላቻ ስሜት ለሁሉም ህዝብ ምቾት አይሰጥም። ፍቅር ደግሞ ሁሉን አዳኝ ነው።

ግዮን፡- በምንም ሁኔታ ውስጥ ብንገኝ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ግጭት ይነሳል ወይም ኢትዮጵያ ትፈርሳለች የሚል ስጋት አለህ?

ዶ/ር ታየ፡- በፍፁም የለኝም። አሁን ያነሳኸው ጥይቄ ራሱ ገዥው ግንባር ኢትዮጵያን በእሱ የመግዛት ዘመን ልክ አድርጎ ለመስፋት የቆረጠውና የቀጠለው የፕሮፖጋንዳ ቅስቀሳ ውጤት ነው። ፍርሃት እንዲሰማህ፣ ያለ ኢሕአዲግ የማትኖር እንዲመስልህ ይፈለጋል። በመጀመሪያ ደረጃ "የተለያዩ አንጃዎች ነፍጥ አንስተው አገሪቱን ሊያፈርሷት ሲሉ እኔ ነኝ የደረስኩላት " ይልሃል ። የሚገርመው ነገር ያኔ የነበሩት እነ ኦብነግ እና ኦነግ አሁንም አሉ። እንደውም አሁን አዲስ የተቋቋሙና ነፍጥ ያነሱ ድርጅቶች ተጨምረውባቸዋል ። ለምን እነሱ ጠፍተው ከስጋት ነፃ አልሆንም? ግንቦት 20/1983 በአገራችን የስርአት ለውጥ ሲመጣ እኔ በስራ አጋጣሚ ኦጋዴን ጫፍ ጎዴ ነበርኩ። የሚገርመው ነገር አዲስ አበባ የተካሄደው የመንግስት መ/ቤት ዝርፊያ ጎዴ ጫፍ ላይ ከመንግስት መ/ቤት እስፒል አልተወሰደም። ወታደሩ ጠመንጃ ትቶ ሲሄድ ኢሕአዴግ እንደሚለው ወደመፍረስ ሳይሆን የሄዱት የአገር ሽማግሌዎች ተውጣጥተው የኦጋዴን ራስ ገዝ ዋና አስተዳዳሪ በነበሩት አቶ በሽር ሼካ አብዲ አገሩን አረጋግተው የኢህአዴግ ሰራዊት ሲመጣ ያስረከቡት እሳቸው ነበሩ። ስጋቱ እንጂ እውነቱ የለም።

ግዮን፡- በአዲሶቹ የኦሕዴድ አመራሮች ቀደም ሰል ያልታየ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ( በንግግር ደረጃም ቢሆን ) የመታየት፣ የቀድሞው የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ወደ 3 ማሊዮን ብር የሚያወጣ መኪና፣የህክምና ወጪያቸውን በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ የመሸፈን፣ የማማከርና የመሳሰሉትን መጠነኛ ስራ ሰርተው ጠቀም ያለ ደመወዝ እንዲታሰብላቸው በማድረግ ከመራራቅና ጥላቻ ፖለቲካ ወጥተው የመቀራረብና የፍቅርን መንገድ የማሳየት ጅምሮች ታይተዋል። ይህ ለውጥ ከየት የመጣ ይመስልሃል?

**...ይህ ጊዜያዊ**
**የፖለቲካ ታክቲክ ነው ።**
**ሕወሓት ከጥንስሱ "ኢትዮጵያ" የሚል**
**የፖለቲካ አጀንዳ አልነበረውም።**
**ኢትዮጵያ የሚለውን አጀንዳ**
**ማስተጋባት የጀመረው በታሪክ**
**አጋጣሚ ኢትዮጵያ እጁ ላይ ስትወድቅ**
**ያንን ለማስተናገድ የተፈጠረ**
**አወቃቀር ነው...**

ዶ/ር ታየ፡- ኦህዴድ ከድርጅቱ ተገንጥሎ ወጥቶ የራሱን ነፃነት የማወጅ፣የራሱን መርህ አውጥቶ ባናየውም ኦህዴድም ሆነ ብአዴን የቀድሞዎቹ እንዳልሆኑ ግን ብዙ ማሳያዎች አሉ። ድርጅቶች ቀድሞውን ሲፈጠሩ የራሳቸው ነፃነት ኖራቸው፣ የራሳቸው ህልውና ኖሯቸው፣በራሳቸው እንዲቆሙ አይደለም ታስቦ የነበረው። አሁን ያለው ከሌሉች መገልገያነት ወደ ነፃነት የሚደረግ ጉዞ ነው። ኦህዴድ አሁን ባለው ሁኔታ ከክልላዊነት ወደ ብሄራዊ ፓርቲነት የመለወጥ አዝማሚያ እየታየበት ነው። ኢሕአዴግ ከሚባለው አገራዊ ድርጅት ይልቅ ኦህዴድ ነው ስለኢትዮጵያዊነት እየዘመረ ያለው ። በአገር ውስጥና በውጪ ላሉት ተቃዋሚዎች ጥሪ ሲያቀርቡ እንደ ክልላዊ ሳይሆን እንደ አገሪቱ ፓርቲ ሆኖ ነው።

ግዮን፡- ይህን ማድረግ ግን መብቱ ነው? የፌደራል መንግስቱን ስልጣን የመቀማትና የማፈንገጥ ጠባይስ አይደለም?

ዶ/ር ታየ፡- መብቱ ላይሆን ይችላል። በትግል ያገኘውና ሂደቶች ያጎናፀፉት የሞራል ብቃት ነው። "ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው" ብሎ ተቀብሮ የነበረውን የኢትዮጵያዊነት ስሜት ቆፍሮ አወጣው። ክልላዊው ኦህዴድ ከአገራዊው ኢህአዴግ በላይ ህብረ ብሔራዊ መልክ እየያዘ ነው። ህዝቡ ደግሞ ውጪ ካሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከኢህአዴግ በበለጠ እምነቱን የጣለው በአዲሱ ኦህዴድ ላይ ነው። ይህች አገር ከብጥብጥ እንድትድን ይህን ስርአት በሰላማዊ መንገድ ከውስጥ ለመለወጥ እድሉ ኦህዴድ እጅ ላይ አለ የሚል የህዝብ እምነት አለ። በምሁራንና በውጭ ተቃዋሚዎች ሳይቀር ተስፋ ተጥሎበታል። ፕሮፌሰር መስፍንም ካሁን ቀደም ለሌሎች ብለው በማያውቁት መልኩ በአቶ ለማ መገርሳ ላይ ያላቸውን ተስፋ ቪኦኤ ላይ ሲናገሩ ሰምቻለሁ።

ግዮን፡- ሰሞኑን በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ የፖለቲካ እስረኞችን ክሳቸው እየተቋረጠና የተፈረደባቸውም ምህረት እየተደረገላቸው ተፈተዋል። ይህ ሂደት መንግስት እንደሚለው የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ወይስ አንዳንዶች እንደሚሉት የመንግስትን እጅ መጠምዘዝ ወይስ ሌላ ሁኔታን የሚያሳየው አንድምታ አለው?


ዶ/ር ታየ፡- በመጀመሪያ ከቀናው ሃሳብ ለመነሳት እነዚህ ሰዎች የፖለቲካም እስረኛ ይሁኑ፣ ወንጀለኛም ይሁኑ፣ ሳያጠፉም ይታሰሩ በማንኛውም መንገድ መፈታታቸው በጎ ነው። እሰየው የሚያሰኝ ትልቅ እርምጃ ነው። በይሁንታ የሚታለፍ እርምጃ ነው። ነገር ግን አሁንም ይህ መንግስት ባለፉት አመታት እንዳደረገው ሁሉ ለፖለቲካ ፍጆታ አውሎት እናገኘዋለን። ከተፈቱት እጅግ አመዛኞቹ ስም ያላቸውና ህዝቡ በስም ጠርቶ የሚያስታውሳቸው ናቸው። እነዚህን የፖለቲካ መሪዎች ይከተሏቸው የነበሩና በእነሱ ሳብያም የታሰሩ፣ ብዙም በስም የማይታወቁ በርካታ እስረኞች በወህኒ እንደሚገኙ ሲታይ እርምጃው እንደተለመደው ፖለቲካዊ እንጂ ከልብ በመነጨ የይቅር ባይነት ስሜት እንዳልመጣ ትረዳለህ ። መሪውን ፈተህ ተከታዩን እስር ቤት ማቆየት ጤናማ ነው?

ግዮን፡- እስቲ ስለ እስረኞቹ ገታ እናድርገውና ስለ እስር እንነጋገር ። የተቃውሞ እንቅስቃሴን ከማዳከም አንፃር ፖለቲከኞችንና ደጋፊዎቻቸውን ማሰር ፋይዳው ምንድነው?

ዶ/ር ታየ፡- በመጠኑም የስርአቱን እድሜ ከማራዘም ያለፈ ፋይዳ የለውም። መታሰር፣ መገረፍ፣ መሰቀል የመጨረሻ ነፃነትህን አይነጥቅህም። ይመስለዋል አሳሪህ፣ ይመስለዋል ቀጥቃጭህ። በውጤቱ ግን እንደውም የቆምክለት አላማ ይበልጥ ገኖና ጠንክሮ ሊወጣ ይችላል። መግረፍ፣መግደል፣መስቀል የሰውየውን አላማ የሚያስቀይር ቢሆን ዛሬ ክርስትና የሚባል ሃይማኖት ባልኖረ ነበር። ከእየሱስ መሰቀል ጋር የክርስትና ሃይማኖት በዚያው በቀረ ነበር። ኔልሰን ማንዴላን በማሰር አፓርታይድ የነበረበትን ተቃውሞ አዳፍናለሁ ብሎ አስቦ ነበር። ነገር ግን የሰውየው መታሰር የስርአቱን መገርሰሰ አስቀረው? አላስቀረውም።

ግዮን፡- የእስረኞች መፈታት የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ስላለው ድርሻ እናውራ። በእርግጥ የእስረኞች ፍቺ የተባለውን ውጤት ያመጣል?

ዶ/ር ታየ፡- ገና ከመነሻው ቀደም ሲል እንደገለፅኩት እስረኞች በተፈለገው ፍጥነትና መጠን አልተፈቱም። ፖለቲካዊ ምህዳሩ የጠበበው በህግና ተቋማትን በማሽመድመድ ነው። እነዚህ እስረኞች ቢፈቱም በማያሰራ ህግና በተሽመደመዱ ተቋማት ውስጥ እንዲሰሩ ከሆነ አሁንም መፈታታቸው ትርጉም አያመጣም። የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት በዋነኝነት ምህዳሩን ያጠበቡ ህጎችን የማሻሻልና እስረኞች ያነሷቸው የፖለቲካ ጥያቄዎች መፈታት አለባቸው። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅና የፖለቲካ ምህዳርን ማስፋት ሁለቱ አብረው የሚሄዱ አይደሉም። አዋጁ በተፈጥሮው የፖለቲካ ምህዳሩን የሚያጠብ ነው። ብዙ ክልከላዎች ያሉበት ነው። መሰብሰብን፣ መቃወምን፣ሰላማዊ ሰልፍን ይከለክላል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ። ስለዚህ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ናቸው አንድ ላይ የተሰጡን ። ስለዚህ የምህዳር መስፋት የሚባል ምልክት ቢያንስ ለእኔ እየታየኝ አይደለም ።



# <<ይህ ሕዝብ ነፃነት! ፍትሕ! ክብር! ይገባዋል!!!>>

## አንዱዓለም አራጌ

- መስከረም 3 ቀን 2004 በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ዋለ
- የካቲት 7 ቀን 2010 ዓ.ም ከእሥር ተፈታ
- የክስ ቻርጁ «የአሸባሪው ግንቦት ሰባት አመራር አባል...» ይል ነበር።
- በማዕከላዊና በቃሊቲ ታሥሮ ቆይቷል።
- በእሥር ቤት እያለ ይናፍቀው የነበረው፣ በአደባባይ ከሰዎች ጋር በነፃነት መዋልና መጨዋወት...

አንዱዓለም አራጌ እንደሚለው ወደ ፖለቲካው ሕይወት የገባው በሁለት ዐብይ ምክንያቶች ነው። አንደኛው ተማሪ በነበረበት የወጣትነት ዘመኑ በፖለቲካ አቋም መለያየትና መካረር የተነሳ ኢትዮጵያ የገባችበትን የእርስ በርስ ጦርነት ሁኔታ መመልከቱ ነው። በተለይ በዚያ የእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ ሻዕቢያና ወያኔ የሀገር አንድነትን በተመለከተ ይሰነዝሩት የነበረው ሐሣብ፣ በተለይም ኢትዮጵያዊነትን እያራከሱ የሚያቀርቡበት ሁኔታ በአዕምሮው ውስጥ ህመም ፈጥሮበት የቆየ መሆኑና ለህመሙም መድኃኒት ሊሆን የሚችል፣ በጎውን የኢትዮጵያዊነት እሴት እና የሕዝቡን አንድነት የሚያስቀጥል መፍትኄ ያስፈልገዋል ብሎ ማለሙ ነው። ሁለተኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ሆኖ አለመኖሩን ከመገንዘቡ በመነጨ ስሜት፤ ወደፊት የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት ሊሆን የሚችልበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት ይኖርበታል ብሎ ማመኑ ነው።

በእሱነቱ ውስጥ እንደዚህ የተዘራውን፣ ያበቀለውን፣ አፍርቶ መጎምራት የጀመረውን የሀገርና የወገን ቀናኢነት ህልምና ዕምነቱን እውንና ተግባራዊ ለማድረግ ሲልም ያዋጣል ብሎ በወሰነበት ሰላማዊና ሕጋዊ የፖለቲካ ትግል ተሳትፎውን በ1993 ዓ.ም ጀመረ። በለውጥ ፈላጊነቱ ዓለም ከቆየባቸው 17 ዓመታት ውስጥም ከስምንት ዓመታት በላይ የሚሆኑትን ጊዜያቶች በእሥራት አሳለፈ። በወህኒ እያለም «የሀገር ፍቅር ዕዳ» የሚል መጽሐፍ ጻፈ። ማንዴላ እንዳሉት «የአሣሪው ዓላማ እሥረኛውን በአካልና በመንፈስ ሰብሮ ማውጣት» ቢሆንም፤ አንዷለም አራጌ ግን ራሳቸው ማንዴላ «የታሣሪው ዓላማ በሥነ-ልቦናም ይሁን በአካል ሳይሰበር መንፈሰ ጠንካራ ሆኖ መውጣት ነው» በማለት ያስተላለፉትን መልዕክት፤ የእሥራት ዘመኑ ሕይወት መርሆ አድርጎ ቆይቷል። እኛም ከእሥር ቤት ከወጣ በኋላ ለመጽሔታችን ጥያቄዎች የሰጠውን ምላሽ እነሆ ብለናል።

**ግዮን፦ በተያዝክበት ቀን ምን ስታከናውን እንደነበር፣ ከተያዝክም በኋላ ስላጋጠመህ ሁኔታና በወቅቱ ስለተሰማህ ስሜት ብትገልጽልን?**

አንዱዓለም፦ የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ የሕዝብ ግንኙት ኃላፊ እንደመሆኔ ፓርቲያችን አዘጋጅቶ በነበረው አንድ ወቅታዊነት ያለው ጥናታዊ ጽሑፍ በሚቀርብበት መድረክ፤ ከጽሑፍ አቅራቢው ከጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር ነበርኩ። ከመድረኩ መዘጋጀት በኋላ እስክንድር በራሱ ወጪ በመድረኩ ላይ የቀረበውን ሐሣብ ወደ አብዛኛው ለውጥ ፈላጊ ሕዝብ ለማድረስ በመፈለጉ በዚሁ ጉዳይ ከእሱ ጋር ተነጋገርን እንዳበቃን ያንን የመድረክ ውይይት በሲዲ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎችን ለማግኘት የበኩሌን ጥረት እያደረኩ ነበር። በተለይ በተያዝኩበት መስከረም 3 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ግ ደርሶኝ እግዚአብሔር ያደለኝን ልጄን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደትምህርት ቤት ያደረስኩት ዕለት ነበር። ልጄም ከእኔ ተለይቶ ወደ ትምህርት ቤት ሊገባ ሲል እጄን ለመልቀቅ አልፈለገም። በድንጋጤና በቅሬታ ስሜት እየተመለከተኝ ነበር። ልጄን ሩሕን በዚያ ሁኔታ ትምህርት ቤት ካስገባሁት በኋላ ከበላይ ፈቃዱ ጋር በመኪው ውስጥ ሆኜ፤ ልጃችንን ከትምህርት በኋላ ማን ወደ ቤት እንደሚመልሰው ከባለቤቴ ጋር በስልክ እየተነጋገርኩም ነበር። እንደዚሁም በዚያው ቀን ያን የውይይት ሲዲ ከሚያትሙት ሰዎች እንዲገኛኝ ለማድረግ ከእስክንድር ጋር ቀጠሮ ነበረን። እሱም ደግሞ በሰዓቱ ልጁን ከትምህርት ቤት ወደ ቤቱ ለመመለስ በዝግጅት ላይ ነበር።

እና አልፎ አልፎ አንድ ቀን ሊይዙኝ ይችላሉ፣ ወይም እንደለመድኩት በእግሬ ከቦታ ቦታ ስዘዋወር ሊገድሉኝ ይችላሉ ብዬ አስብ እንደነበረው፤ ይህንኑ ጉዳይ ሳሰላስልና ለፓርቲያች መሥራት የሚገባኝን ሥራ ፈጥኜ ላከናውን... እያልኩ ከራሴ ጋር በምነጋገርበት ደቂቃ ሊይዙኝ ከመጡት የፌደራል ፖሊስ ባልደረቦች አንዱ እኔና በላይ የነበርንበትን መኪና መስኮት አንኳኳ። ከዚያም ልጄን ከትምህርት ቤት ሳልቀበለው ወደማዕከላዊ ተወሰድኩ። ያም በመሆኑ ያን ዕለት በሕይወቴ እጅግ ከባድና ጥልቅ ኀዘን ተሰማኝ። ልጄ የመጀመሪያዬ ነው። ከዚያም በፊት ትምህርት ቤት ወስጄው አላውቅም ነበር። ለእሱም ይሁን ለእኔ ወደትምህርት ቤት መሄዱና መውሰዱ ገና አንድ ብሎ መጀመሩ ነበር። የልጄን አዋዋል ልጠይቀው እያሰብኩ በነበረበት ሁኔታ ተለያየን። ያም ብቻ ሳይሆን «ቤቱ ይፈተሽ» ብለው መኖሪያችንን ለመበርበር ከፖሊሶች ጋር በሄድኩበት አጋጣሚ፤ ልጄ በመጋረጃ ተጠቅሎ እንዴት ይመለከተኝ እንደነበር አጠቃላይ ሁኔታውን መቼም ቢሆን የማልረሳው ነው።

**ግዮን፦ እጅህ ከተያዘ ወዲህ የደረሰብህ ለየት ያለ ችግር ነበር?**

አንዱዓለም፦ አዎ ነበር። ለምሣሌ ያህል እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን ሊያሥሩኝ ይችላሉ እንጂ ለደቂቃዎች ያህል «በሽብር ወንጀል» ይከሱኛል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ነገር ግን በታሠርኩ በሁለተኛው ቀን አራዳ ፍ/ቤት አቅርበውኝ ሲያበቁ «በሽብር ተግባር የሚፈለግ ነውና ጊዜ ቀጠሮ ይሰጠኝ...» ማለታቸውን ስሰማ በጣም ተገረምኩ። ሌላው በባንክ ቡኬ ላይ ምንም ዓይነት ገንዘብ እንደሌለ ተመልክተው «የደሀ ልጅ!» ብለው ሲሰድቡኝ ደግሞ ለጊዜው በጣም ተሰማኝ። ያም ሆኖ ገባቸውም አልገባቸው «አፄ ቴዎድሮስም ሆኔ ራስ አሉላ አባ ነጋ ድሆች ነበሩ፤ እነሱ ናቸው የዛሬዋን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ያደረጓት። እኔ በዚህ አባባላችሁ የምሸማቀቅ ሰው አይለሁም » የሚል መልስ ሰጠኋቸውና ራሴን አረጋጋሁ። እነሱ ግን አስራርተውኝ ቃሌን ለመቀበል፣ ምክንያት እየፈለጉ ሊደበድቡኝ ሞክረዋል። እናቴንም ጸያፍ ስድብ ሰድበዋታል። በዚህም የተነሳ መርማሪዬ የነበረውን ፖሊስ «ይቅርታ የማትጠይቀኝ ከሆነ ቃሌን ልሰጥህ ፈቃደኛ አይደለሁም» እስከማለት ደርሼአለሁ።

**ግዮን፦ በማዕከላዊ ለምን ያህል ጊዜ ቆየህ? የቃሊቲ የእሥራት ጊዜህስ እንደምን አለፈ?**

አንዱዓለም፦ በማዕከላዊ ምርመራ የቆየሁት ለሁለት ወራት ነው። ቃሊቲ እደወረድኩም የሚባለውን ያህል ድቅድቅ ባይሆንም «ጨለማ» በሚባለው ቤት ውስጥ ነበር ያስገቡኝ። ቤቱ ከናካቴው የብርሃን ጭላንጭል የማይታይበት አይደለም። ግን የታሣሪውን ነፍስ የሚያስጨንቅ ድባብ ነበረው። በሀገራችን «አሉ የሚባሉ ወንጀለኞች» በልዩነት የሚታሠሩበት ቦታ ነው። በማረሚያ ቤቱ የአሠራር ደንብ መሠረት አንድ ታሣሪ እዚያ የሚገባው፤ በእሥር ላይ እያለ ከባድ ጥፋት መፈፀሙ ሲረጋገጥና በቆይታው እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ ሲታወቅ ብቻ ነበር። እኔን ግን ገና ከበር እንደተቀበሉኝ ወደዛው ወሰዱኝ። እዛ ጨለማ ቤት ሲያስገቡኝ በውስጥ አቶ በቀለ ገርባ ስለነበር ደስታ ተሰማኝ። ከበቀለም ጋር ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ከቆየሁ በኋላ እሱን ወደ ዝዋይ ሲወስዱት በደረቅ ወንጀል ተጠያቂ ከነበሩ አራት እሥረኞች ጋር ቆየሁ። በአጠቃላይ ለሁለት ዓመት ተኩል በዚያ ሁኔታ ቆይቼ፤ ቀሪዎቹን አራት የእሥር ዓመታት ወዳሳለፍኩበትና «ኂይት ሐውስ» ወደተባለው ቦታ ተወሰድኩ። ከእስክንድር ጋር የተገናኘሁትም በዚያ ነበር። ቀጣዮቹን ስምንት ወራት ከእሱ፣ በግንቦት ሰባት ከተከሰሱት ከመላኩ ተፈራ፣ ከኮሎኔል ጌታቸው

ብርሌና ‹‹ሙስና ፈጽመዋል...›› ከተባሉት ከአቶ መላኩ ፈንታ ጋር ቆየሁ። እንደገና ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ተይዞ ወደ ቃሊቲ ሲመጣ ከነበርኩበት ቦታ ወጥቼ ሃያ ሜትር ርቀት ላይ ከተሠራ አንድ ክፍል ውስጥ ከእስክንድር ለይተው አስቀመጡኝ።

**ግዮን፡- በቃሊቲ ቆይታህ አቶ አንዳርጋቸውን ጽጌን አግኝተኸው ነበር?**

አንዱዓለም፡- አንዳርጋቸውን አይቸዋለሁ። መጀመሪያ እንዳመጡት እኔ ከምገኝበት ክፍል አጠገብ ወደ ነበረው ቤት ነበር ያስገቡት። የእኔ ክፍል እሱ ካለበት ክፍል ጋር አንድ ግርግዳ ይጋራል። እንደማስታውሰው የመጣው ኦባማ አዲስ አበባ በገባበት ሰሞን ነው። እና አንድ ቀን ጆሮዬን ግርግዳው ላይ ለግቼ በወዲያኛው ቤት ያለውን ድምፅ ስከታተል አንድ ሰው ስለ እንግሊዝ ሀገር ሁኔታ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሲያወራ ሰማሁ። ምናልባት እሱ ይሆን ብዬ ስለገመትኩ፤ ግድግዳውን ደጋግሜ በመምታት ‹‹ማን ነህ በዚያ ያለኸው?›› ብዬ ስጠይቅ ‹‹አንዳርጋቸው ነኝ! አንተስ ማን ነህ ?›› የሚል ምላሽ አገኘሁ። ማንነቴን ስገልጽለት ወዲያውኑ አወቀኝ። ከዚያን ቀን ወዲህ በእኛ ክፍል የነበረውን ቴሌቪዥን እንዲሰማው ብዬ ድምፁን ከፍ አደርገው ነበር። በዚያ ክፍል እስከቆየበት ጊዜ ድረስም ድምፃችንን ከፍ እያደረግን ሰላምታ እንለዋወጥ ነበር። ለደህንነት ጥበቃ እንዲያመች ተደርጎ ወደተሠራው ክፍል ከተዛወረ በኋላ ደግሞ፤ ዘመድ ለመጠየቅም ይሁን በሌላ በማላውቀው ምክንያት ሲወጣና ሲገባ በቀዳዳ ስመለከተው ቆይቻለሁ። እሱም አንድ ቀን ምግብ ተቀብዬ ስመለስ ሊመለከተኝ ችሏል። በተረፈ በአብዛኛው በቀዳዳ እያጮለቅኩ የምመለከተው እኔ ነበርኩ። ይህም ተፈትቼ ከወህኒ እስከወጣሁበት እስከ የካቲት 7 ቀን 2010 የቀጠለ ነበር። እስከዚያም ቀን ድረስ ደህና መሆኑን አውቃለሁ።

**ግዮን፡- ፍርድ ቤት የዕድሜ ይፍታህ ውሳኔ ሲያስተላልፍብህ ምን ተሰማህ**

አንዱዓለም፡- አስቀድሞ ‹‹ይሙት በቃ›› የሚለውን ውሳኔ ያሳልፉብኛል የሚል ግምት ስለነበረኝ ባለቤቴን ሁሉ ሊሆን ስለሚችለው ነገር እንድትዘጋጅ ነግሬአታለሁ። እንደሚታወቀው በቅንጅት ጊዜ ዕድሜ ይፍታህ የተፈረደብኝ ሰው ነበርኩና ብዙም የተለመደ ባይሆን ከዚያ ተነስተው በመቀጣጫ ሊፈርዱብኝ የሚችሉት ሞት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሼአለሁ። ማዕከላዊ እያለሁ ጀምሮ የማስበው ያው ሊገድሉኝ ይችላሉ የሚለውን ብቻ ነበር። ከዚህም ሐሣቤ በመነሳት እንዴት ወደ ሞት አደባባይ ያለ አንዳች ፍርሃት ልራመድ እንደምችል ራሴን እያለማመድኩ ቆይቻለሁ። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የዕድሜ ይፍታ እሥራት ውሳኔ ያስተላለፈብኝ ዕለት ምንም ዓይነት ስሜት አልተሰማኝም።

**ግዮን፡- ዛሬ ላይ ሆነህ ሞት የተመኘህበትን ጊዜ ስታስበው፤ የሚታይህ የተለየ ነገር ይኖራል?**

አንዱዓለም፡- የለም። ሞትን የተመኘሁት በሰላማዊ ትግል በሀገሬ ለውጥ ለማምጣት ከነበረኝ ህልም፣ ዓላማና ዕምነት አንፃር ነው። ከመነሻው ወንድሙን ከማፍቀር በቀር ከቶውንም ለመግደል ባለማሰብ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ወደ ፖለቲካ የሚገባ ሰው፤ ተስፋ የቆረጠ ሳይሆን ተስፋ ያለው ነው። የዚህች ሀገር ችግር የሚቀረፈው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነባራዊና ወቅታዊ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚያገኘው በሰላማዊ ትግል ነው ብዬ ስል፤ ትግሉ የሚያስከፍለውን የሕይወት መስዋዕትነት ዋጋ ራሴው ለመክፈል ዝግጁ ነኝ ማለቴ ነው። ስለዚህ እነሱ የተለያየ ባጅ ቢለጥፉልኝም ሰላማዊ ትግልን የኃይማኖት ያህል አምንበታለሁ። እኔ ስታሠር ሰላማዊው ትግል ሊቋረጥ እንደማይችልም ተስፋ አድርጌአለሁ። ብሞትም እንደዛው። ነገር ግን የዞን ዘጠኝ ልጆች ወደ ወህኒ ሊጠይቁኝ በመጡበት አጋጣሚ እንዳስተዋልኩት፤ በዚያ ፍጥነት እኛ ምትክ አግኝተን የጀመርነው ሰላማዊ ትግል በሂደቱ ይቀጥላል የሚል ግምት ግን አልነበረኝም። ለማንኛውም በሕይወቴ በጣም የተደሰትኩበት ቀን ቢኖር፤ እነዛ በአካል የማያውቁኝ የዞን ዘጠኝ በሳልና በራስ የመተማመን ስሜት የሚታይባቸው ወጣቶች አሥራ ሁለት ሆነው መጥተው በጠየቁኝ ዕለት ነው። በዚያን ቀን የማልመውን ለውጥ ፈላጊ ትውልድ ምስል ነፀብራቅ በእነሱ ገጽ ላይ በመመልከቴ ኩራት ተሰምቶኛል። ለእነሱም ‹‹እኔ የታገልኩት እናንተን እያሰብኩ ነው›› ብዬ ነግሬአቸዋለሁ። ስለዚህም ነው እኔ ሞትኩም ኖርኩም ያለምኩትና አንግቤ የተነሳሁት የሰላማዊ ትግል ዓላማ ግቡን እንደሚመታ፣ ለፍሬ እንደሚበቃ፣ ኢትዮጵያ የነፃነት ሀገር እንደምትሆን አምን የነበረው።

**ግዮን፡- የዕድሜ ይፍታህ እሥራት ውሳኔ ሲተላለፍብህ በችሎት የተናገርከው ምን ነበር?**

አንዱዓለም፡- ‹‹በኢትዮጵያ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ባለፉት ሃምሣ ዓመታት ብዙዎች መስዋዕትነት ከፍለዋል። እኔም አቅሜ በፈቀደው የራሴን አስተዋጽዖ ለማበርከት ጥሬአለሁ። ግን አሁን የውሸት ክስ ተመስርቶብኝ፣ የውሸት ፍርድ ተላልፎብኛል። ይሄንን ፍርድ በንፁህ ህሊናዬ በመቀበሌም ፍፁም የሆነ ደስታና ሰላም ተሰምቶኛል›› የሚል ዓይነት ይዘት ያለው ንግግር ነው የተናገርኩት።

**ግዮን፡- ስለ ይቅርታ ጉዳይ ምን ትላለህ?**

አንዱዓለም፡- በበኩሌ ለመታሠር ብቻ ሳይሆን ስታሠር የይቅርታ ላለመጠየቅ የወሰንኩት ገና ከመታሠሬ በፊት ነው። በእኔ ዕምነት አንደኛ ሰው አጥፍቶ ይቅርታ መጠየቁ ትልቅነት ነው። ከዚህ አኳያ ይቅርታ የሚሰጥም፣ የሚቀበልም ብፁዕ ነው። ተግባሩም የትልቅነት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው

...አንድ ቀን ጆሮዬን ግርግዳው ላይ ለግቼ በወዲያኛው ቤት ያለውን ድምፅ ስከታተል አንድ ሰው ስለ እንግሊዝ ሀገር ሁኔታ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሲያወራ ሰማሁ። ምናልባት እሱ ይሆን ብዬ ስለገመትኩ፤ ግድግዳውን ደጋግሜ በመምታት «ማን ነህ በዚያ ያለኸው?» ብዬ ስጠይቅ «አንዳርጋቸው ነኝ! አንተስ ማን ነህ ?» የሚል ምላሽ አገኘሁ...

ባልሠራው ወንጀል ወይም ባልፈፀመው ጥፋት ስድስት ዓመት ተኩል ያህል በውሸት ታሥሮ፣ ዘመኑን ተቀምቶ፣ አንገቱ ላይ ተቆሞበትና እንዲጨነቅ ተደርጎ ከሳሹ ወይም ጉልበተኛው ወገን የዋሸውን ውሸት እውነት ነው ብሎ ፈርሞ መውጣቱ ተገቢ ነው ብዬ አላምንም። ለምን? ውሸት ስለሆነ። ውሸት በመሆኑም እነሱን ፈርቼ ፈጣሪዬን ማሳዘን አልፈለኩም። ያለው ሁለት ኃይል ፈጣሪና እነሱ ናቸው። ፈጣሪ እንድዋሽ አይፈልግም። በማንኛውም ጊዜና ቦታ እውነቱን ይዤ እንድሞትና ሊያወጣኝ እንደሚችልም ነው የሚነግረኝ። እነሱ ደግሞ ‹‹ይቅርታ ካልጠየቅ እንገልሃልን›› ባዮች ናቸው። ሰው ከፈጣሪና ከእነሱ ማንን ያስበልጣል? የሚሞተውን የሰው ልጅ ፈርቼ ፈጣሪዬን ልዋሸው? የማይሆን ነው። ለዚያውም ስድስት ዓመት ተኩል ያህል ዕድሜ የማስቢያ ግዜ እያለኝ፤ እነሱ ከሚያሰቃዩኝ ፈጣሪዬን ልዋሸው የሚል መደምደሚያ ላይ ልደርስ አልችልም። እንዴ?! በ1997 ምርጫ ምክንያት በታሠርኩበት ግዜ ያውም ብዙ ስሚገት ቆይቼ የፈረምኩበት ጉዳይ እራሱ ይቆጨኛል። ያኔ በቡድን ደረጃ ብንጠነክር ኖሮ ጥሩ ለውጥ እናመጣ ነበር ብዬ ነው የማምነው። ይህኛው ግን የመጀመሪያ ምክንያቴ እግዚአብሔር ነው። ሁለተኛው የይቅርታ ባሕላችንን ማቆሸሽ ነው ብዬ ማሰቤ ነው። ይቅርታ ከሆነ ይቅርታውን መጠየቅ የሚኖርበት በትክክል ያጠፋ ሰው ነው። የተበደለ ሰው ከሆነ ደግሞ ከልቡ በንፅህና ይቅር ማለት ትልቅ ባሕላችን ነው። አሁን ግን አንገትህ ላይ ቆሞ ስለረገጠህና ስለፈራህ ብቻ፤ በማታምንበት ሁኔታ ይቅርታ ማለት ተገቢ ነው ብዬ አላምንም። ለልጆቻችንስ ምን ዓይነት መልዕክት ነው የምናስተላልፈው? ‹‹ውሸታም አባቶች›› የሚለውን ካልሆነ በቀር።

**ግዮን፡- ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር መፍትኄ ምን ሊሆን ይችላል?**

አንዱዓለም፡- ሁላችንም ሊያስማማን እንደሚችለው፤ ካለን የልዩነት አጀንዳ ይልቅ የሚያስማማን የሚበልጥ ነው። በሀገራችን ዴሞክራሲ እውን የሚሆን ከሆነ በርካታው የኢትዮጵያ ችግር በዚሁ የዴሞክራሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሊፈታ የሚችል ነው። ዋናው ነገር ግን የሕዝቡ ሉዐላዊ የሥልጣን ባለቤት መሆን ነው። ለእኔ የሚታየኝ ትልቁ የኢትዮጵያ ንጋትም እሱ ነው። ከሀውልቶቻችን ሁሉ ትልቁ ሀውልትም የዴሞክራሲ ሀውልት ነው። ከቅርሳችን ሁሉ ትልቁ ቅርስ የዴሞክራሲ ቅርስ ነው። ከባሕላችን ሁሉ ጎልቶ የሚወጣው ባሕል የዴሞክራሲያችን ባሕል ነው። እስካሁን በኢትዮጵያችን ታሪክ ውስጥ ይህን የሚያህል ታሪክ ተሠርቶ አይታወቅም።

የአክሱም ሀውልት፣ የላሊበላ ቤተክርስቲያን፣ የገዳ ዴሞክራሲ፣ የጎንደር ቤተ-መንግሥት አለ። ግን እነዚህ ሁሉ ሕዝባዊ ሉዐላዊነት ያመጣቸው አይደሉም። የግብፅ ፒራሚድ አለ። ፒራሚዱን ያነፁት ሰዎች ግን ሉዓላዊ አልነበሩም። እንደዚሁም የአክሱምን ሐውልት የሠሩም የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት አልነበሩም። የጎንደርን ቤተ-መንግሥት የሠሩ ሰዎችም የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት አይደሉም። ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲን እውን ካደረግን ግን፤በትውልድ ሂደት ውስጥ ካስገኘናቸው ድሎች ሁሉ ከዓድዋም ይሁን ልንጠቅሳቸው ከምንችላቸው ሌሎች ድሎች የሚበልጠው የዴሞክራሲ ድል ነው። የዴሞክራሲ ብርሃን ለአንዱ በርቶ ለሌላው የሚጨልም አይደለም። ብርሃንነቱ ለሁሉም ነው። በጊዜ የሚገደብም አይደለም። ለኢትዮጵያ የምመኘው ይህን ሲሆን የምታገለውም ለዚሁ ነው። ሕዝብ ሉዓላዊ የሚሆን ከሆነ አብዛኞቹን ችግሮች ራሱ መፍትኄ ያበጅላቸዋል። የጎበጡትን ጎዳናዎች ሕዝቡ ራሱ ያስተካክላቸዋል። ስለዚህ ሕዝብ ሉዓላዊ እንዲሆንና የሉዓላዊነቱም ተጠቃሚ እንዲሆን መፍቀድ ያስፈልጋል።

**ግዮን፡- በመጨረሻ የምትለው ይኖራል?**

አንዱዓለም፡- በቅድሚያ ትቢያ ላይ በወደቅኩበት ጊዜ አልተወኝምና፣ ለሰው ልጅ እንኳ በማይገባ በዚያ አስጨናቂ ሥፍራ አብሮኝ ነበርና፤ የድፍረቴ ምንጭ፣ የጽናቴ መሠረት፣ የተስፋ ሙላቴ ለሆነው እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ግን ምን ብዬ እንደማመሰግነው አላውቅም። ከሀገር ውስጥ ከከተማም ይሁን ከገጠር፣ከኢትዮጵያ ውጭ ከያለበት ሀገር በእኔ መፈታት የተሰማውን ደስታ፤ ከታላቅ ጨዋነትና ትኅትና ጋር የገለጸልኝ ሰው እጅግ በጣም ብዙ ነው። ስለዚህ በማልጠብቀው ሁኔታ ከጎኔ ለነበረውና ላከበረኝ ሕዝብ ምስጋናዬን የማቀርበው፤ በፊቱ መሬት ላይ ተደፍቼ ቢሆን ነው ከልቤ ደስ የሚለኝ። ይህ ሕዝብ ነፃነት፣ ፍትሕ፣ ክፍታ፣ ታላቅነት ይገባዋል። ለዚህ ሕዝብ መታሠር አይደለም መሞት መባረክ ነው። ክብር ነው። ከዚህ ውጭ ባለቤቴ ሰላም ከሁሉም በላይ ዋጋ የከፈለችና ለእኔ ሞራል መጠበቅ ስትል በወጣትነቷ መበለት የሆነች... በመሆኑ፤ ይህን ተግባሯን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት እንደከፈለችው መስዋዕትነት እቆጥረዋለሁና የትዳር አጋሬ ከመሆኗ ባሻገር ሊኖረኝ የሚችለውን ለየት ያለ አክብሮትና ምስጋናዬን ላቀርብላት እወዳለሁ። እግዚአብሔር ዋጋዋን ይክፈላት።

# <<አደባባይ የወጣነው ሰው እንዲሞት ፈልገን አይደለም>>

## ወይዘሪት ንግሥት ይርጋ

- የታሠረችው መስከረም 5 ቀን 2009 ዓ.ም
- ክስ ተመሥርቶባት ፍ/ቤት የቀረበችው ጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም
- የክስ ቻርጅ «የአርበኞች ግንቦት ሰባት አባል...»
- ከእሥር የተፈታችው የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም
- ታሥራ የነበረው በማዕከላዊ ምርመራና በቃሊቲ፡፡
- በእሥር ላይ ሳለች የምትናፍቀው አክስቷን፡፡



‹‹ንግሥት አማራ›› በመባሏ እና ‹‹አማራ አሸባሪ አይደለም›› በማለቷ የምትታወቀው ንግሥት ይርጋ ተፈራ፤ የተወለደችው በሰሜን ጎንደር ‹‹ሳንጃ›› ተብሎ በሚታወቀው ሥፍራ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሲነሳ ምንግዜም የሚታሰባት መይሳው ካሣ፤አፄ ቴዎድሮስ ነው፡፡ እሱ ለእሷ የኢትዮጵያ አንድነት አባት ነው፡፡ በታሪኩ የምትኮራበት፣ የምታምንበት ባለራዕይ ሰው፡፡ ወጣቷ ንግሥት ‹‹የኢትዮጵያ ብሔሮች የማንነት ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የተፈጠርንና የምንኖር፤ በወንድማማችና በእህትማማችነት ተባብረን… ብንቀጥል፣ ትልቂቱን ኢትዮጵያን ፍቅር የሰፈነበት ቤተሰብ አድርግን ብንገነባት፣ ብንከባከባትና ብንጠብቃት ደስታዬ ሙሉዕ ይሆናል›› ትላለች፡፡ ‹‹የሕዝባዊ ትግሉና የፖለቲካው ዓላማ ሁሉ ግብ፤ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ብልጽግና መሆን አለበት፡፡ ጎሠኝነት፣ ጎጠኝነት… ይጎዳናል፡፡ በሥልጣን ላይ የሚገኙትም ይሁኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መሥርተው ‹እንታገላለን› የሚሉት ወገኖች ለጋራ ሀገር ጥቅም የሚሠሩበትን ሁኔታዎች ያመቻቹ፡፡ የሚሞቱት ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣ አባት እናቶቻችን፣ሕፃናት ሊያሳዝኑን ይገባል፡፡ አዛውንቶች፣ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ብዙ መሥራት የሚችሉ ታዳጊዎችና አፍላ ወጣቶች ዕድሜያቸውን በእሥር ሲያሳልፉ መመልከት ቅስም የሚሰብር ነው! ይህ ሁሉ ከመለያየትና ካለመግባባት የመጣ በመሆኑ መለያየቱንና መናቆሩን ትተን፣ አንድነታችንን አደራጅተንና አጠናክረን መቀጠል ይኖረብናል፡፡ ለዚህም ዓላማ ስኬት አቅሜ የፈቀደውን ሰላማዊ ትግል ከማድረግ አልቆጠብም›› የምትለው ንግሥት፤ ከመጽሔታችን ጋር ያደረገችው ቆይታ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

### ግዮን፡- በአንቺ ዕምነት የታሠርሽበት ምክንያት ምንድን ነው?

ንግሥት፡- እሥር ቤት የገባሁበት ምክንያት በአንድ አጋጣሚ በተፈጠረ ችግር ነው ብለው የተሻለ ነው፡፡ በጎንደር ከተማ በኢትዮጵያ ደረጃ የታወቀ፣ ዓለም አቀፉም ማኅበረሰብ የሰማው አንድ ትልቅ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተካሂዶ ነበር፡፡ በዚያ እንቀስቃሴ እኔም ሆንኩ ሌሎች ወጣቶች አደባባይ በወጣንበት ሰዓት የአማራ ሕዝብ መብቱን ስለጠየቀ ‹‹አሸባሪ ነው›› ሊባል አይገባም፡፡ ‹‹አማራ አሸባሪ አይደለም! አማራነት ወንጀል አይደለም!…›› የሚሉ መፈክሮችን አሰምተን ነበር፡፡ ምናልባትም ለእሥር የተዳረኩበት ምክንያት ያን የመሰለውን መፈክር አሰምታለች፣ የሰውን ስሜት የሚቀሰቅስና በአመጽ ተግባር እንዲሳተፍ ሊያደርግ የሚችል መልዕክት ያዘለ ቲሸርት ለብሳ ጎዳና ላይ ወጥታለች የሚለው ይመስለኛል፡፡

### ግዮን፡- ፍርድ ቤት በቀረብሽበት ሰዓት የተመሠረተብሽ ክስ ምን የሚል ነበር?

ንግሥት፡- በቅድሚያ ማዕከላዊ እያለሁ አራዳ ምድብ ችሎት ስቀርብ የተነበበልኝ ‹‹በሽብር ወንጀል ተሳታፊ ሆና ተገኝታለች፣የተለያዩ በራሪ ወረቀቶችን ታዘጋጃለች፣ ታሠራጫለች፣ ወጣቶችን እየመለመለች ወደ ግንቦት ሰባት አሸባሪ ቡድን ትልካለች›› የሚል ነበር፡፡ ለዚያ ክስ ምስክርና ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው፤ እንደገና ታኅሣሥ 28 ቀን 2009 ዓ.ም ሌላ ክስ ተዘጋጅቶ ጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም በከፍተኛው ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ቀረብኩ፡፡ ሁለተኛው ክስም ‹‹በከፍተኛ ንብረት ውድመት፣ አመፅና ሁከት በመፍጠር ተግባር ተሠማርታ ተገኝታለች›› የሚል ነው፡፡

### ግዮን፡- መቼ እና የት አካባቢ ነው የተያዝሽው?

ንግሥት፡- መስከረም 5 ቀን 2009 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ወደ 11 ሰዓት አቅራቢያ ከጎንደር ከተማ ወጣ ብሎ ካለ ሥፍራ ወደ ትውልድ አካባቢዬ ሳንጃ በሞተር ሳይክል እየሄደኩ በነበረበት ሰዓት ነው፡፡ ልክ ወደ ሳንጃ ልንቃረብ ስንል መከላከያ መንገድ ዘግቶ ጠበቀኝ፡፡ ከዚያም ይዘውኝ ወደ ጎንደር ከተማ ተመለሱ፡፡ ቀጥሎ ምን እንዴት እንደሆነ ማስታወስ በማልችልበት ሁኔታ አዲስ አበባ ማዕከላዊ ውስጥ ራሴን አገኘሁት፡፡ መስከረም 6 ቀን ከሰዓት በኋላም አራዳ ፍ/ቤት አቀረቡኝ፡፡

### ግዮን፡- የማዕከላዊ ቆይታሽ ምን ይመስል ነበር?

ንግሥት፡- ኦ!… የማዕከላዊ ቆይታዬ በምድር ሲዖል ውስጥ የመኖር ያህል ነው፡፡ በእኔ አስተያየት ያ ሥፍራ ፖሊስ ትክክለኛውን ሙያዊ ምርመራ የሚያካሂድበት ቦታ አይደለም፡፡ በቃ ሲዖል ነው! ለአራት ወራት የቆየሁበትን ያን የሰቀቀንና የጭንቅ ቦታ ከዚህ በተሻለ ቃላት ልገልጸው አልችልም፡፡ በማዕከላዊ ወንዶች ሌሊት እየተወሰዱ መርመራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ሴቶችን በተመለከተ ግን ምናልባት የሌሊቱ ምርመራ የተጀመረው በእኔ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በእኔ ላይ ከባድ ምርመራ በሌሊት ሲካሄድብኝ፤በዚያ የነበሩት ሌሎች ሴት እሥረኞች ተረብሸዋል፡ ፡ ታመዋል፡፡ ራሳቸውን መቆጣጠር ባለመቻላቸው፤የሚያስቀምጣቸው፣ የሚያስመልሳቸው ነበሩ፡፡ እና የማያልፍ ነገር የለምና እነዛ ከባድ የነበሩ ጊዜያቶች አለፉ፡፡

### ግዮን፡- ስለ ቃሊቲ ምን የምትይው አለ?

ንግሥት፡- ቃሊቲ ከማዕከላዊ የሚሻል ሥፍራ ነው፡፡ ቢያንስ በሰላም ተኝቶ ማደር ይቻልበታል፡፡ ሌሊት እጠራለሁ ብለው የሚሰጉበት የእሥር ቦታ አይደለም፡፡ ሌቱ ሲነጋም ቤተሰብ መጥቶ ይጠይቀኝ ይሆናል የሚለውን እያሰቡ በተስፋ ቀጣዮቹን ጊዜያት ለመቀበል ዝግጁ የሚሆኑበት የእሥረኞች ማዕከል ነው፡፡

### ግዮን፡- ቤተሰቦችሽ መታሠርሽን ያወቁት መቼ እና እንዴት ነው?

ንግሥት፡- ወዲያው ነው፡፡ ሳልያዝ በፊት መከላከያዎች እኔን ለማግኘት ወደመኖሪያ ቤታችን መጥተው ነበር፡፡ የመጡት እኔን የማያገኙኝ ከሆነ ‹‹እናቷንም ቢሆን ይዛችሁ እንድትመጡ›› የሚል ትዕዛዝ ተቀብለው ነው፡፡ እቤት ሲደርሱ ታማ የሰነበተችው እናቴ አልጋ ላይ ተኝታ ያገኟታል፡፡ ይህንኑ ሁኔታ ሪፖርት ሲያደርጉ ‹‹ከእነአልጋዋም ቢሆን ይዛችኋት ኑ!.›› ይባላሉ፡፡ በዚያን ጊዜ ‹‹ይዘን መሄድ አለብን፣አይ የለብንም›› በሚል በመካከላቸው አለመግባባት በመፈጠሩ፤ እናቴን ሳይወስዷት ቀሩ፡፡ ያም ሆኖ ለጊዜውም ቢሆን በእኔ ምክንያት የምወዳት እህቴን አሥረዋት ከቆዩ በኋላ በተያዝኩ ማግስት ፈተዋታል፡፡

### ግዮን፡- በምርመራው ጊዜ እንድታምኚላቸው የሚፈልጉት ምን ነበር?

ንግሥት፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀርቡልኝ

ነበር። ለምሣሌ ‹‹አንቺ የምታውቂያቸው እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር የጦር መሣሪያ አለ። እነ እገሌ የሚባሉትን አሸባሪዎች ታውቂያቸዋለሽ። የትስ ነው የምታውቂያቸው? ከሀገር ውጭ ከሚገኙትና እነ እከሌ ከሚባሉ ሰዎችም ጋር ግንኙነት አለሽ›› እያሉና የማላውቀውን ነገር እንደማውቅ አድርገው ሊያውጣጡኝ ሞክረዋል። እኔም ‹‹የምትሏቸውን ሰዎች ስማቸው ሲጠራ እንጂ በአካል አላውቃቸውም። ከእነሱም ጋር የተለየ ግንኙነት የለኝም›› በማለት መልሼላቸዋለሁ። ‹‹ይህን ይህን ዕኮ ብታምኚ ነገሩ ይቀልልሽ ነበር›› ሲሉኝም፤ እራሴን ለማዳን ብዬ ያልሆነ ነገር ውስጥ መግባት ስላልፈለኩ፤በሐሣባቸው አልተስማማሁም።

**ግዮን፡- ከኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ ጋር ግንኙነት ነበረሽ?**

ንግሥት፡- አልነበረኝም። የነበርኩት በጎንደር ከተማ ተስተውሎ የነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄ እስኪረጋጋ የሚኖሩትን ጥያቄዎች፤ ወደ መንግሥት አካላት ሄዶ በመፍትኄው ሐሣብ ላይ ለመነጋገር እንዲችል ከሕዝቡ ውክልና በተሰጠው ኮሚቴ ውስጥ ነው።

**ግዮን፡- ኮሚቴው እንዴት ተቋቋመ? ቀጥሎስ ምን ተፈጠረ?**

ንግሥት፡- ኮሚቴው የተቋቋመው ‹‹ሕዝቡ ጥያቄዬ ይመለስልኝ እያለ ሁልጊዜ ሰልፍ ከሚወጣ፣ በዚያም የተነሳ ነገሮች ተካረው ሀገሪቱ ላይ አንድ ችግር ከሚፈጠር፤ ጥያቄውን ለሚመለከተው አካል የሚያቀርብለት አካል ያስፈልገዋል›› በሚል ቀና መንፈስ ነበር። ከመቋቋሙም በፊት ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም ‹‹የተፈጠረው ችግር በሚፈታበት ነጥቦች ዙሪያ የበላይ አካሎችን እንዴት እናነጋግራቸው›› በሚል ርዕስ በተዘጋጀው ስብሰባ ተሳታፊ ነበርኩ። በስብሰባውም ‹‹ኮሚቴ ይደራጅ፣ ደህና የመናገርና የማሳመን ችሎታ ያላቸው 10 ወይም 15 ሰዎች ይመረጡ›› ተባለና ከ14 ወንዶች በተጨማሪ እኔ አንድ ብቸኛ ሴት የኮሚቴው አባል ሆኜ ተመረጥኩ። ያ ምርጫ የተደረገበት ስብሰባ ሳይቋጭም ተደወለልኝና ማስጠንቀቂያ ተሰጠኝ። ‹‹ስብሰባ ላይ ነው ያለሽው። የኮሚቴ አባልም ሆነሻል›› ሲሉኝ ‹‹አዎ ተመርጫለሁ። ግን መመረጤ ምንድን ነው ችግሩ?.›› አልኳቸው።

እነሱም ‹‹አርፈሽ ብትቀመጪ ይሻልሻል!.›› አሉኝ። እንደዚያ ስባል ነገሩን አላከበድኩትም ነበር። ግን ደግሞ ከስብሰባው ወጥቼ ወደቤቴ በመመለስ ላይ እንዳለሁ ሌላ ስልክ ከቤተሰቤ ተደውሎ ‹‹በስብሰባ ተሳትፈሻል እንዴ?!.›› ተባልኩ። ‹‹አዎ›› ስል ‹‹ለምን?! እንዴት የኮሚቴ አባል ሆነሽ ትመረጫለሽ?!›› እያሉ በመመረጤ ደስተኛ አለመሆናቸውን ገልጹልኝ። ትንሽ ጭቅጭቅም ተፈጠረ። ለቤተሰቦቼም ‹‹ሰላማዊ ጥያቄ ማቅረብ ወንጀል መስሎ አልታየኝም። ስለዚህ ተመርጬአለሁ። ያም ሆኖ ቅር ካላችሁና የሚደብራችሁ ከሆነ ልተወው እችላለሁ›› የሚል መልስ ሰጠኋቸው።

በዚያ ሁኔታ ላይ እያለን፤ አንድ ለቤተሰቦቼ ዘመድ የሆኑ የጓደኛዬ አባት ሞተው ለቀብር ወደ ሳንጃ ሄድኩ። በዚያም ሆኜ ጎንደር ልመለስ በዝግጅት ላይ እያለሁ ስልክ ተደውሎ ‹‹ሳንጃ ነው ያለሽው?›› ተባልኩ። ‹‹አዎ ሳንጃ ነኝ...›› ስል ‹‹ለምንድን ነው ወደዚያ የሄድሽው?›› የሚል ጥያቄ ቀረበልኝ። የሚደውሉልኝ በማኅበራዊ ሕይወት የማውቃቸው ግን ከጎንደር ባለሥልጣናትና የጸጥታ መ/ቤት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ነበሩ። ‹‹እንዴት ሳንጃ አልሄድም?! ተወልጄ ያደኩበት ሥፍራ ዕኮ ነው። ከጎንደር 60 ኪሎ ሜትር የማይርቅ ቦታ የመሄድ መብት የለኝም ወይ?›› ብዬ ስል ‹‹አይ... የሄድሽው ለሌላ ሥራ ነው›› አሉ። እንዲያም ሆኖ ወደ ጎንደር ተመለስኩ። እንደተመለስኩም የምተዳደርበትን የባልትና ሥራ መሥራት ቀጠልኩ። ግን ነገሩ ከንክኖኝ ስለነበር ወደሚከታተሉኝ በመደወል ‹‹ሥራውንም ላቁመው እንዴ?›› የሚል ጥያቄ አቀረብኩ። እነሱም ‹‹ወደ ሳንጃ የሄድሽው ለሌላ ሥራ መሆኑን አውቀናል›› አሉኝ መልሰው። ‹‹አይ የሄድኩት ለሌላ ጉዳይ አይደለም። አሁን ተመልሼያለሁ። ለማንኛውም የምትፈልጉኝ ከሆነ ቢሮ ድረስ መምጣት እችላለሁ›› ስላቸው ‹‹ሥራሽን ሥሪ›› አሉኝ። በዚያም መሠረት እስከ ጳጉሜ 3 ቀን 2008 ሥራዬን ሥሠራ ቆየሁ። በማግስቱ ጳጉሜ 4 ቀን ቤታችን በመከላከያ ሠራዊት ተከቦ አደረ። የቤታችንን ተከቦ ማደር የተመለከቱ የታክሲ ሾፌሮችም ደውለውልኝ ‹‹ኧረ ቤታችሁ ተከቧል!›› አሉኝ። ጥፋተኛ ነኝ ብዬ ስለማላምን የቤታችንን መከበብ በሰማሁበት ጊዜ ድንጋጤ አልተሰማኝም። አሁንም ደግሜ የምናገረው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን የምታገል መሆኔን ነው። ‹‹አማራነት ወንጀል አይደለም›› ነው የምለው። ዛሬ ታሥሬ በተፈታሁበት ሰዓትም የማሰማው ድምፅ ይህንኑ ነው። የማቀርበው ጥያቄም ዴሞክራሲ ይስፈን የሚል ነው።

**ግዮን፡- በቃሊቲ ቆይታሽ የገጠመሽን የማይረሳ ጉዳይ ብትነግሪን?**

ንግሥት፡- በታሠርኩ በስምንተኛ ወሬ አንድ እግሩን ታማሚ የሆነ ትልቅ ወንድሜ ከጎንደር ሊጠይቀኝ መጣ። በወቅቱ ሊጠይቀን የሚችለው እኛ ያስመዘገብነው ከአሥር የማይበልጥ ሰው ብቻ በመሆኑ ከጎንደር ድረስ የመጣውን ወንድሜን ‹‹ልታያት አትችልም›› ብለው የመለሱት መሆኑን፤ እንዲጠይቁኝ ካስመዘገብኳቸው ዘመዶቼ መሀል የሆነው የአጎቴ ልጅ በሱፍቃድ ሰጠኝ ነገረኝ። እኔም ‹‹በቃ ነገ ሰኞ እንዲመጣ ንገርልኝ። ለማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ጉዳዩን አሳውቄ እንዲገባ አደርጋለሁ›› አልኩና ሸኘሁት። የማረሚያ ቤቱን ኃላፊዎች ተማጽኜም ወንድሜ እንዲጠይቀኝ አስፈቀድኩ። በተፈቀደልኝ መሠረት ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ ወንድሜን መጠበቅ ጀመርኩ። እሱን ለማየት ብቻ ሳይሆን የእናቴንም የደኅንነት ዜና ከአንደበቱ ለመስማት ጓጓሁ። ግዜው ደርሶ

**‹‹ነይ ውጪ! የት ነው ያለሽው?! ወንድ ከሆንሽ ወጥተሽ አናግሪኝ! ሰው በልቼ አይደለም እዚህ የመጣሁት! ወንጀለኛ አይደለሁም! እኔን ባልፈጸምኩት ነገር የሰው ነፍስ በአረመኔነት እንዳጠፋ ነው የምታዩኝ! ለምድን ነው?! ነይ ውጪና አናግሪኝ›› እያልኩ ጮኹኩ...**

ከመጠየቂያው ቦታ ስሄድ ወንድሜ የለም። ያገኘሁት ያንኑ የአጎቴን ልጅ ነበር። የት አለ ወንድሜ? ስለው መከልከሉን ይነግረኛል። እዚያው በነበረችው የፖሊሶች ኃላፊ ላይ ‹‹ተፈቅዶልኝ የለም! ለምንድን ነው የሚከለከለው?!›› ብዬ አንባረቅኩባት። ‹‹ትዕግስት ይኑርሽ መግባቱ አይቀርም›› ብትለኝም ልሰማት አልቻልኩም። ሊጠይቀኝ የመጣውን የአጎቴን ልጅ ‹‹ሁለተኛ እኔን ብለህ እንዳትመጣ!›› ብዬው፤ አጃቢዎቼን ሁሉ ከምንም ሳልቆጥር የመጣልኝን ምግብ ወዲያ ጥዬ ፍቃድ ተሰጥቶሻል ወዳለችኝ ኃላፊ ቢሮ ሩጫ ጀመርኩ። ያዟት! ቢባል፣ መሣሪያ አውጥተው ሊያሥፈራሩኝ ቢሞክሩ ማን ሊያቆመኝ። ንዴትና ብስጭት እየነዳኝ ነበር። ኃላፊዋ ቢሮ መግቢያ ላይ ስደርስ መሣሪያ የያዙ ጠባቂዎች ቀድመው በሩን ዘግተውታል። ክፈቱልኝ! ገብቼ ላናግራት!. እያልኩ ብጮህ አልሰሙኝም። ‹‹ነይ ውጪ! የት ነው ያለሽው?! ወንድ ከሆንሽ ወጥተሽ አናግሪኝ! ሰው በልቼ አይደለም እዚህ የመጣሁት! ወንጀለኛ አይደለሁም! እኔን ባልፈጸምኩት ነገር የሰው ነፍስ በአረመኔነት እንዳጠፋ ነው የምታዩኝ! ለምድን ነው?! ነይ ውጪና አናግሪኝ›› እያልኩ ጮኹክ። ኃላፊዋ ሳትወጣ ቀረች። ፖሊሶቹም ለሦስት፣ ለአራት ተረባርበው ያዙኝ። ‹‹አርፈሽ ካልተቀመጥሽ እንደብድብሻለን›› ብለው አስጠነቀቁኝ። እኔ ግን በእልህ እየተወራጨሁና እያለቀስኩ ነበር። ትንሽ ቆይቶ አንዲት ሴት የፖሊሶች አለቃ መጣችና ዕንባዬን እየጠራረገች ‹‹ተረጋጊ። እምትፈልጊያት ጋር አቀርብሻለሁ። ግን ንግግርሽ ሥርዓት ይኑረው። ወንድምሽን ታገኚዋለሽ›› እያለች አግባባችኝ። ከዛ ወንድሜን ለማግኘት ስል ያቺን ፈቃድ የምትሰጥና የምትከለክል ፖሊስ በተረጋጋ ሁኔታ አነጋገርኳት። ስልክ ደውዬ እንዲመጣ እንድነግረውም አደረገች። እንደዛ በረበሽኩበት ቀንም ባይሆን በቀጣዩ ዕለት ወንድሜን ላገኘው ቻልኩ። እጅግ በጣም በጣም ከፍተኛ ደስታ ተሰማኝ። ያ ከሆነ በኋላ ያዋከብኳቸውን ፖሊሶች በሙሉ ይቅርታ ጠየቅኳቸው። እና በቃሊቲ ያጋጠመኝና የማይረሳኝ ነገር ቢኖር ይህ ነው።

**ግዮን፡- ወደ ፍርድ ቤት ስትመላለሺ ምን ተስፋ እያደረግሽና እየናፈቅሽ ነበር?**

ንግሥት፡- ብዙውን ጊዜ ተስፋ የማደርገውና የምናፍቀው እንደእኔው የፖለቲካ ክስ የተመሰረተባቸውን ወንድሞቼን ማየት ነው። በሩቁም ይሁን በቅርቡ እነሱን ተመልክቼ ሰላም ማለቱ ያስደስተኝ ነበር። ከጎንደር የመጡ በጣም ብዙ ልጆች ነበሩ። ጠበቃዬን ጨምሮ ጓደኞቼም፣ የሠፈሬ ልጆችም የሆኑ። በተለይ ጠበቃዬ በእኔ ምክንያት ብዙ ፍዳ ነው ያየው። ከእሷ ጋር ይህን ይህን አድርገሀል ብለው ያለአግባብ አሥረውታል። እሱን ወደ ቃሊቲ ልዛወር ስል በማዕከላዊ ግቢ ውስጥ ስመለከተው፤ መሬት ተከፍቶ ቢውጠኝ እወድ ነበር። በሕይወቴ ለረዥም ጊዜ ያለቀስኩትም በዚያን ቀን ነው። እሱ መታሠር የማይገባው ንፁህ ሰው ነው። በዚህም ይሁን በሌሎች መሰል ምክንያቶች ወደ ፍርድ ቤት የምሄደው ዳኝነት አገኛለሁ ብዬ ሳይሆን የታሠሩ ወንድሞቼን በመመልከት መንፈሴን ለማለምለም ነው። በማዕከላዊ ምርመራ የማውቃቸውና አይዞሽ በርቺ! እያሉ ሞራሌን ይገነቡ የነበሩትን ኦሮሞ ወንድሞቼንም በችሎት አካባቢ አግቼአቸው ሰላምታ አቀርብላቸዋለሁ በሚል ተስፋ ነው።

**ግዮን፡- የመፈታታችሁን ዜና እንዴት ሰማሽ? ዜናው የፈጠረብሽ ስሜትስ ምን ይመስላል?**


ንግሥት፡- በቅድሚያ የሰማሁት የኮሎኔል ደመቀ ዘውዱን መፈታት ነበር። እሱን በቴሌቪዥን እንደሰማሁ ደስታ ፈንቅሎኝ ጮኹክ። ከተቀመጥኩበት መኝታ ላይ ተነስቼ ኮሎኔሉን ያገኘሁት ያህል ቴሌቪዥኑን ላቅፈው የተሰቀለበት ቦታ ላይ ልወጣ ስል፤ ያዟት! ኧረ አውርዷት! ጸበል እርጩአት!... እያሉ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት 43 የሚሆኑ እሥረኞች ተንጫጩ። በዚያ አጋጣሚ የእኔን ስም መጠራት አድምጠው ስለነበር ‹‹አንቺም ዕኮ ትፈቻለሽ ተብሏል...›› ቢሉኝ፣ አንኳን ደስ ያለሽ እያሉ ቢያቅፉኝ ‹‹አዎ ኮሎኔል ዕኮ ተፈታ›› እያልኩ ስቅስቅ ብዬ ከማልቀስ በቀር ስለ እኔ የሚሉትን መስማት አልቻልኩም። በዚያው ቅፅበትም ይታየኝ የነበረው መሞት ሳይገባቸው የሞቱት ንፁሃን ሰዎች ነበሩ። የእነሱ መሞት የፈጠረብኝ የኀዘን ስሜትም አገረሸብኝ። ሰከን ብሎ ሰላማዊ መፍትኄ ማፈላለግ ሲቻል፤ንፁኀን ሞቱ እያልኩ አለቅስ ነበር። በተረፈ አስቀድሞም ምንም ጥፋት ሆነ ወንጀል ፈጽሜአለሁ ብዬ ስለማላስብ ‹‹ልትፈቱ ነው›› መባሉ የደስታም ይሁን የመገረም ስሜት አልፈጠረብኝም።

**ግዮን፡- በመጨረሻ የምትይው ይኖርሻል?**

ንግሥት፡- ከእሥር በመፈታቴ በአዲስ አበባ ከተማ ሰዎች ያደረጉልኝ አቀባበል እጅግ አስደስቶኛል። አኩርቶኛልም። ስለዚህ የአዲስ አበባን ሕዝብ በጣም አመሰግናለሁ። ደግሞም በመፈታቴ ብቻ ሳይሆን በመታሠሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእኔ ያለውን ፍቅርና አክብሮት ፍፁም ባልጠበቅኩት ደረጃ አሳይቶኛል። በእሥር ቤት የሚገኙና አይዞሽ ሲሉኝ የነበሩ በርካታ እህቶቼና እናቶቼም ነበሩ። በእነሱ የተመለከትኩትን የወገን ፍቅር ከእሥር ቤት ስወጣም እጥፍ ድርብ ሆኖ ተመልክቼዋለሁ። ቤተሰቦቼን፣ ወዳጅ ዘመዶቼን፣ በማንኛውም መልኩ እኔ ለማበረታታት፣ ለመደገፍና የደስታዬ ተካፋይ ለመሆን ከአጠገቤ የቆሞትን ወገኖቼን በሙሉ፤ እግዚአብሔር ውለታቸውን ይክፈላቸው።

# “የጎንደርን ሕዝብ ችግር በደንብ እጋራለሁ”

## አቶ በቀለ ገርባ



- የታሠሩት ታኅሣሥ 14 2008 ዓ.ም ነው፡፡
- የተፈቱት የካቲት  ቀን 2010 ዓ.ም
- በማዕከላዊና በቃሊቲና በቂሊንጦ የእሥር ጊዜያቸውን አሳልፈዋል፡፡
- በእሥር ላይ እያሉ አብዝተው የሚመኙት ከሕዝብ ጋር ተገናኝተው መነጋገርን ነበር፡፡

በተለያዩ ጉዳዮች ከአንድም ሁለት ጊዜ የታሠሩትን  አቶ በቀለ ገርባን አነጋግረናቸዋለል፡፡ ለእሥር ስለዳረጋቸው ምክንያት፣ ከእሥር ስለተፈቱበት ሁኔታ፣ በጎንደር አግኝተውት የነበረውን ሕዝባዊ ድጋፍ በተመለከተና ከነዚህም ጋር ቁርኝት በሚኖራቸው ነጥቦች ዙሪያ ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው፡-

**ግዮን፡- የተያዙት የትና እንዴት ነበር?**

አቶ በቀለ፡- የተያዝኩት አዳማ 01 ቀበሌ በሚገኘው መኖሪያ ቤቴ ውስጥ ነው፡፡ እንደ ወንጀለኛ በብዙ አጀብና  ፍተሻ ነበር ከቤቴ የወሰዱኝ፡፡ በፍተሻው ብዙ ነገሮች ወስደውብኛል፡፡ አስቀድሞ ከነበረኝ ተሞክሮ በመነሳት ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ እንደሚወስዱኝ አውቅ ነበር፡፡ ሁኔታዎቹ በሙሉ አስቀድሞ ሲዩዝኝ ከነበረው ሂደት የተለዩ አልነበሩም፡፡

**ግዮን፡- አስቀድሞ ስለተመሠረተብዎና ስለ አሁኑ ክስ  ይዘት ቢነግሩን?**

አቶ በቀለ፡- በመጀመሪያው እሥር፤ የተመሠረተብኝ ክስ ‹‹የአገር አንድነትና ፖለቲካን በመንካት›› የሚል ሲሆን፤ በተለይ “ኦነግ ከሚባልና በሽብርተኝነት ከተፈረጀ ድርጅት ጋር ለመሥራት ኬኒያ ሶሎሎ ሄደህ ወታደራዊ ስልጠና ወስደህ በመመለስ፤ ያንን ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረሃል” የሚል ይዘት ነበረው፡፡ ግን እኔ በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ነበርኩ፡፡ ቅዳሜና ቀጣዩን ቀን በአዳማ ከቤተሰቦቼ ጋር ቆይቼ እሁድ አመሻሹ ላይ አዲስ አበባ እመለሳለሁ፡፡ አኗኗሬ ለማንም ሰው ግልጽና የሚታወቅ ነበር፡፡ በምን ዓይነት መንገድ ሄጄ ስልጠናውን እንደወሰድኩ አላውቅም፡፡ የተረጋገጠብኝ ነገርም የለም፡፡ ሆኖም ሌሎች ነገሮችንና የሃሰት ምስክሮችን አቀረቡብኝ፡፡ የስምንት አመት ፅኑ እስራት ከተፈረደብኝ በኋላ ይግባኝ ጠይቄ  የተላለፈብኝ ቅጣት ወደ ሦስት ዓመት ከ7 ወራት እሥር ዝቅ ተደረገ፡፡ ይሄንን የቅጣት ጊዜ በሦስት ዓመት ከሁለት ወር በአመክሮ ጨርሼ መውጣት ሲገባኝ፤ የተወሰነብኝ የእሥር ጊዜ ጨርሼ ለመውጣት ተገደድኩ፡፡

የአሁኑ እሥራቴ ክስ ደግሞ ‹‹ሽብርተኝነት›› ነው፡፡ “ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የነበረውን ማስተር ፕላንን የተመለከተ ጥያቄ በማንሳት ሕዝቡን ቀስቅሳችኋል” የሚል ይዘት አለው፡፡ ያ ጥያቄ ሕዝቡን አደባባይ ያስወጣ  ጥያቄ እንጂ ሁከት አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ የፌዴራልና የክልላዊ መንግሥቱ አመራር አባሎችም “የራሳችን ችግር ነው” በማለት ያመኑበት ነበር፡፡ ለማንኛውም ሁለት ዓመት ከሁለት ወራት በላይ በእስር ቤት እንድቆይ ያደረገኝ፤ ይሄ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኝ የኦሮምያ ክልል ልዩ ዞኖች ማስተር ፕላን ጉዳይ ነው፡፡

**ግዮን፡- በችሎት ስለነበረው እሰጥ-አገባና ‹‹ችሎት ደፍራችኋል›› ስለተባላችሁበት ጉዳይ ማብራሪያ ቢሰጡን?**

አቶ በቀለ፡- የሚሠሯቸው ድራማዎች ሁሉ በመጨረሻ ወደመጋለጡ ደርሰው ነበር፡፡ እኛ የጠራናቸው ማስረጃዎች እንዳይሰሙ ሲደረግ ተቃውሞ አቀረብን፡፡ ተቃውሞአችንን የሚሰማ ሲታጣ በራሳችን መንገድ ተቃወምን፡፡ የተቃወምነው በሰላማዊ መንገድ መዝሙር በማስራጨትና የፍርድ ቤት ዳኞች የሚናገሩትን ባለማዳመጥ ነበር፡፡ በዚያ ምክንያት ሁከት ፈጥራችኋል፣ ረብሻችኋል በማለት ስድስት ስድስት ወራት እስር ተፈረደብን፡፡ በሚቀጥለው ችሎትም የእኛን ማስረጃ የማይሰማና ለማዳመጥ ፈቃደኛ ካልሆነ ፍርድ ቤት፣ ከሕግ አካሄድ ውጭ ማስረጃ ከማይሰማ ፍርድ ቤት፣ የክርክር መቃወሚያ ንግግር እንዳናደርግ ከከለከለን ፍርድ ቤት፤ ምንም የምንጠብቀው ነገር አልነበረም፡፡ ምንም ሳለመናገር ወሰንን፡፡ ዳኞች በሚቀርቡበት ጊዜም “ክብር የማይገባው ፍርድ ቤት ነው” ብለን ስላመንን ላለመነሳት ወሰንን፡፡ ስንጠራም ዝም አልን፡፡ መኖራችንን በእጃችን ብቻ በማመልከት ተቃውሞአችንን ገለፅን፡፡  ድርጊታችን ሕገ-ወጥ መሆኑን ብናውቅም፣ ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ነገርን ብንቃወምም፤ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ስንል አንድን ሕግ ጥሰን የሚያስከትለውን ቅጣት በመቀበል፤ ሰላማዊ ታጋይነታችንን ለመግለፅ ሞክረናል፡፡ ይሄ ሁሉ ሆኖ እያለ በመካከል ምን እንደተፈጠረ በማናውቀው ሁኔታ ውጡ ተባልን፡፡

**ግዮን፡- አወጣጣችሁ እንዴት ነበር?**

አቶ በቀለ፡-  ጥድፊያ የተመላበትና በጣም የተለየ ነው፡፡ ሌሎቹ ስማቸው ይጠራል፣ ከዚያ ተሃድሶ ወደሚሰጥበት ቦታ ይወሰዳሉ፡፡ ከተሃድሶ በኋላ የምስክርና የመፍቻ ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡ እኛ በዚያ ሂደት ውስጥ ሳናልፍ  ከምንኖርበት ክፍል ተጠራንና “አሁኑኑ እቃዎቻችሁን ይዛችሁ ውጡ!” ተባልን፡፡ በእጃችን ምንም ገንዘብ ስላልያዝን ቤተሰብ ለመጥራት እንኳ ጊዜ አላገኘንም፡፡ ደውለን ቤተሰብ የምንጠራበት ገንዘብም አልነበረንም፡፡

**ግዮን፡- ሲፈቱ ምን ተሰማዎት? እሥር ቤቶቹን እንዴት ይገልጿቸዋል?**

አቶ በቀለ፡- የእሥሩ ሁኔታ ለእኔ በጣም የተለየ ትርጉም የለውም፡፡ ብዙ ሰዎች እኔ ያለፍኩበትን አልፈውታል፡፡ ከዚህ በፊትም ሌሎች ሲያልፉበት የነበረ የእሥር ዓይነት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በቤተሰቦቻችን ላይ ከደረሰው ሁኔታ፤ እሥርን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ  እናውቀዋለን፡፡ በእያንዳንዱ ቤተሰብ የታሠረ ሰው እናውቃለን፡፡ እሥር የሚፈራ ቢሆንም ሁሌ ዝግጁ ነን፡፡ እዚያ ውስጥ የነበረውን ነገር የመናገሩ አስፈላጊነት አይታየኝም፡፡ ያም ሆኖ እስር ቤቶች ይታወቃሉ፡፡ በአንድ ቦታም ክፍሎቹ ጠባብ ናቸው፡፡ በተባይ የተሞሉም ናቸው፡፡ ህክምና የላቸውም፡፡ በቂ ንፋስና አየር አይገኝበትም፡፡ በቂ የመኝታ ቦታ የለም፣ መዝናኛ የለም፣ በቂ ምግብ አይቀርብም፡፡ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ነው የሰው ልጅ 10 እና 15 ዓመታት፣ አንዳንዶችም ዕድሜ ልክና ሞት የሚፈረድባቸው፤ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ለማኖር ነው፡፡ እጅግ በጣም ዘግናኝ ነው፡፡ ለአገሪቱም በጣም አስከፊ የሆነ አኗኗር ነው፡፡ እሥር ቤትን እንዲህ ነው የማስበው”

**ግዮን፡- “ኢሕአዴግ እሥረኞችን የፈታው የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ሳይሆን በህዝብ ትግል ተገድዶ ነው” በሚሉት አስተያየቶች ይስማማሉ?**

አቶ በቀለ፡- “የፖለቲካ ምህዳሩን እንዲያሰፉ ሲጠይቁ ሃያ ስንት ዓመታት አለፉ፡፡ እስከዛሬ ድረስ የቆየው “ጆሮ ዳባ ልበስ” በማለት ነው፡፡ አሁን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መቀጠል

የማይቻልበት ደረጃ ደርሰዋል። የሕዝቡ ጫናም በዝቷል። የውጪ ተፅዕኖም እጅግ ከፍተኛ ነው። ሕዝቡም ከአሁኑ በኂላ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ለመቀጠል ፈቃደኛ አይደለምና አንድ ነገር መደረግ ነበረበት። በመሆኑም "ለጊዜው ይህች ማስተንፈሻ ትሆነናለች" ብሎ እሥረኞችን መፍታት መርጧል። ይህ ስለሆነ የፖለቲካ ምህዳሩ ይሰፋል የሚል ብዙም ዕምነት የለኝም። ይኸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መልሶ እየታወጀ ነው። ከመታሠራችን በፊት ወደነበረው ሁኔታ ተመለስን እንጂ "ሰፋ" ማለት አይቻልም።

**ግዮን፡- የፖለቲካ ምህዳሩን አሰፋ የሚባለው ምን ሲደረግ ነው?**

አቶ በቀለ፡- የፖለቲካ ምህዳሩን አሰፋ የሚባለው አሁንም መንግሥት በደንብ ሕዝቡን አዳምጦ ስልጣኑን ለመልቀቅ ዝግጁ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው። ይሄ ሥርዓት አርጅቷል። እንደዚሁ እየተደረተ፣ እየታጠፈ፣ አሮጌ ነገር እየተደራረበ በዚህ ሁኔታ መቀጠል የሚችል አይመስለኝም። ይሄ በተፈጥሮም ሕገ ወጥ ነው። ያረጀ ነገር ለአዲስ መንገድ መልቀቅ አለበት። ስለዚህ ይሄ ያረጀ ሥርዓት ስለሆነ አዲስ የሥርዓት መንገድ መፈጠር አለበት። ያን ጊዜ ነው ፖለቲካዊ ምህዳሩን ለማስፋት ዝግጁ ነው የምንለው። አሁን በዚህ በምናየው ሁኔታ ዝግጁ የሆነ አይስመለኝም። ባለበት እየረገጠ መቀጠሉን የሚፈልግ ይመስለኛል

**ግዮን፡- በአገራችን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በፈጣን የለውጥ ሂደት ላይ ያለለ ይመስላል። ይህን መሳዩ የለውጥ እንቅስቃሴ፤ እየታገላችሁለት ላለው ነገር ስኬት የሚጠቅም ነው ወይስ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል?**

አቶ በቀለ፡- በአንዳንድ ቦታዎች ከታለመላቸው እቅድ ውጪ እየሄዱ ያሉ የሚመስሉ ሁኔታዎች አሉ። በኢሕአዴግ ዘንድ ንብረት እንዲወድም እና ሕዝቦች ከኖሩበት ቀዬ እንዲፈናቀሉ ወይም በአንድ ስፍራ ብቻ ተገድበው እንዲኖሩ፣ አንዱ ወደሌላ እንዳይንቀሳቀስ የማድረግ አዝማሚያ አለ። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከስሜታዊነት ሊሆን ይችላል፤ በሌላ ቦታዎች ደግሞ ሆን ተብሎ ለውጡን በማይፈልጉ ኃይሎች አማካይነት የብጥብጥ አዝማሚያዎችና ዜጎችን ትንሽ ስጋት ላይ ሊጥሉ የሚችሉ የሚመስሉ ሁኔታዎች ይታያሉ። ይሄ ግን ማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ እውነተኛ ለውጥ ፈላጊዎች የሚሹት አይደለም። ሲሠሩ የነበሩትም ለዚህ አይደለም። ሰለዚህ ይሄ ያሳስባል። በዚህ ሁከትና በብጥብጥ በመሳሰሉ ነገሮች ለውጥ ይመጣል ተብሎ አይታሰብም። ስለዚህ መንገዳቸውን የሳቱ አንዳንድ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በእነዚህ ላይ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሕዝብ አበክሮ መሥራት ያለበት ይመስለኛል።

በበኩላችን እንዲህ ዓይነት ነገሮችን፣ አመፅ እና ብጥብጥን በጥብቅ እንቃወማለን። ሰዎች በየአካባቢያቸው ተዘዋውረው የመሥራት መብታቸውን የሚገድቡ አሠራሮችን በሙሉ እንቃወማለን። ዘርን ወይም ኃይማኖትን መሠረት ያደረጉ የማግለል፣ ለይቶ የማጥቃት እንቅስቃሴዎችን በጣም እንቃወማለን። ዜጎች ምንጊዜም ቢሆን በመካከላቸው የጠላትነት ስሜት እንደሌላቸው ሁሉም ይገነዘባል።

በዚህ መሠረት ይሄንን ችግር ያመጣው ሥርዓቱ ከሆነ፣ ሥርዓቱ ላይ ብቻ እንዲያተኮርና ሕዝቡ ትግሉን ማካሄድ ካለበት ከሥርዓቱ ጋር እንጂ በየትኛውም አካባቢ በተገኙ ሕዝቦች ላይ አለመሆኑን ሁሉም እንዲያውቅ ያስፈልጋል። እኛም በዚህ መሠረት ለአባሎቻችንም ሆነ ለደጋፊዎቻችን በምንገናኝበት ቦታ ሁሉ፣ በአገኘነው አጋጣሚዎች ሁሉ ይሄንን ከማሳሰብ እና ከማስተማር ተቆጥበን አናውቅም። ነገር ግን እነዚህ አዝማሚያዎች የሉም ማለት ደግሞ አይቻልም።

**ግዮን፡- የኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ በቅርቡ ባወጣው መግለጫ በአገር ውስጥና በውጪ ካሉ ተቃዋሚዎች ጋር አብሮ የመሥራት ፍላጎት እንዳለው ጠቅሷል። ለዚህ ምን አስተያየት አለዎት?**

አቶ በቀለ፡- እኔ በፓርቲዬ ስብሰባ ላይ ተገኝቼ የሰጠሁት ሐሳብ የለኝም። ይመስለኛል መግለጫው የወጣው ከመፈታታችን በፊት ነው። እንደ ግለሰብ፣ ውሳኔው በጣም ጥሩ ነው። ከዚህ በፊትም ያጣነው እንዲህ ዓይነት ተነሳሽነት ነበር። ዜጎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ በሚያገባቸው በአገራቸው ጉዳይ ላይ ተሰብስበው ቢወያዩ መልካም ነው ብለን እናስባለን። ከዚህ በፊት መንግሥት ማንንም አላወያየም። ከማንም ጋር አልሠራም። "እኔ ብቻ ነኝ አዋቂ። የዚህ አገር ጉዳይ የሚመለከተው እኔን ብቻ ነው። ትክክለኛው መንገድ የእኔ ብቻ ነው" በማለት አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይሄ ለብዙ ችግር ዳርጎናል። በሕዝቡና በአገር ጉዳይ ላይ ብንመካከር በጣም ደስተኞች ነን።

**ግዮን፡- የኦሕዴድን መግለጫ ተከትሎ ኦፌኮ አራት ጉዳዮችን በማንሳት ለኦሕዴድ ጽ/ቤት የእንነጋገር ደብዳቤ ማስገባቱንና ለጊዜው ምላሽ አለመገኘቱን ዶክተር መረራ ጉዲና ለቪኦኤ ገልጸው ነበር። ስለዚህ ሁኔታ የሚያውቁት ነገር አለ?**

አቶ በቀለ፡- ደብዳቤ መግባቱን አላወኩም። ምናልባት ከመፈታቴ በፊት የሆነ ነገር ሊሆን ይችላል። ያም ሆኖ ጉዳዩን የምመለከተው በመልካም ጅማሮነቱ ነው። ቢጠሩንም ባይጠሩንም ፍላጎታቸውን ካየን በመነጋገር እና አብረን አንድ በሚያደርጉን በአገራችን ጉዳዮች ላይ ብንነጋገር ደስ ይለኛል። ተግባራዊ ይሆናል ብለንም እንጠብቃለን።

**ግዮን፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ኦሕዴድ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ አሠራር ትንሽ ያፈነገጠ አካሄድ በማሳየት ለውጦች መታየት ጀምረዋል። ግን ተቀራርባችሁ የምትሠሩበት ዕድል ቢፈጠር፤ ኦሕዴድ ሲከተለው በነበረውና እናን በምትከተሉት ርዕዮተ-ዓለም መካከል ግጭት ሊፈጠር አይቻልም?**

አቶ በቀለ፡- እኛ አሁንም ሆነ በፊትም ኢሕአዴግ ከሚከተላቸው ፖለሲዎች የምንቀበላቸው አሉ። በመርህ ደረጃ ከሚከተላቸው ነገሮች እኛም የምንቀበላቸው ነገሮች ነበሩ። ግን ዋናው ነገር ተግባራዊ አለመሆኑ ነው። ኢሕአዴግ ራሱ የፃፈውን ሳይሆን የሚተገብረው ሌላ ነገር ነው። ከራሱ ጠባብ የቡድን ፍላጎት አንፃር ነው የሚተረጉመው። በተለይ ሕወሓት የበላይነቱን ይዞ በዚያ ፓርቲ ዙሪያ ከሚሠራቸው ነገሮች አሁን እየራቀ ያለው ኦሕዴድ ራሱን እየፈለገ፣ የራሱንም ሥራዎች በመጠነኛ ደረጃም ቢሆን እያስከበረ መሆኑን እንገነዘባለን። ስለዚህ በነፃነት መንቀሳቀሱን ከቀጠለ ኦሕዴድ ከእኛ ጋር ለመሥራት ብዙ የሚቸግረው አይመስለኝም።

**ግዮን፡- ለሁለተኛ ጊዜ ከእስር ሲወጡ በአዳማ በተደረገልዎ አቀባበል ምን ዓይነት ስሜት ተሰማዎ?**

አቶ በቀለ፡- አቀባበሉ በጣም ግሩም ነበር። በጣም አስገራሚ ነበር። ያልጠበቅኩትም ነበር የሆነው። ከዚህ በፊት ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ባደረኩት ሙከራ ብዙ ሰው አብሮኝ አልነበረም። ከዚህ በፊት ታስሬ በተፈታሁበት ጊዜም መጥተው ለመጠየቅ እንኳን ብዙ ሰዎች ይፈሩ ነበር። በዚያ ምክንያት አሁንም ከዚህ ያልተሻለ ሊሆን ይችላል የሚል ዕምነት ነበረኝ። ነገር ግን እጅግ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ነው የተቀበለኝ። ይሄ አሰገርሞኛል። ይህም የሆነው በሁለት ምክንያት ነው ብዬ አስባለሁ።

አንደኛው ሰው ለዘመናት ከተጫነበት ኢ-ፍትሐዊነት ወይም የነፃነት እጦት በአሁኑ ሰዓት መላቀቅ የሚፈልግ መሆኑን ነው የተረዳሁት። ስለዚህ ሕዝቡ ከጎኑ ሊቆሙ የሚችሉ ሰዎች በተገኙ ጊዜ መተባበር የሚፈልግ መሆኑን ተረድቻለሁ። በሌላ መንገድ ደግሞ ኢሕአዴግ "አሸባሪ" ፣ "ፀረ ሰላም" ብሎ ያሠራቸውን ሰዎች "የለም ፀረ ሰላም አይደሉም። እነዚህ የሕዝብ ወገኖች ናቸው። ከዚህ በፊት በፍትሕ ሥርዓቱ ሲሠሩ የነበሩ ነገሮች ሁሉ፣ ሲሰሙ የነበሩ በደሎችና ደባዎች ሁሉ ልክ አይደሉም። እዛ ታሥረው ያሉት የሕዝብ ወገኖች ናቸው እንጂ፣ ድሆች ናቸው እንጂ ፀረ-ሕዝቦች አይደሉም። ወይንም ሌላ በደል የፈፀሙ ሰዎች አይደሉም። ይልቅስ ልክ ያልሆንከው አንተ ነህ! ስለዚህ ይሄንን አይተህ ይሄንን ማዕበል ተመልክተህ አንተም ወደመንገድህ ተመለስ" ብሎ የማስጠንቀቅያ ደውል ነው የሰጠው ሕዝቡ።

**ግዮን፡- የጠቅላይ ሚኒስትሩን የስልጣን መልቀቅ ጥያቄ እንዴት ተመለከቱት?**

አቶ በቀለ፡- ኦ ይሄን ባልናገር ይሻላል ነበር። ምክንያቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ስልጣን ነበራቸው? በግላቸው ቅን እና መልካም ሰው ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በእውነቱ ስልጣን ነበራቸው? የመወሰንና የመሻር ስልጣን ነበራቸው? እንደ አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊሠራ የሚገባውን ነገሮች ይሰሩ ነበር ለማለት ያስቸግረኛል። ስለዚህ ስልጣን ኖሯቸው ስልጣን ለቀቁ ቢባል ራስን ማሞኘት ነው ይሆናል። ከኢሕአዴግ አንድ እጅ ወደ ሌላው ስልጣን ቢተላለፍም ብዙ የሚያመጣው ለውጥ ያለ አይመስለኝም። ስልጣን መልቀቅ ማለት የግለሰቦች ሳይሆን የሥርዓት ነው። እንዳለ ቡድኑ ወይም ፓርቲው ሲለቅ ነው ስልጣን ለቀቀ የሚባለው እንጂ በመካከላቸው ከአንዱ ወደ አንዱ ቢያዘዋውሩት የአሁኑ ጠ/ሚኒስትር፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር ከመባል ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም። በዚህ ሥርዓት ወደፊት የሚነሳውም በራሱ መንገድ የወሳኝነት ሚና ይቀጥላል ብዬ መናገር ያስቸግረኛል።

**ግዮን፡- በእስር ላይ እያሉ ጎንደር ላይ በተካሄደው ትልቅ ሕዝባዊ ሰልፍ፤ የእርስዎን ፎቶ ግራፍ በመያዝ ‹‹አቶ በቀለ መፈታት አለባቸው!›› ሕዝቡ ድምፁን ሲያሰማ ነበር። በአጭሩ በአማራው ክልል የሚደረገውን የሕዝብ እንቅስቃሴ እንዴት ይመለከቱታል?**

አቶ በቀለ፡- በመድረክ ውስጥ ሳለሁ በጥቂቱም ቢሆን ከኅብረ-ብሔር ፖርቲዎች ጋር ተቀራርቦ የመሥራት ባሕል ነበረኝ። በግሌም የምቀርባቸው ሰዎች አሉ። በአንድነትና በኅብረ-ብሔራዊነት አምናለሁ። የሁሉም ሕዝብ መብት ሊከበር እንደሚገባው አምናለሁ። በአንድ አካባቢ ያለ ኢ-ፍትሐዊነት የትም ቦታ ላለ ፍትሕ ጠንቅ ነው የሚባለውን አስተሳሰብ በደንብ እጋራለሁ። በየትኛውም የአገራችን ክልል ያለ ኢ-ፍትሐዊነት የትኛውም ቦታ ያሉ ፍትሖችን ያዛባል። ችግር ያመጣብናል ። ስለዚህ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚከሰቱ፣ የሚታዩ ነገሮችን በጥሞና እከታተላቸዋለሁ። ጎንደር አካባቢ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ የት ድረስ እንደነበር እረዳለሁ። በአካልም የተወሰነውን አውቃለሁ። በጎንደርና አካባቢው ጥንት የነበረውንና አሁን ያለውን አውቃለሁ። በዛ አካባቢ ሆኜ አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ባልችልም የጎንደርን ሕዝብ ችግር በደንብ እጋራለሁ። ይሰማኛልም። አቅም በፈቀደ መጠን ደግም የትግሉ አካል ብሆን ደስ ይለኛል። በጎንደር አካባቢ ብዙ ደጋፊዎች አሉኝ። እኔም በጣም አከብራቸዋለሁ። የቀድሞ የእሥር ቤት ወዳጄና አሁንም ጓደኛዬ የሆነው አንዱዓለም አራጌ የጎንደር ሰው ነው። እናም የጎንደር ሰው ብዙ ጊዜ የእኔን ፎቶ ይዞ እንድፈታ ይጠይቅ እንደነበርም አውቃለሁ። አሜሪካን አገር በሄድኩበት ጊዜም አንዳንድ ከጎንደር አካባቢ ወደዛ የሄዱ ወዳጆቼ መተው ጎብኝተውኛል። በግል ደረጃም ተገናኝተን ተነጋግረናል።

እንዴት እንደምገልፀው አላውቅም። በጣም ጥሩ የሆነ ስሜትና ሀገራዊ ፍቅር ነው ያለው በዛ ምክንያት ሊሆን ይችላል። አሁንም ድረስ በእዛ አካባቢ ያለውን ሁኔታ በልዩ ዓይን እና ፍቅር እመለከተዋለለሁ። በአገራችን በሁሉም ዙሪያ ያለው ነገር የሚገባኝ ቢሆንም የጎላ ችግር ያለባቸው አካባቢዎችን ደግሞ በተለየ ትኩረት መታየት እንዳለባቸው አምናለሁ። ምናልባት ከነዚህ ችግሮች ሁሉ የመነጨ ሊሆን ይችላል ብዙ ደጋፊዎች እና አድናቂዎች አሉኝ። ስለዚህ በጣም ነው ደስ የሚለኝ። እግዚአብሔር ያክብርልኝም እላለሁ። እኔም በጣም አከብራቸዋለሁ። ወደፊትም ብዙ መንገድ አብረን መሄድ እንችላለን።



# <<ማታ ማታ ዓይኔ ተሸፍኖ በሰንሰለት ታስሬ ለሴት ልጅ የማይገባ ዘግናኝ ጭካኔ ተፈጽሞብኛል>>

## እማዋይሽ ዐለሙ

ከአሥር ዓመታት አሥራት በኋላ ከወህኒ የወጣችው ወ/ሮ እማዋይሽ ዐለሙ፤ በእሥር ላይ እያለች የሰማንያ ዓመት አዛውንት በሆኑት መንፈሰ-ጠንካራ እናቷ ትጎበኝ ነበር። ከጥንካሬዋና ከአስተዋይነቷ በስተጀርባ የነበሩት እናቷ ናቸው። ‹‹ጽኑ ምኞቴ ፍቅርና ሰላም በወንዞቿ ውስጥ እንዲፈስ፣ አንድነትና የጠነከረ ኅብረት በየተራራዎቿ አናት ላይ እንዲያስተጋባ እንዲሰፍን ነው። ህልሜም የጎጥ፣ የጎሳና የዘር ነገር በዚች የተባረከች ለምለም አገር ላይ እንዳይኖር ነው›› የምትለው ወ/ሮ እማዋይሽ ከመጽሔታችን ጋር ያደረገችው ቆይታ የሚከተለውን ይመስላል።

**ግዮን፡- በቅድሚያ ስለማንነትሽና ወደ ፖለቲካው ዓለም ስለመጣሽባቸው ምክንያቶች ብትገልጪልን?**

እማዋይሽ ዐለሙ እባላለሁ። ቀደም ሲል የተማርኩት የቱሪዝምና የሕግ ሙያ ነው። እንደገና ሁለተኛ ድግሪ በሕዝብ ግንኙት ሠርቻለሁ። የንብረት አያያዝ ሙያም ተምሬያለሁ። በኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት ሆኜ አገልግያለሁ። ትዳር የመሰረትኩት ገና በልጅነቴ ነው። አራት ልጆችንም አፍርቻለሁ። ወደ ፖለቲካው የገባሁበት አንደኛው ምክንያት በሕዝቡ ላይ የማየው የመልካም አስተዳደር ችግር ውስጤን የጎዳው መሆኑ ነው ። ሌላው ደግሞ መቼም ሰው አብረነው በፍቅር ብንኖርም የማንነት ጥያቄ የሚባል አለ። በአማራ ዙሪያ የማደርገው ነገር ውስጤን ይረብሸኝ ነበር። እና ‹እኔ ማን ነኝ?› የሚል ጥያቄ ይመጣብኝ ነበር። በግሌ በመንግሥትና በአስተዳደሩ የደረሰብኝ ችግር አልነበረም። የወገኖቼን ጉዳት መመልከቴና ችግሩ ሲከፋም በዝምታ ማለፉ ስለከበደኝ ነው።

**ግዮን፡- ወደ ፖለቲካው በማተኮርሽ ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሰብሽ ችግር ምን ነበር?**

እማዋይሽ፡- በመጀመሪያ ከደረጃ ዝቅ አድርገውኛል። መስሪያ ቤት ላይ ከስራ አግደውኛል። አንድ ዓመት ሙሉ ያለምንም ሥራ ደመወዝ ይከፈለኝ ነበር። ያን ያደረጉት በአካባቢው የማደረገውን እንቅስቃሴ በማየት ይመስለኛል። እኔም ነገሮች ጥሩ እየሄዱ እንዳልሆነና አዝማሚያው እየከፋ መሆኑን ከተረዳሁ በኋላ አኩርፌያለሁ፣ አፈንግጫለሁ።

**ግዮን፡- በነበርሽበት አካባቢ የማኅበረሰቡ መሠረታዊ ጥያቄ ምን ነበር?**

እማዋይሽ፡- መሠረታዊ ጥያቄው ሥርዓቱ በአማራ ክልል ሕዝብ ላይ ያደርግ የነበረው ጫና የከፋ በመሄዱና የወሰን ጥያቄም ስለተነሳ ሕዝቡ ሕገ-መንግሥቱን ብቻ ተመርኩዞ በሰለማዊ መንገድ በሚጠይቅበት ጊዜ እስርና እንግልት ይደርስባቸው ነበር። ኢኮኖሚያዊ ጫናም ይደረግባቸው ነበር። እነዚህ ነገሮች ተደማምረው ሕዝቡ የመብት ጥያቄ ማንሳት ጀመረ።

**ግዮን፡- የተከሰስሽበት ክስ ምን ይላል? እንዴት ተያዝሽ?**

እማዋይሽ፡- የተያዝኩት በ2001 ዓ.ም ሚያዝያ 16 ቀን ነው። የተከሰስኩት መንግሥትን ለመገልበጥ ከግንቦት ሰባት ጋር ግኑኝነት ፈጥረሻል… በሚል ነው ።

**ግዮን፡- እስር ቤት እንደገባሽ ምንድነው ያገጠመሽ?**

እማዋይሽ፡- በቅርቡ በሆነ ሚዲያ ላይ ስለዚህ መንግሥት ሰብዓዊ መብት አያያዝ ሲናገሩ ሰምቻለሁ። እና በጣም አዝኛለሁ። ማስተካከል ነው እንጂ የሚሻለው መካድ በጣም ያሳፍራል። እኔ ማዕከላዊ በከፍተኛ ደረጃ ነው የተደበደብኩት። ማታ ማታ ዓይኔ ተሸፍኖ በሰንሰለት ታስሬ ለሴት ልጅ የማይገባ ዘግናኝ ጭካኔ ተፈጽሞብኛል። በጣም የሚገርመው የደረሰብኝ ስቃይ ምርመራ ላይ እያለሁ ነበር በአሜሪካ ሬድዮ ጣቢያ የተጋለጠው። የተፈጸመብኝ ግፍ ብዙ ነው። በድብደባ ብዛት ብዙ ጊዜ ደም በደም ሆኛለሁ። አሰቃቂና ዘግናኝ ነበር። እስካሁን በሰውነቴ ላይ ያሉት የድብደባው ምልክቶች አልጠፉም። በየሚዲያው ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ‹በደርግ እንጂ በእኛ ሥርዓት እንዲህ ዓይነት ስቃይ የለም› እያሉ ሲናገሩ በጣም ያሳፍራል ። ይድረስባቸው እንዳንል ለሰው ክፉ አንመኝም። ግን ከመካድ ማስተካከል ይቀል ነበር። የአንድ አገር ዜጎች ሆነን በዚች አገር ላይ ያለውን ችግር ማስተካከልና ለሕዝቦች ምቹ መደላደል መፍጠር ሲገባ ለፕሮፖጋንዳ፣ ለዕርዳታ

ተብሎ የዜጎች መብት እየተረገጠ ሀቁን መካድና ማስተባበል በጣም ያሳዝናል።

**ግዮን:- ማዕከላዊ በስቃይ ውስጥ በነበርሽበት ወቅት መረጃው ሾልኮ ወጥቶ ሲነገር ምን ተሰማሽ?**

እማዋይሽ:- እግዚአብሔር ይመስገን በእናንተ በጋዜጠኞች፣ በጦማሪያን እና በተለያዩ ሰዎች ጩኸት ምክንያት ስቃዬ ረጅም ጊዜ አልቆየም። አንድ ወር ከሃያ ቀን ነው ማዕከላዊ የቆየሁት።

**ግዮን:- ከዚያ በኋላ ወዴት ወሰዱሽ?**

እማዋይሽ:- ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ነው። እኔን ብቻዬን ነው ያሠሩኝ። ጠዋት ወይም ማታ ነበር ለሽንት የሚከፈትልኝ። ውሃ ጠምቶኝ የሽንት ቤት ውሀ ጠጥቻለሁ። በእውነቱ ሳላመሰግነው የማላልፍው ዶክተር በየነ የሚባል እሥረኛ ነው። ቋንቋ ያው እዚህ ኩታ ገጠም ስለሆነ እሰማለሁ። በትግርኛ ቋንቋ "ይቺ ሴት እየሞተች ነው፤ ወደ ከፍተኛ ሕክምና ትሂድ" ብሎ ለአጃቢዬ ነገራት፤ ዶክተሩ እሥረኛ ስለነበረ አላምን ብለው ሌላ ራሳቸው ዶክተር ጋር ነው ያቀረቡኝ።

**ግዮን:- ለምንድነው የእናንተ የፍርድ ሂደት አጭርና ፈጣን ውሳኔ ያገኘው?**

እማዋይሽ:- እንዳንገናኝ፣ እርስ በርሳችን እንዳንነጋገር በማድረግ የስነ-ልቦና ጉዳት ማድረስ ይመስለኛል። እርስ በርስ እንኳ ዓይን ለዓይን እንዳንተያይ ተደርገናል። ለምሳሌ ጄነራል ተፈራ ወይም ጄነራል አሳምነው ወጥተው ከሄዱ በኋላ ጀርባቸውን እንኳ እንዳላይ አቆይተው ይወስዱኛል።

**ግዮን:- የእሥር ጊዜሽን የምታሳልፊው በምን መልኩ ነበር?**

እማዋይሽ:- ሬድዮ ይዘን ስንገባ ተከልክለን። ቴሌቭዥን ከ70 በላይ ሰው ባለበት ክፍል ታጭቀን ነው የምናየው። እንደምንም ዜና ለማዳመጥ እሞክራለሁ። መጽሐፍ በእኔ ስም እንዳይገባ ብከለከልም በሌሎች እስረኞች ስም እየገባ አነብ ነበር። ብዙ ጊዜዬን በማንበብ ነው ያሳለፍኩት።

**ግዮን:- በእስርቤት የሚገኙትን የሴቶች ብዛትና የሴት እስረኞችን ሁኔታ እንዴት ታዘብሽው?**

እማዋይሽ:- በእስር ቤት ውስጥ ያሉት ሴቶች እጅግ ብዙ ናቸው። ይሄን ያህል ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ወንጀለኞች ናቸው ብሎ ማሰብ በራሱ ከባድ ነው። በልጅነታቸው እንደታሰሩ እዚያው ያረጁ ነበሩ። ይሄ በጣም ስለሚያሳምመኝ መፅሐፍ ቅዱስ አስተምራቸው ነበር። ቢያንስ የሚፅናኑበትን ዕድል ለመፍጠር ጥሬአለሁ።

**ግዮን:- መንግሥት በይቅርታና በምህረት እንደምትፈቱ ሲናገር ምን ተሰማሽ?**

እማዋይሽ:- ያ የሰው ፍርድ እንደሆነ አውቃለሁ። ሆኖም አንድ ቀን እግዚአብሔር ነፃ እንደሚያወጣኝ አምን ነበር። በዚህ መልኩ እንዲሆን ግን አልፈለኩም። የሀገራችን ነፃነት ቀን ሲመጣ እወጣለሁ ብዬ ነበር የማስበው። ምክንያቱም አሁን ተፈታሁ እንጂ ነገን አላውቅም።

**ግዮን:- ከእስር ተለቃችኋል ውጡ ስትባሉ የነበረውን ስሜት እስኪ ንገሪኝ?**

እማዋይሽ:- መጥተው ውጡ ነው ያሉት። በማይክ እንደማንኛውም ተፈቺ አልጠሩንም። ካለሁበት መጥተው "ዕቃሽን ይዘሽ ውጪ ተብለሻል" ስባል ሌሎቹስ አልኳቸው። "አንቺ ምን አገባሽ ለራስሽ ብቻ ውጪ" ሲሉኝ "በቃ ሌሎች ካልተፈቱ መፈታት አልፈልግም እስሬን ጨርሼ እወጣለሁ" አልኩኝ። ዕቃዬን ይዤ ተመልሼ ገባሁ። በዛ ሰሞን የነበረው ለየት ያለ የፖሊሶች መቅበዝበዝ ይገርመኛል። በሌላ ቀን ፀጉሬን እየሰራሁ ሳለ ተረኛ ፖሊስ እየሮጠች መጥታ ነይ ተነሽ ዕቃሽን ያዥ ስትለኝ "ቆይ ፀጉሬን ልጨረስ" አልኳት። ከዛ በኋላ ሌላ ኦፊሰር መጣችና ሊሰናበቱኝ የነበሩትን ሰዎች ገፈታትራ አስወጣችኝ።

**ግዮን:- የፊርማው ጥያቄ መቼ መጣ?**

እማዋይሽ:- ከወጣሁ በኋላ "ነይ ፈርሚና ውጪ" ተባልኩኝ እኔ በእምቢታየ ፀናሁ። "ትበሰብሻለሽ!" እያሉ ቢያስፈራሩኝም ወደ እሥስር ቤት ልመለስ ዕቃየን አነሳሁ። አንድ አዳራሽ ሰዎች በነበርንበት ሁላችንም በአንድ ድምፅ አንፈርምም አልን። በዚህ መልኩ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወጣን።

**ግዮን:- ከእሥር ስትፈቺ ቅድሚያ በአዕምሮሽ የመነጨው ሐሳብ ምን ነበር?**

እማዋይሽ:- "እውነት ሁላችንም ተፈታን ወይ?" የሚለው ሐሳብ ነው። አሁን ለአብነት እኔ የምኖርበት አካባቢ ሳላውቅ ብዙ ሕዝብ ታሥሯል። ብዙ ሰው ከወልቃይት፣ ከጎንደር ከተማ፣ ከመተማ ስንቱን ልግለፅልህ? እንዳለ በጅምላ ታፍሶ ነው የታሠረው። በሙሉ ነው ወይ የተፈታነው? የእውነት ፍቺ ነው? ነገስ ምንድነው የሚያደርጉን? እኔ የምፈለገው በነፃነት መውጣት ነበር።

**ግዮን:- የቤተሰብሽ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት ይገለፃል?**

እማዋይሽ:- ባለቤቴን በደርግ መንግሥት ኢሠፓ ነበር ተብሎ ኢሕአዴግ ለ11ዓመት አስሮብኛል። እኔ በወቅቱ አራስ ነበርኩና ልጃችንን ክርስትና ባስነሳን ማግስት ታሰረ። አሥራ አንድ ዓመት ታስሮ በተፈታ በአምስተኛው ቀን ደግሞ እኔን እስር ቤት አስገቡኝ። እኔ ደግሞ በተራዬ አሥር ዓመት ታሰርኩ። በዚህ መንግሥት ባለቤቴ ለአሥር አንድ እኔ ለአሥር ዓመታት ታሥረናል ማለት ነው። በነዚህ ሃያ አንድ ዓመታት ውስጥ ከባለቤቴ ጋር አብረን የቆየነው ለአምስት ቀናት ብቻ ነው።

> ..."ዕቃሽን ይዘሽ ውጪ ተብለሻል" ስባል ሌሎቹስ አልኳቸው፡፡ "አንቺ ምን አገባሽ ለራስሽ ብቻ ውጪ" ሲሉኝ "በቃ ሌሎች ካልተፈቱ መፈታት አልፈልግም እስሬን ጨርሼ እወጣለሁ" አልኩኝ፡፡ ዕቃዬን ይዤ ተመልሼ ገባሁ...

**ግዮን:- የጄኔራሎቹን ከእስር መለቀቅ ስትሰሚ ምን አልሽ?**

እማዋይሽ:- "እሰይ በመጠኑ ተፈታሁ" ነው ያልኩት። ምክንያቱም ብዙ ተነግሮ የማያልቅ ግፍና መከራ አሳልፈናል። አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የነበሩበት ክፍል ውስጥ ነበር የታሰሩት። ገና እስር ቤት እያለሁ መረጃው ነበረኝ።

**ግዮን:- አሁን ያለውን? የአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ እንዴት ትገመግሚዋለሽ?**

እማዋይሽ:- እኛ አሁን ሁሉም ሰው እንዲያውቅልን የምንፈልገው፤ የምንታገለው ሥልጣን ፍለጋ አይደለም። ዛሬ የሚሰደደው ወገናችን የሰለጠነ አገር፣ የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ከመሄድ እንዲቆጠብ እዚህ የተሻለ አገር እንፍጠር ነው። አገር የሞቀውን ጥፋቱን የማያምን ሁሌ እኔ ብቻ አውቃለሁ፣ እኔን ብቻ ተቀበሉኝ ከኔ በላይ ላሳር የሚል አባዜ የትም አያደርሰንም።

**ግዮን:- የእናንተ ከስር መፈታት ተከትሎ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት እገዛ ያደርጋል የሚል ዕምነት አለሽ?**

እማዋይሽ:- የፖለቲካ ምህዳሩ ይሄ ሥርዓት እያለ ይሰፋል ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ሁሌም እንደሚባለው ጉልቻ ቢቀየር ወጥ አያጣፍጥም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለወረዱ ለውጥ ይመጣል ብዬ አልጠብቅም። እኛም ከእስር የተፈታነው ገዥው ቡድን የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ተጨንቆ ሳይሆን በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የተፈጠረው ተከታታይ ተቃውሞና ግፊት አስጨንቆት ነው።

**ግዮን:- የእማዋይሽ የወቅቱ የፖለቲካ ህልምና ምኞት ምንድነው?**

እማዋይሽ:- የእኔ ህልም ማናቸውም ስለኢትዮጵያ የሚለፉ፤ መሳሪያ የወደሩም፤ ብዕር የቀሰሩም አጠቃላይ ይሄን ሥርዓት የሚቃወሙ ሁሉ ኢሕአዴግንም ጭምር ፍትህ በነገሰበት፤ መከባበር በሰፈነበት ሁኔታ ተወያይተው የሽግግር መንግሥት ቢያቋቁሙ ምኞቴ ነው። በመቀጠል በሕዝብ አብላጫ የተመረጠ አዲስ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ቢፈጠር ህልሜ ነው። ዴሞክራሲ እኮ ስላወራህ አይደለም በተግባር የሚገለፅ መሆን አለበት። ለማውራቱማ ኢሕአዴግም 27 ዓመታት ሙሉ አውርቶታል። አሁን የምናየው በኢትዮጵያ ዕድገት አለ ምናምን ይባላል። ሕዝቡ ሳያድግ ህንፃ ቢደረደር አይጠቅመንም። ሕዝቡ በልቶ ጠግቦ ሳያድር ድንጋይ ቢቆለል አይበጀንም። ያልጠገበ የተራበ ሕዝብ ያፈርሰዋል። ህልሜ በተለይ ይሄ የጎጥ፣ የጎሳና የዘር ነገር በዚች የተባረከች ለምለም አገር ላይ እንዳይኖር ነው። ጽኑ ምኞቴ ፍቅርና ሰላም በወንዞቿ ውስጥ እንዲፈስ፣ አንድነትና የጠነከረ ኅብረት በየተራራዎቿ አናት ላይ እንዲያስተጋባ እንዲሰፍን ነው። እኔ ዕድሜዬ እየገፋ ቢሄድም ወጣቶች ጥሩ ነገር እንዲገጠማቸው እመኛለሁ።

**ግዮን:- በአካባቢሽ ያለውን የሕዝብ የኑሮ ሁኔታ እንዴት ታዘብሽው?**

እማዋይሽ:- እኔ አሁን እዚህ ጎንደር መጥቼ ወደ ገጠሩ ጎራ ስል እጅግ በጣም እያለቀስኩ ነው። ህዝቡ እያለቀሰ ነው። በማዳበሪያ፣ በእርሻ ግብአቶች በመሰረታዊ ሸቀጥ ምርቶች እጦትና የዋጋ ንረት ህዝቡን ደም እያስለቀሱት ነው። ሌላው በእኛ አካባቢ ሰላሙን እየነሳው ያለው የመሬት ወሰን ጉዳይ ነው። ህዝቡ የሚለው ሌላ ነው፤ ገዥው ሥርዓት ደግሞ ከራሱ ጥቅም ፍላጎት አንፃር የሚለው ሌላ ነው። ህዝቡ ሰሚ የሌለው ሥርዓት ተጭኖበት ምሬቱ የማይመለስ ደረጃ ላይ ደርሷል። ብቻ አገራችን አምላክ ይጠብቃት።

**ግዮን:- በመጨረሻም ጎንደር ላይ የህዝቡ አቀባበል እንዴት ነበር? እናትሽንስ ስታገኛቸው ምን ተሰማሽ?**

እማዋይሽ:- ስለህዝቡ ሁሌም ግርም ይለኛል። ከዚህ ህዝብ መሀል መፈጠር በራሱ ልዩ ኩራት ነው። ይሄ ሁሉ ይቀበለኛል ብዬ አልሜ አላውቅም። አስቸኳይ አዋጅ በታወጀ ማግስት መሆኑ ደግሞ አድናቆቴን ከፍ አድርጎታል። ይሄ ህዝብ ምን ይሠራል ብዬ ጠይቄ ነበር? ለኔ አልመሰለኝም። ከብዛቱ የተነሳ ሰው አይታይም ነበር። ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ የጎንደር ቀሚስ፣ ጋቢ፣ መቀነት፣ የቴዎድሮስን ጃኬት፣ የአፄ ፋሲል አምሳል በነሃስ ተሠርቶ ሌላም ብዙ ስጦታዎች ነበሩ። ከእግዚአብሔር ጥበቃ ቀጥሎ የወገኔ ጩኸትና ጥብቅና ነው ለዚህ ያበቃኝ። እናቴ እንደምታየው ያው ታስራለች ማለት ትችላለህ። አንደኛውኑ እኔ የታሰርኩት እሻላለሁ። በየወሩ ትመጣለች። ስቆጣት ደግሞ በየሦስት ወሩ በየስድስት ወሩ ትመጣለች። ይሄን ሁሉ የምትፈፅመው በ80 ዓመት የአዛውንትነት ዕድሜ ላይ ሆና ነው። በመጨረሻ በኢትዮጵያ ምድርም ሆነ በመላው ዓለም ለእናት አገራችሁ ነፃነት እየታገሉ ለሚገኙ ወገኖቻችን ምስጋናዬ ከፍ ያለና የላቀ ነው።



በታምራት መርጊያ

# የፖለቲከኛ እሥረኞች አፈታትና የኢሕአዴግ የሐሳብና የተግባር አንድነት ችግር

የሐሳብና የተግባር አንድነት ጎድሎኛል ያለን ኢህአዴግ፤ ጉድለቱን ከነገረንም በኋላ፤ ፖለቲከኛ እስረኞችን ልፈታ ወስኛለው ባለው ቃል ታስሮ፤ እራሱ የገባውን ቃል ለማክበር ሕቅ-እንቅ ብሎት በማመንታቱ፤ እነሆ አሁንም ይኸው ጉድለቱ እራሱን በራሱ ተወቃሽ እና አመድ አፋሽ አደረገው።

እንደ እውነቱ ከሆነም ለኢህአዴግ ይህ ውሳኔው በህብረተሰቡና በአለም አቀፍ ማሕበረሰብ ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ በአዎንታዊ ጎኑ የተወሰደለት ነበር። ሆኖም ድርጅቱ ሊመሰገንበት ይችልበት የነበረውን ውሳኔውን በምልዓት ለመፈፀም የፖለቲካ ተነሳሽነትና ብልህት ጎድሎት፤ ይኸውና እራሱን በራሱ፤ በራሱ ቃል አስሮ ተመስጋኝ ከመሆን ይልቅ ለተወቃሽነት መዳረጉ ድርጅቱ እራሱን ይቅር ሊልበት የማያስችል ከፍተኛ የፖለቲካ ስህተት እንደሆነ በብዙዎች ታምኗል።

እንደሚታወሰው የገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሦስት ሳምንታት ገደማ የፈጀውን ድርጅታዊ የግምገማና የሂስ ችሎት ካጠናቀቀ በኋላ፤ የጥቂት ቀናት ፋታና ትንፋሽ ወስዶ፤ የአራቱን የግምባሩ አባል ድርጅቶች ሊቃነመናብርት ከበር መልስ ያካሔደውን የስብሰባ ሒደትና ውሳኔዎች፥ በጋራ ያብራሩለት ዘንድ በአንድ ጠረንጴዛ ዙሪያ መሳ ለመሳ ደርድሮ ከቴሌቪዥናችን አንፃር አቀረበልን።

ሊቃነመናብርቱም የጋራ በተባለው የድህረ ግምገማ ማብራሪያቸው፥ ለብዙዎቻችን የጋራ ያልመሰለንን ማብራሪያ እያንዳንዳቸው በገባቸውና በተረዱት መጠን የየበኩላቸውን አረዳድ ሲያቀርቡልን ቆዩ። የጋራ ማብራሪያውን ተከትሎም ብዙዎች በግንባሩ ድርጅቶች ማህከል ግልፅ የሐሳብና የአቋም ልዩነት የተንፀባረቀበት ሲሉ ስለማብራሪያው ያላቸውን ትዝብ ገለፁ።

የሆነው ሆኖ፥ በዚሁ ማብራሪያ ላይ በርካቶችን ጮቤ ያስረገጠና፤ የብዙዎችን ቀልብ የሳበ የግንባሩ ውሳኔ በቅርቡ የስልጣን መንበራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው "የሐገሪቱ ቀውስ የመፍትሔ አካል ለመሆን አስቤ፥ ከፓርና ከመንግሥታዊ ሐላፊነቴ በገዛ ፈቃዳዬ ለመልቀቅ ጥያቄዬን አቅርቤያለሁ፤ በቅርቡ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ብላቹ እንደምትጠሩኝ ተስፋዬ ከፍ ያለ ነው" ባሉን፥ የደህዴኑና የግንባሩ ሊቀመንበር ጠ/ሚ አቶ ሐይለማሪያም ደሳለኝ አማካኝነት ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው በሚል ይዘት የኢህአዴግ ስራ አስፈሚ ኮሚቴ መወሰኑን ነገረን።

"በአቃቤ ህግ ጉዳያቸው ተይዞ በእስር የሚገኙና የተፈረደባቸው የተለያዩ ፖለቲከኞችን የተሻለ ሃገራዊ መግባባት ለመፍጠርና የዲሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት በማሰብ፤ ማንም ሳያስገድድኝና የማንም ምክር ሳያሻኝ፤ እራሴዉ አስቤና ወስኜ ፓለቲከኛ እስረኞችን ክሳቸው ተቋርጦ ወይም በይቅርታ እንዲለቀቁ ወስኛለሁና፤ እነሆ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ደስይበላችሁ" ብሎ አበሰረን።

እኛም "አሜን ወ አሜን ለይኩን" አልንና እንደየ እምነታችን ምስጋናችንን ለፈጣሪያችን እናቀርብ ያዝን። ይህ አልበቃ ብሎንም፥ በዚህ ብስራት መነሾ ሳይታወቅ እንደ ደራሽ ውሃ ውስጣችንን ፈንቅሎ በወጣ፤ ከእኩልነት፣ ከፍትህ እና ከዴሞክራሲ ጥም ምንጭ በሚቀዳ የደስታ እምባ ጎርፍ ተጥለቅልቀን በደስታ የደስታ እንባ አነባን፥ የደስታ ጮቤም ረገጥን...። ኢህአዴግም እንዳለው ከዚህ ቀደሙ በተለይ መልኩ የእውነት ከልቡ ሊቀየር እንደሆነ ተሰምቶን፥ በልባችን ሐሴትና ተስፋ ሞላ።

ዳሩ ምን ያደርጋል፤ "ቃል-ቃተተ" እንዲል ባለቅኔው ፀጋዬ ገ/መድህን፤ ከግብታዊ የደስታ ስሜታችን ገና በቅጡ እንኳን ሳንወጣ፤ ብስራቱን ወደ መርዶነት ቀይሮና ደስታችንን አደፍርሶ ወደ ጥርጣሬ የለወጠ፣..... ሀሴታችንን ወደ ሀዘን፣.... ተስፋችንንም ወደ ቀቢፀተስፋነት፥ በቅፅበት የሚቀይር ዜና ለመስማት ከአንድ ጀምበር የበለጠ ጊዜ ሳይወስድብን ቀረ። ለደስታ ያላደለን።

ይህ ዜና የወጣው ደግሞ፥ የኢህአዴግ አራቱ አባል ድርጅቶች ሊቃነ መናብርት የጋራ መግለጫ ከሰጡ በኋላ፤ አፍታ እንኳን ሳይቆይ ነበር።

የዚህ መርዶ መሰል ዜና ይዘት በግርድፉ፥ "የጠቅላይ ሚኒስትሩ መግለጫ ትክክለኛ በሆነ መንገድ አልተተረጎመም ወይም በተሳሳተ መንገድ ተተርጉሟል (misquoted)ነው" ከሚል መነሻ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው።

ይህንኑ ተከትሎም መንግሥት ውሳኔውን በድጋሚ እንደሚያጤነው ማስታወቁን የሚዘግብ ዜና በተለያዩ የሐገር ውስጥና የውጭ የመገናኛ አውታሮች በስፋት ይናኝ ያዘ።

ከዚህ ጋር ተያይዞም፤ ይህ ውሳኔ የተገለፀበት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽህፈት ቤት፥ ይፋዊ ድህረ ገጽ፤ የዉሳኔውን ይዘት በተደጋጋሚ ጊዜ በአዲስ ዓይነት የይዘት አቀራርብ እየለዋወጠ ያቀርብ ገባ። ይህ አድራጎትም ብዙዎችን ከማስገረሙ ባሻገር በአያሌ ዜጎችና የውጭ አካላት ዘንድ ትዝብትን አጭሮ፥ የጽሕፈት ቤቱን የመረጃ ክፍል የሙያ ብቃት (Competency) በእጅጉ ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አደረገው።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ በደስታ ማእበል ተጥለቅልቆ ይዋኝ የነበረው ድፍን አገሬው መንግሥት ቃሉን አጠፈ በሚል ስሜት ኩም አለ። የጨበጠው እንደ ሐገር የመለወጥ የተስፋና የምኞት ጉም እንደ ጤዛ ተነነ። ቅፅበታዊ ሐሴቱም በቅፅበት ወደ ሐዘንና ሰቀቀን ተቀየረ።

ምክንያቱ ደግሞ፥ ከቀደሙት የተለየ የመሰለው የኢሕአዴግ ስህተቴን አውቄዋለሁ እናም ተለዉጫለዉ አይነት ኑዛዜ፥ ግንባሩ የመለወጥ-መቀየሩን እጅግ ቀላሉ ማሳያና ድርጅቱንም ሆነ መንግስቱን ምንም አይነት ዋጋ ሊያስከፍል የማይችለው፥ እዳው ገብስ የሆነው እንዲሁም ኢሕአዴግ እንዳለው መለወጡን በተግባርና በቅፅበት ለህዝቡ ሊያሳይበትና በቀላሉ ሊተገብራቸው ከሚችላቸው ተጨባጭ ተግባራት መካከል ይኸው የፖለቲከኛ እስረኞችን የመፍታት ድርጊት እንደሆነ በሕዝብ ዘንድ በመታሰቡ እና በመታመኑም ጭምር ነበር።

ኢህአዴግም ያለውን በተግባር ሳይከውን፥ ሕዝቡም መጪውን ለማየት ሲጠባበቅ የተፈጥሮ ሂደት ነውና፥ ቀናት ይነጉዱ ያዙ። ዘግይቶም ቢሆን መንግስት ዶ/ር መረራን፣ ኦቦ በቀለ ገርባን፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ወዘተ... ጨምሮ

ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ በአደባባይ ችግሬ ነው ያለንን የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ከመቅረፍ ይልቅ፤ በማግስቱ አንዱንና ዋነኛውን የመልካም አስተዳደር አንጓ የሆነውን "ተዓማኒነት" በዜጎች ዘንድ ጥርጣሬ በሚፈጥር መልኩ፤ ፖለቲከኛ እስረኞችን ለመፍታት የገባውን ቃል ፈጥኖና በምልዓት ያለመፈፀሙ፤ አሁንም ድርጅቱ ይህንን ችግሩን በማያዳግም ሁኔታ ሊቀርፈው መዘጋጀቱን እንደምን መቀበል ይቻላል???

የተወሰኑ ፖለቲከኛ እስረኞች አንድ፥ አንድ እያለም ቢሆን በተለያየ ጊዜ መፍታት መጀመሩ፤ በመንግስት ለህዝብ የተገባውን ቃል ሙሉ ባያደርገውም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በጎና አበረታች ጉዳይ ሆኖ የሕዝቡን ትንፋሽ መለስ አደረገው።

በርግጥ ይህ የሆነው (የዶ/ር መረራን መፈታት ሳይጨምር) በብዙዎች እንደተገለፀውና እንደታመነው፤ መንግሥት ፓለቲከኛ እስረኞችን ለመፍታት የወሰነውን ውሳኔና ለህዝብ የገባውን ቃል ላለማክበር በማመንታቱ ምክንያት፥ በተለይም በኦሮሚያ ክልል በተጠራ የሶስት ቀናት ከእቤት ውስጥ ያለመወጣትና የኢኮኖሚ ግብይቶችን የማቀዝቀዝ የሦስት ቀን አድማ ባሳረፈበት ፓለቲካዊ ጫና እንደሆነ በስፋት ሲገለፅ ተደምጧል።

እጅግ በጣም አስገራሚው ጉዳይ፤ ኢህአዴግ ፖለቲከኛ እስረኞችን በራሱ ተነሽነት እንደሚፈታቸው ለህዝብ አሳውቆና ቃል ገብቶ ሲያበቃ፤ በህዝብ ዘንድ የሚያስመሠግነውንና የፖለቲካ ትርፍ የሚያስገኝለትን ይህንን ተግባር በምልዓት መፈፀም ሲገባው፤ ዘገየም ፈጠነ ሰሞኑን እየተመለከትን እንዳለዉ አንድ፤ ሁለት እያለም ቢሆን መተግበሩ ሳልቀረ፤ በዉሳኔው ላይ ማመንታትና ማወላወሉ እንዲሁም በጫናና በፖለቲካ ግፊት የራሱን ውሳኔ መተግበሩ፤ በራሱ ውሳኔው አመድ አፋሽ ከመሆኑም ባለፈ በፖለቲካ ሳይንስ ልሒቃን አገላለፅ (Committing Political suicide) ተብሎ የሚወሰድ ድርጊት ነው ብሎ ለማሰብ ያስደፍራል።

በሌላ መልኩ የተመለከትነው እንደሆነ ደግሞ፤ የመንግሥት የመልካም አስተዳደር ችግር መንሰራፋት ጉዳይ፥ እስኪያቅለሸልሸንና እጅ እጅ እስኪለን ድረስ ዘለግ ላሉ ዓመታት ሲለፈፍልንና ስንሰማው የቆየ፥ አሁንም እንደ ብሔራዊ መዝሙር በነጋ በጠባ ቁጥር እየሰማነው የቀጠለ ጉዳይ ነው።

እነሆ የመልካም አስተዳዳር ችግር አለብኝ ማለት የማይታክተው ኢህአዴግ በቀደምም፤ ከበር መልስ 17 ቀናት የፈጀውን ድርጅታዊ ዝግ ግምገማዉን ማጠናቀቁን ተከትሎ፤ እንደተለመደው "በጥልቀት ከገመገምኳቸው አበይት ችግሮቼ ውስጥ፤ አንዱና ዋነኛው "የመልካም አስተዳደር ችግሬ ነው" ብሎ በድህረ ግምገማ መግለጫው ላይም ደገመው።

ርግጥ ነው፤ ኢህአዴግ ችግሮቼ ብሎ የዘረዘራቸው ህልቆ መሳፍት ቢሆኑም የመልካም አስተዳደርን ችግር እዚህ ላይ በተለየ የምንመለከትበት አብይ ምክንያት፥ ይህንን ክልሼ ሐሳብ በመደጋገም በቸከና በተሰለቸ ጉዳይ አንባቢን ለማሰልቸት አይደለም።

ይልቁንም፥ የመልካም አስተዳደር መለኪያ ሚዛን ከሆኑት አበይት ነጥቦች ውስጥ፤ አንዱና ዋነኛው የሆነው፥ የመንግሥትን ታአማኒነት (government credibility) የሚለው ሐሳብ (Good Governance indicator) በመሆኑ ነዉ።

እናም መንግሥት ፖለቲከኛ እስረኞችን ለመፍታት የገባውን ቃል በተጨባጭና በአፋጣኝ አለመፈፀሙ እንዲሁም ማመንታቱ፤ በመልካም አስተዳደር መመዘኛ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያስነሳል።

• የመንግሥታት የመልካም አስተዳደር መለኪያ የሆነው አንዱና አንኳሩ ሚዛን (Major government indicator)፤ ታእማኒነት (Credibility) ከሆነ፤ ኢህአዴግም ይህ ችግር እንዳለብኝ በሚገባ ተረድቻለሁ፤ እናም ይህንን ችግሬን እደከዚህ ቀደሙ ሳይሆን በተግባር እቀርፈዋለሁ፤ ብሎ ያውም በከፍተኛ አመራሩ አማካኝነት ቃል ገብቶ ከነገረን በኋላ፡ አፍታ እንኳን ሳይቆይ ተአማኒነቱን በእጅጉ የሚሸረሽረውን፤ እንደ መንግሥት የገባውን ቃል ለማክበር ማመንታቱ፤ አሁንም ከፍተኛ አመራሩ የመልካም አስተዳደር ችግሩን ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ አይጨምረውም ወይ??

• በከፍተኛ አመራሩ ያልታየውና ያልተተገበረው የመልካም አስተዳደር ችግርን የመፍታት ቁርጠኝነትስ፥ አረቦች እንደሚሉት "የፊተኛው ግመል ከሸና፤ የኋለኛውም ግመል ይሸናል" ነውና፤ ለማሕበረሰቡ ቅርብ በሆነውና ሕብረተሰቡን ለከፍተኛ ምሬትና እሮሮ እየዳረገው በሚገኘው መካከለኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኘው አመራርስ፥ ችግሩ የከፋ ይሆን እንደሆን እንጂ፥ ከቶ እንደምን ሊቀረፍ ይችላል???

• ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ በአደባባይ ችግሬ ነው ያለንን የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ከመቅረፍ ይልቅ፤ በማግስቱ አንዱንና ዋነኛውን የመልካም አስተዳደር አንጓ የሆነውን "ተዓማኒነት" በዜጎች ዘንድ ጥርጣሬ በሚፈጥር መልኩ፤ ፖለቲከኛ እስረኞችን ለመፍታት የገባውን ቃል ፈጥኖና በምልዓት ያለመፈፀሙ፤ አሁንም ድርጅቱ ይህንን ችግሩን በማያዳግም ሁኔታ ሊቀርፈው መዘጋጀቱን እንደምን መቀበል ይቻላል???

የሚሉ አመክንዮአዊ ተጠየቆችን በማንሳት ድርጅቱ እራሱን በድጋሚ ይመለከትበት ዘንድ ማቅረቡ ተገቢና ምክንያታዊ ይሆናል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፤ ኢህአዴግ እራሱ ልፈታቸው ነው፤ ያላቸውን ፓለቲከኛ እስረኞችን ያለአንዳች ማመንታት በምልዓትና በተግባር ፈፅሞት ቢሆን ኖሮ፤ የተሻለ ሃገራዊ መግባባትን (National consensus) ከመፍጠርና ሐገራዊ የዲሞክራሲ ምህዳሩን ከማስፋት ባለፈ፤ ለኢህአዴግም ለራሱ ቢሆን፥ በሐገር ውስጥም ይሁን በአለም አቀፍ የፓለቲካ መድረክ ላይ ከፍተኛ የፖለቲካ ትርፍ ሊያስገኝለት ይችል የነበረ ከፍተኛ እድል እንደነበር ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነበር።

በርግጥ ይህ እድል ለኢሕአዴግ፥ "ነበር" ተብሎ የሚታለፍ፤ ያመለጠ ወይም የባከነ እድል (Missed opportunity) ነው ተብሎ የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም አሁንም ድርጅቱ ሳይረፍድ መጠቀም ከቻለ፥ በእጁ ላይ የሚገኝ ነውና።

ነገር ግን፥ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ፤ ማንኛውም ነገር የጊዜ ዋጋ (Time value) እንዳለው ነው። ምክንያቱም፥ እድልም ቢሆን በጊዜና በቦታው ካልተጠቀሙበት የሚባክን እንጂ ዘላቂና ዘላለማዊ ሆኖ የሚቆይ ነገር አይደለምና ነው። ይህንን አውነት በአግባቡ መገንዘብ ደግሞ በሳልነትንና አስተዋይነትን ይጠይቃል። እድልን በወቅቱና በጊዜው ያለመጠቀምና የማባከን ተግባር፤ በተለያዩ የአለም የፓለቲካ መድረኮች ላይ ብልሀትና ብስለት በጎደላቸው አያሌ መሪዎችና በርከት ባሉ የፖለቲካ ስርዐቶች ላይ የፈጠረውን ውድቀት መለስ ብሎ ማስተዋሉ ተገቢ ይሆናል።

አብዛኛዎቹ ከእስር ተፈቺዎች ሲናገሩ እንደሚደመጠው ከተፈቱት አንፃር ያልተፈቱት ፓለቲከኛ እስረኞች ቁጥር በእጅጉ እንደሚልቅ ነው። ስለሆነም ኢህአዴግ ቀሪዎቹንም ፓለቲከኛ እስረኞች ፥የተፈቱት በተፈቱት አግባብ ዛሬ፥ ነገ ሳይባልና ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ቢፈታ ለሐገራዊ መግባባት የሚኖረው ፋይዳ እጅግ ከፍ ያለ ይሆኖል ።

ይህን ማድረግ ከተሳነው ግን መንግስቱ በህዝብ ዘንድ የሚኖረውን ታዕማኒነት በእጅጉ ጥያቄ ውስጥ የሚከተው እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። በተጨማሪም የመንግሥትን ሀገር የመምራት ብቃት አጠያያቂ የሚያደርግና በራሱ ውሳኔ አመድ አፋሽ የሚያደርገው መሆኑን አመራሩ ልብ ሊለው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል።

ለማጠቃለል ያክል፤ የዚህች ሀገር ፖለቲካ በተለይም በአሁኑ ወቅት ፍፁም ተገማች (predictable) እየሆነ አይደለም። በአጭር ጊዜ ውስጥ እንኳን በርካታ ፓለቲካዊ ኹነቶች ተከስተዋል። ለምሳሌ የሐገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርም በገዛ ፍቃዳቸዉ ከስልጣን መንበራቸው በራሳቸው ፈቃድ ለመልቀቅ ጥያቄ ማቅረባቸውን በራሳቸው አንደበት አስታውቀዋል፥ ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅም የራሳቸውን ከስልጣን መልቀቅ ተከትሎ በሐገሪቱ ታውጇል። ነገ ደግሞ የሚሆነው አይታወቅም።

ይህ ሁሉ እንግዲህ የሚያመላክተው በአሁኑ ሰዓት በሐገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ላይ፥ ከምክንያታዊነት ይልቅ ግብታዊነት፤ ከዘላቂ ሐገራዊ የመፍትሔ እርምጃዎች ይልቅ ደራሽና የእሳት ማጥፋት ውሳኔዎች እንዲሁም ከፖለቲካዊና ሳይንሳዊ ሐገር የማስተዳደር የቅደምተከተል እርምጃዎች ይልቅ የፖለቲካ ስርዐቱ ተገማችና (predictable) ታዕማኒ (credible) ያለመሆን አዝማሚያ መስፈኑን የሚያሳይ ሁኔታ መኖሩን ነው።

ለማንኛውም በጎውን ያምጣልን።

የመንግሥት
የመልካም
አስተዳደር ችግር
መንሰራፋት ጉዳይ፥
እስኪያቅለሸልሸንና እጅ
እጅ እስኪለን ድረስ
ዘለግ ላሉ ዓመታት
ሲለፈፍልንና ስንሰማው
የቆየ፥ አሁንም እንደ
ብሔራዊ መዝሙር በነጋ
በጠባ ቁጥር እየሰማነው
የቀጠለ ጉዳይ ነው...





በተረፈ ወርቁ

# ክብር ለዐድዋ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን፣ ክብር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት!

እ.ኤ.አ. በ1953 በለንደን ከተማ በቅኝ ግዛት ስር ኾነው ይማቅቁ ለነበሩ ጥቁር ሕዝቦች ነጻነታቸውን ይቀዳጁ ዘንድ ለመመካከር የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች፣ ምሁራንና የፓን አፍሪካኒስት ፅንሰ ሐሳብ አቀንቃኞች የተሳተፉበት ትልቅ ስብሰባ ተካሂዶ ነበር። በዚህ የፓን አፍሪካ እንቅስቃሴ ስብሰባ ላይም የአፍሪካና ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት የተስፋ ምድርና ተምሳሌት የሆነች ሀገራችን ኢትዮጵያ በእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ልብና ሕሊና ውስጥ ከፍ ያለ ክብርና ስፍራ ተሰጥቶአት ነበር።

በወቅቱ በሀገረ ጋና ይታተም የነበር አንድ ጋዜጣ ከ70 ዓመታት ገደማ በፊት የተካሄደውን የዚህ ታሪካዊ ስብሰባ ድባብ እንዲህ ቃኝቶት ነበር። ለዚህ ጽሑፌ መግቢያ ይሆነኝ ዘንድ በጥቂቱ ለመቀንጨብ ወደድኹ። አፍሪካውያን ለነጻነታቸውና ለመብታቸው በአንድነት በከተሙበት የስብሰባ አዳራሽ ግድግዳው ከጥግ እስከ ጥግ የኢትዮጵያ ሰንደቀ ዓላማ በሆነው በአረንጓዴው፣ ቢጫውና ቀዩ ሰንደቀ ቀለማት ተውቧል። በአዳራሹ መድረክ አራት ማዕዘን አቅጣጫም በወርቃማ ዘንጎች፣ የብቸኛዋ ነጻ ጥቁርና አፍሪካዊት ሀገር ሰንደቀ ዓላማ በክብር ሲውለበለብ ይታያል።

ስብሳባውን ሲመራ የነበረው የዌስት ኢንደስ ተወላጅና የዓለም አቀፍ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ንቅናቄ መሪ የኾነው ጆርጅ ፓድሞን ነበር። ፓድሞን ተሰብሳቢዎች ወደ አዳራሹ እንዲገቡ ጥሪውን አስተላለፈ። ‹‹የማኡ ማኡ›› የነጻነት ንቅናቄ መሪ የኾነው ፓን አፍሪካኒስቱ ጆሞ ኬንያታ በግንባራቸው ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቀ ዓላማ አስረው፣ በደረታቸውም ላይ የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ምስል ፒን አድርገው ገቡ።

በመቀጠልም የጋናው የነጻነት ዐርበኛ ዶ/ር ክዋሜ ንክሩማ ከላይ እስከ ታች በኢትዮጵያ ሰንደቀ ዓላማ ልብስ አሸብርቀው ወደስብሰባው አዳራሽ ዘለቁ። ሌሎች የአፍሪካ አገሮች የነጻነት ታጋዮችና ዐርበኞች በአፍሪካዊ ባህልና ወግ የተሠራ ልብሳቸው ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቀ ዓላማ ሰክተው፣ ግማሾቹ ከካርቢያንና ከደቡብ አፍሪካ የመጡ የነጻነት ፋኖዎችና ዐርበኞች ደግሞ በእጃቸው የኢትዮጵያን ሰንደቀ ዓላማ እያውለበለቡ ነበር ወደስብሰባው አዳራሽ የታደሙት። በሁሉም ተሰብሳቢዎቹ ፊት ላይ የኢትዮጵያዊነት የነጻነት ተጋድሎ፣ የአይበገሬነትና የጽናት መንፈስ ይነበብባቸው ነበር።

በዚህ ስብሰባ ላይም የዐፄ ምኒልክ ስምና የዐድዋው አንጸባራቂ ድል በስብሰባው ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ይነሣ ነበር። የዚህን የዛሬ 70 ዓመታት ገደማ በፊት በኢትዮጵያዊነት የነጻነትና የአይበገሬነት ሕያው መንፈስ የተደረገን ታላቅ ስብሰባ በሕሊናችን እያመላለስን እስቲ ጥቂት ስለዓድዋ ድል አብረን እንቆዝም።

ጥቁር ሕዝቦች ለነጻነታቸውና ለክብራቸው ያደረጉትና ታሪክ በክብር መዝገብ ያሰፈረው ምክክር ካለፈ እነሆ ስድሳ ዓመታትን አስቆጥሯል። ዛሬ አፍሪካና አፍሪካውያን ሲጓጉለት የነበረውን ነጻነታቸውን ከተጎናጸፉ በርካታ ዓመታትን አስቆጥረዋል። ግና አፍሪካና ሕዝቦቿ የተጎናጸፉት ይህ ነጻነታቸው እንዲህ እንደ ዋዛ፣ በቀልድ የተገኘ እንዳልነበረ ለማንኛችንም ግልጽ ነው።

ጥቁር ሕዝቦች ለአፍሪካዊ ማንነታቸው፣ ታሪካቸው፣ ቅርሳቸው፣ ነጻነታቸውና ሉዓላዊነታቸው መከበርና ዕውን መኾን የአኅጉሪቷ እልፍ ልጆቿ ደም እንደ ጅረት ፈሷል፣ አጥንታቸውም ተከስክሷል። አፍሪካውያንና መላው ጥቁር ሕዝብ በስስትና በናፍቆት የሚያስቡትና የሚያዩት አረንጓዴው፣ ቢጫውና ቀዩ ሰንደቀ ዓላማችን፣ በጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ክቡር ደም መሥዋዕትነትና አጥንታቸው መከስከስ ያሸበረቀና ያንጸባረቀ ነው። ተወዳጇ ከያኒ እጅጋየሁ ሽባባው/ጂጂ ‹‹ዓድዋ›› በሚለው ተወዳጅና ድንቅ ዜማዋ እንዲህ ብላ እንዳጎራጎረችው፦

‹‹… የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነጻነት፣
ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት።
ስንት ወገን ወደቀ፣ በነጻነት ምድር፣
ትናገር ዓድዋ፣ ትናገር አገሬ
እንዴት እንደቆመኩኝ ከፊታቻሁ ዛሬ።
ዐድዋ ዛሬ ነው ዐድዋ ትንናት…››

ይህ ዛሬ በነጻነት የቆምንባት ምድር በብዙዎች፣ በእልፎች ክቡር ደም መሥዋዕትነት የጸናች መኾኑን ለአፍታ እንኳን ልንዘነጋው አይገባም። በዛ ጥቁር መኾን እንደ ወንጀልና ክኽደት በተቆጠረበት አስከፊ ዘመን፣ ለጥቁር ሕዝቦች ከእንስሳ ያነሰ ክብር እንኳን በተነፈገበት የአፍሪካችን የጨለማና እንደ መርግ የከበደ የመከራ ዘመኗ፣ አፍሪካውያን የሰው ልጅ ሕሊና ሊሸከመው የማይችል ውርደትና መከራን አሳልፈዋል። ለዘመናት በእንዲህ ዓይነት ውርደትና መከራ ጀርባዋ ለጎበጠው አፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝብ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ አፍሪካውያንና ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ በናፍቆትና በሰቀቀን የሚያስቧት፣ በዘላለም ቃል ኪዳን በልባቸው ጽላት የተጻፈች፣ የታተመች ከሩቅ አሻግረው የሚያይዋት አፍሪካዊት የነጻነት ቀንዲል/ብርሃን፣ የነጻነታቸውና የሉዓላዊነታቸው የተስፋቸው ምድር ነበረች።

አገራችን ኢትዮጵያን በብዙዎች አፍሪካውያንና በመላው የጥቁር ሕዝብ ዘንድ የነጻነታቸው ተስፋና ብርሃን ተምሳሌት ሆና ከፍ ብላ እንድትታይ ያደረጓት በርካታ ታሪካዊ ሐቆች አሉ። በሺሕ ዘመናት የሚለካው ታሪኳ፣ ጥንታዊና ገናና የኾነ ሥልጣኔዋ፣ ነጻነታቸውን አፍቃሪ ለኾኑ የዓለም ሕዝቦች ተምሳሌት የኾነው የልጆቿ የአይበገሬነት ጽኑ የነጻነት መንፈስ የሚጠቀስ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚነሣው አንጸባራቂው የዓድዋው ድል በግንባር ቀደምትነትና በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው።

ይህ መላው አፍሪካ በባርነት ቀንበር ስር ወድቆ በሚማቅቅበት ዘመን፣ ከምሥራቅ አፍሪካዊቷ፣ ጥንታዊት አገር የተሰማው የድል ብስራት፣ ለአውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች ሊሰሙትና ሊቀበሉት የተናነቃቸው ታላቅ መርዶ ነበር። በ1888 ዓ.ም. ከሮማ ገሥግሦ፣ ቀይ ባሕርን አቋርጦ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት የመጣው ኃይል በጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ብርቱ ክንድ ተመቶ በታላቅ እፍረት ወደመጣበት ተመለሰ። የዓድዋ ድልም በጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ አዲስ የታሪክ ምዕራፍን ከፈተ።

የዚህ ድል ዜማም በዓለም ዙሪያ ሁሉ ከፍ ብሎ ተሰማ። በአውሮፓና በአሜሪካ ያሉ የመገናኛ ብዙኃንም ስለ ድሉ በሰፊው አወሩ፤ የተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶችም ድሉን አስመልክተው በፊት ገጾቻቸው ዘገቡ። ቪቫ ምኒልክ! ቪቫ ጣይቱ! የሚሉ የድል ብስራቶችና ዜናዎች በመላው ዓለም ናኙ። በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በካርቢያንና በጃማይካ በዓድዋው የድል ስሜትና፣ በኢትዮጵያዊነት የነጻነት ተጋድሎ ስሜት የተረገዙ ንቅናቄዎችም ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ዓድዋ የአፍሪካውያንና የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ቀንዲል ኾኖ ደምቆ፣ ፈክቶ አበራ። በባርነትና በቅኝ ግዛት ስር ኾነው የሚማቅቁ አፍሪካውያንና ጥቁር ሕዝቦችም ከዓድዋው ድል በኋላ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማሰማት ጀመሩ።

ሁጊንስና ጃክሰን የተባሉ አውሮፓውያን የታሪክ ምሁራን፣ An Introduction to African Civilizations with Main Currents in Ethiopian History, በሚል ርእስ በጻፉት ዳጎስ ያለ መጽሐፋቸው እንደገለጹትም።

‹‹ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ ሰራዊት በኢጣሊያ ቅኝ ገዢ ኃይሎች ላይ የተጎናጸፉት ድል፣ ጥንታውያኑን ኢትዮጵያውያንን ዘመናት ያስቆጠረ ነጻነታቸውንና ሉዓላዊነታቸውን ዳግም በተግባር ያረጋገጠ ድል ነው።›› በማለት ምስክርነታቸውን ሲሰጡ እንግሊዛዊው የታሪክ ምሁርና ጸሐፊ ጆርጅ በርኬሌይ

ደግሞ፣ ‹‹የዓድዋ ድል ቅኝ ገዢ ተስፋፊ የኾኑ አውሮፓውያን ሕልም ከንቱ ያደረገና ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ዳግመኛ ቆም ብለው እንዲያስቡ ያደረጋቸው አንጸባራቂ፣ ታሪካዊ ድል ነው፡፡›› በማለት ነበር በአድናቆት መንፈስ ተመልቶ ድሉን የገለጸው፡፡

ይህ ታላቁ የዓድዋ ድል የተጻፈለትንና የተባለውን ያህል በስንቶቻችን ልብ ውስጥ ታላቅና ሕያው ኾኖ አለ ቢባል ምላሹ አጠያያቂ ነው የሚኾነው፡፡ በብዙዎቻችን ልብ ውስጥ ዓድዋ ተገቢውን ስፍራና ክብር አግኝቷል ብለን መናገር የምንችል አይመስለኝም፡፡ ‹‹ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም›› እንዲሉም በእኛ ትውልድ አፍሪካውያን የዓድዋ ድል በመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ትግል ንቅናቄ ውስጥ የነበረውን ስፍራና ውለታ በጭራሽ ዘንግተውታል፣ አሊያም ደግሞ ጭራሽኑን አያስቡትም፣ አያውቁትም ማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ያለን ይመስለኛል፡፡

ለዚህ እንደ ትልቅ መሳያ የሚኾነን፣ በአዲሱ የአፍሪካ ኅብረት መሰብሰቢያ ለጋናው ፓን አፍሪካኒስትና የነጻነት ታጋይ የመታሰቢያ ሀውልት በቆመለት ግቢ ውስጥ ለዚህ አፍሪካዊ የነጻነት ታጋይ፣ ለመላው አፍሪካውያንና ጥቁር ሕዝቦች የወኔ ስንቅ ኾኖ ያገለገለው ዓድዋ ምንም መታሰቢያም ኾነ ማስታወሻ አልቆመም፡፡ ይህን ታላቅ የታሪክ ምጸት ራሱ ዶ/ር ንኩርማ ከመቃብር ቀና ብሎ ቢመለከት እኛንም ኾነ አፍሪካውያኑን ወገኖቹን ከልቡ እንደሚታዘበንነው የምገምተው፡፡

ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነትን ቀንዲልና ደወል ለኾነው ለዓድዋና ለዓድዋ ጀግኖች በአፍሪካ ኅብረት ምንም ዓይነት ማስታወሻ አለመኖሩ አያስቆጭም ትላላችሁ፡፡ በኅብረቱ ግቢ መታሰቢያ የቆመለት ፓን አፍሪካኒስቱ ዶ/ር ንኩርማ በሕይወት ዘመኑ ለእርሱና ለሕዝቦቹ የነጻነት ቀንዲል የኾነች ኢትዮጵያ ሁሌም የነጻነት ብርሃን ኾና በልቡ ለዘላለም ታትማ እንደምትኖር ነበር ሲገልጽ የነበረው፡፡ የኢጣሊያ የፋሽስት ወራሪ የዓድዋውን ድል ለመበቀል ከዐርባ ዓመት በኋላ ኢትዮጵያን ወርሮ ሕዝቦቿን በመርዝ ጭስ ሲፈጃቸው፣ ንኩርማ ለከፍተኛ ትምህርት በነበረበት አሜሪካ አገር ኾኖ- እንዴት የአፍሪካና የመላው የጥቁር ሕዝብ የነጻነት ምልክት የኾነች ኢትዮጵያ በፋሽስት መዳፍ ስር ትወድቃለች በሚል ቁጭት፣ ወኔ እና ጥልቅ ኀዘን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን እንባውን ማፍሰሱ ይነገርለታል፡፡

እንዲሁም የኬንያው የነፃነት ታጋይና ዐርበኛ ጆሞ ኬንያታም ለትምህርት እንግሊዝ አገር በነበሩበት ወቅት በዩኒቨርስቲያቸው ቤተ-መጻሕፍት መደርደሪያ ላይ ባገኙት የኢትዮጵያን ታሪክ በሚተርከው መጽሐፍ ውስጥ ያገኙትን የምኒልክን ፎቶ ወደ ደረታቸውና ፊታቸው አስጠግተው በማቀፍ፣ ዐፄ ምኒልክ ለመላው አፍሪካና ለጥቁር ሕዝብ ያበሰሩትን የዓድዋውን የነጻነት ድል ብስራት በማሰብ በስሜት ተውጠው፣ ዓይናቸው በደስታ እንባ መርጠቡ ይጠቀስላቸዋል፡፡

**የዐፄ ምኒልክ ስምና የዐድዋው አንጸባራቂ ድል በስብሰባው ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ይነሣ ነበር፡፡ የዚህን የዛሬ 70 ዓመታት ገደማ በፊት በኢትዮጵያዊነት የነጻነትና የአይበገሬነት ሕያው መንፈስ የተደረገን ታላቅ ስብሰባ በሕሊናችን እያመላለስን እስቲ ጥቂት ስለዓድዋ ድል አብረን እንቆዝም**

ደቡብ አፍሪካዊ የፀረ-አፓርታይድ ታጋይና የሰላም የኖቤል ተሸላሚ የኾነው ማንዴላ በ1950ዎቹ ለወታደራዊ ሥልጠና ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ያለውን ታላቅ ክብርና ስሜት ‹Long Walk to Freedom› በሚል የትግል ሕይወቱን በተረከበት መጽሐፉ እንዲህ ነበር የገለጸው፡፡ ማንዴላ ከሀገሩ ከደቡብ አፍሪካ ተነስቶ በሱዳን ካርቱም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሲመጣ ጥቁር ፓይለትና ጥቁር አስተናጋጆች በማየቱ ትልቅ ደስታ ነበር የተሰማው፡፡

ይህ የኢትዮጵያዊነታችን ኩራት አንድ መገለጫ በኾነው በኢትዮጵያ አየር መንገድ ያየው እውነታ ለዘመናት ‹‹ጥቁር ሕዝብ ከሰው ተራነት ሊያስመድበው የሚችል ምንም ዓይነት መንፈሳዊና ሰብአዊ፣ ማኅበራዊም ኾነ ኢኮኖሚያዊ ባህርይ የለውም፤ እንዲህ ዓይነቱን አእምሮአዊ ብቃትና ከፍተኛ ትምህርት የሚጠይቅን አውሮፕላን የማብረርን ሥራ የጥቁር ሕዝብ አእምሮና ልብ ሊያደርገውና ሊደፍረው ቀርቶ ሊያስበው እንኳን የማይችለው ሥራ ነው፤›› የሚለውን የአፓርታይድን መንግሥት ክፉ የዘረኛ ስብከት ከንቱና ረብ የለሽ መሆኑን ያስረገጠለት አጋጣሚ ነበር፡፡

ማንዴላ በዚህ በአየር መንገዳችን ጥቁር አብራሪዎች/ፓይለቶች የተሰማው ደስታ ልቡን አሙቆት አውሮፕላኑ የሱዳንን ጠረፍ ተሻግሮ የኢትዮጵያ ድንብር ዘልቆ ሲገባ በአውሮፕላኑ መስኮት አሻግሮ የአገራችንን ተራራና ገደል፣ ሸለቆና ሜዳ እያየ በዚህ ተራራና ገደል ነው ኢትዮጵያውያን አውሮፓውያንን፣ ወራሪውን የኢጣሊያ ሰራዊት በታላቅ ወኔና ጽናት ተጋድለው ነጻነታቸውን አስጠብቀው የኖሩት በማለት በአውሮፕላኑ መስኮት ባሻገር ከኢትዮጵያ ተራሮች፣ ሸለቆዎችና ሜዳዎች ጋር በምናብ እንደተጫወተ በዚሁ የሕይወት ታሪኩን በጻፈበት መጽሐፍ በሚገባ ተርኮታል፡፡

የዐድዋ ድል ከአፍሪካና ከመላው የጥቁር ሕዝቦች ባሻገር እንደ ጃፓን ላሉ ሀገራት ሳይቀር የወኔ ስንቅና ብርታት ሆኖአቸው በቅኝ ገዥ አውሮፓውያን ነጭ ሕዝቦች ላይ አንጸባራቂ የሆነ ድል እንደዲያስመዘግቡ አስችሎአቸዋል፡ ፡ በዘመናዊው ዓለም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ያደረገው ዐድዋ ድል - ከማርከስ ጋርቬይ እስከ ኪንግ ማርቲን ሉተር፣ ከኔልሰን ማንዴላ እስከ ታቦ እምቤኪ፣ ከጆሞ ኬንያታ እስከ ዶ/ር ክዋሜ ንኩርማ ድረስ ትልቅ ክብርና ስፍራ የተሰጠው ነው፡፡ በዚህ በእኛ ዘመንና በመጪው ትውልድ መካከልም ዐድዋ ተገቢውን ክብርና ስፍራውን ይዞ እንዲቀጥል ከእያንዳንዳችን ትልቅ የሆነ የቤት ሥራ ይጠበቅብናል፡፡

ላለፉት ጥቂት ዓመታት የዓድዋ ድልን ከፍ ባለ ብሔራዊ ስሜት እንዲዘከርና እንዲከበር እየተደረጉ ያሉ እንቀስቃሴዎችን ታዝበናል፡፡ ከጉዞ ዐድዋ ጀምሮ በታሪካዊቷ የዐድዋ ከተማ የፓን አፍሪካን ዩኒቨርሲቲ ለማቋቋምና እንዲሁም ለታሪክ፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ፍቅርና ክብር ያላቸው ሰዎች በተናጠልና በኅብረት እያደረጉት ያሉት እንቅስቃሴዎች ደስ የሚያሰኙ ናቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታዘብን እንዳለነው ትውልዱ ላለፉት ሃያ ዓመታት ያለ ቅጥ ከተራገበው የብሔር/የዘውግ ትርክትና የመለያየት ድንበር ወጥቶ በይበልጥ የኢትዮጵያዊነት- አንድነቱንና ኅብረቱን በፍቅር በማጥበቅ በሀገሩ፣ በኢትዮጵያዊነቱ፣ በታሪኩና በቅርሱ የሚኮራ ትውልድን እያየን፣ እየታዘብን ነው፡፡

አንድ መገንዘብ ያለብን ነገር ቢኖር ይህ ለአፍሪካና ለጥቁር ሕዝብና በአጠቃላይም ለሰው ልጆች ሁሉ ማንነት፣ የዘመናት ታሪክ፣ ግዙፍ ሥልጣኔ፣ የመንፈስ ኩራትና ልእልና የሆነ ኢትዮጵያዊ ማንነት በብሔር/በጎሳ ወይም በዘር ልዩነት የሚገደብ፣ የሚደበዝዝ፣ የሚኮሰምን ማንነት ሣይሆን ሁሉን የሰው ልጆችን በፍቅር መሸከም የሚችል ሰፊ ልብና ጠንካራ ጫንቃ ያለው ‹ሰው የመሆን› ክብርን የሚያጎናጽፍ ታላቅና ክቡር ማንነት መሆኑን ከሺሕ ዘመናት በፊት በታሪክ፣ በጥበብ፣ በፍልስፍና እውቀት የተራቀቁ የግሪክ ምሁራንና እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ እስከ ቅዱስ ቁርዓን፣ ከሙሴ እስከ ነቢዩ መሐመድ፣ ከኔልሰን ማንዴላ እስከ ዶ/ር ክዋሜ ንኩርማ የመሰከሩለት ሐቅ ነው፡፡

የፀረ-አፓርታይድ ታጋዩ፣ የነጻነት አርበኛው፣ የዓለም የሰላም ኖቤል ተሸላሚው አፍሪካዊው ኔልሰን ሮሂላላ ማንዴላ/ማዲባ ከላይ በጠቀስኩት ‹ሎንግ ዎክ ቱ ፍሪደም› በተባለ መጽሐፋቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለእርሳቸውና ለአፍሪካ ሕዝብ ያለውን ማንነት፣ ታሪክ፣ ሥልጣኔና ቅርስ ያለውን ፋይዳና ትርጓሜ እንዲህ ሲል ነበር የገለጸው፡-

Ethiopia always has a special place in my imagination and the prospect of visiting Ethiopia attracted me more strongly than a trip to France, England, and America combined. I felt I would be visiting my own genesis, unearthing the roots of what made me an African.

ይህ ታላቅ የሆነ ኢትዮጵያዊ ማንነት ለዘመናዊው ዓለም ዳግመኛ በክብር እንዲያበራ ያደረገው ደግሞ ታላቁ የዐድዋ ድል መሆኑን ለአፍታ ያህል እንኳን ልንዘነጋው አይገባም፡፡ የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ታቦ እምቤኪ እ.ኤ.አ. በ2010 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በሰጣቸው ጊዜ ባደረጉት ታሪካዊ ንግግራቸው- ኢትዮጵያዊነትና የዐድዋ ድል ያላቸውን ጥብቅ የሆነ የመንፈስ ቁርኝት፣ ለሀገራቸው ደቡብ አፍሪካና ለመላው አፍሪካ ጥቁር ሕዝብ ያለውን ትልቅ ትርጉም እንዲህ ሲሉ ነው የገለጹት፡-

Fundamental tenets of the Ethiopian movement were self-worth, self-reliance and freedom. These tenets of drew the advocate of Ethiopianism, like a magnet to the growing political movement. The Adowa Victory provided practical expression to Ethiopianism: self-worth, diginity, uniy, confidence, self-reliance, race pride, spirituality and freedom from colonialism.

ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት በኋላም ለአፍሪካ ኅብረት መቋቋም የመሠረት ድንጋይ ያኖረው የዐድዋው ድልን የሚዘክር ትልቅ የጥበብ ሥራ ሊኖር ይገባል፡፡ የዐድዋ ድል በአፍሪካ ደረጃ እንዲከበር የኅብረቱ መቀመጫ በኾነችው አገር በኢትዮጵያ ሰፊ የኾነ እንቅስቃሴና ቅስቀሳ ልናደርግ ይገባል፡፡ በእርግጥም ዓድዋ በኅብረቱ አዳራሽ ቋሚ መዘክርም ሊደረግለት ያስፈልገዋል፡፡ ከአፍሪካ እስከ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ጃማይካና ካረቢያ ብዙዎችን ለነጻነታቸውና ለሰብአዊ መብታቸው ያንቀሳቀሰ ይህ ታላቅና አንጸባራቂ ድል፣ በእኛ ዘመን፣ በእኛ ትውልድ በኢትዮጵያውያንም ኾነ በአፍሪካውያኑ ልብ ውስጥ እንዲህ መዘንጋቱ እጅጉን በጣሙን የሚያስቆጭ ጉዳይ ነው፡፡

በእነ ጆሞ ኬንያታ፣ በንኩርማ፣ በእነ ሴዳር ሴንጎር፣ በሮበርት ሙጋቤ፣ በእነ ኔልሰን ማንዴላና በእልፎች አፍሪካውያን የነጻነት ዐርበኞችና ታጋዮች ልብ ውስጥ የነጻነትን ብርሃን ጎሕ የቀደደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፣ ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የነጻነት ጎሕ የቀደደው የዓድዋ ድል በኢትዮጵያም ኾነ በአፍሪካ በታላቅ ድምቀትና ስሜት ሊከበር፣ ሊዘከር ይገባዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ዓድዋ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ እየተደረገ የሚገኘው እንቅስቃሴም ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩላችን ጥረት ልናደርግ ይገባናል ለማለት እወዳለሁ፡፡

ክብር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት!

ክብር ለዓድዋ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ሁሉ!



# ''ከህዝቡ ጋር ሆነን አገራችንን በጋራ የምናድንበት መስመር ይኖረናል ''

## ማሙሸት አማረ

ግዮን፡- በእስር መቼና የት ነበር የተያዝከው አጋጣሚውን እስኪ ንገረን?

ማሙሸት፡- እኔ ሚያዝያ 20/2008 ዓ.ም ነው የተያዝኩት። ቦታው ሽንኮራ ዮሃንስ ፀበል ላይ ነው የያዙኝ።

ግዮን፡- ሽንኮራ ዮሃንስ ፀበል ላይ መጥተው ነው የያዙህ?

ማሙሸት፡- አዎ።

ግዮን፡- ከዚያ ወዴት ነው የወሰዱህ?

ማሙሸት፡- በቀጥታ ወደ ማዕከላዊ ነው የገባሁት።

ግዮን፡- ማዕከላዊ ከገባ ጀምሮ የነበረህ ቆይታና የምርመራ ሂደቱ እንዴት ነበር?

ማሙሸት፡- ስለማዕከላዊ ምን የማይወራ አለ? ማዕከላዊማ ገና ወደፊት ለሙዚየም ተብሏል። ሙዚየሙ ላይ ታሪካችን ተፅፎ ነው የሚሆነው። ማዕከላዊ የቱ ተነስቶ ስንቱን አውርተን እንዘልቃለን?

ግዮን፡- ከታሪኩ ትንሽ ቀንጭብልን?

ማሙሸት፡- አዎ ማዕከላዊ እንደሚታወቀው ለአራተኛ ጊዜ የገባሁበት ነው። በዚህ ስርአት ምንም የተለወጠ ነገር የለውም። ሁልጊዜም ቢሆን ምድራዊ ሲኦል የመከራ ምንጭ ነው። ማዕከላዊ ማለት ምድራዊ ሲኦል ነው። እጅግ ብዙ መከራ የሚታይበት። የሰው ልጅ እንደ ሰው የማይታይበት። ሰው የሆኑ ሰዎች ወንድሞቻቸውን እህቶቻቸውን አባት እናቶቻቸውን ወገኖቻቸውን እንደ ሰው ሳይቆጥሩ እንደ አውሬ የሚበላበት። የሰው ልጅ ስጋ የሚበላበት የሚቆረጥበት ማለት ነው ማዕከላዊ። እኔም ሌሎች ጓደኞቼም ወገኖቼም እዚያ ውስጥ ብዙ መከራ ታልፎ ነው እዚህ የደረስነው። ስጋችን ወጥቶ ከላይ ያለው ስጋችን ቆስሎ ሽሮ ሰዋዊ ስብዕናችን ተዋርዶ ነው ዛሬ እዚህ ወጥተናል። ማዕከላዊ ደግሞ በቀላሉና በችኮላ የሚገለፅ ቦታ አይደለም።

ግዮን፡- ማዕከላዊ ሙዚየም አደርገዋለሁ እያለ መንግስት ይናገራል። በዚህ ጉዳይ ላይ አንተ ማዕከላዊን በደንብ ስለምታውቀው ምን ትላለህ?

ማሙሸት፡- የማዕከላዊ የጉዳቱ ሰለባዎች በአጠቃላይ በደንብ መልዕክት አስፍረውበት በትክክለኛው ወደ ሙዚየምነት የሚቀየረው እዛው ባሉት ሰዎችና በገዥው አይደለም። በህዝብና በትክክለኛው ለሰው ክብር ባላቸው አካላት የሚፈፅምና ደግሞ ሌላ ማዕከላዊ እንዳይፈጠር የሚደረግበት አሰራር ሲፈጠር ብቻ ነው። ማዕከላዊ ከሰው አዕምሮ ሊጠፋ የሚችለው።

ግዮን፡- የተመሰረተብህ ክስ ምንድን ነበር?

ማሙሸት፡- የተመሰረተብኝ ክስ ሽብር ነው። ሽብር ፈጥረሃል ነው። የሻብያ ተላላኪ የግንቦት ሰባት ተላላኪ ተብዬ ነው። ሰሜን ሸዋ ውስጥ ሁለት የጦር ማሰልጠኛ ከፍቶ ወታደሮችን እያሰለጠነ ያወጣል ነው። የሰለጠኑ ሰዎች የሉም። ያሰለጠንኳቸውም ሰዎች አልቀረቡም። አሰልጣኝም የለም። እኔው አሰልጣኝ። እኔው ጠመንጃ ገዥ። እኔው ጥይት አቅራቢ። እኔው ደግሞ ላኪ። ሁሉም በሆነበት አንዱ ይሄ ነው። ሁለተኛው ጎንደር አካባቢ በሙሉ የተከሰቱትን በጃን አሞራ፣ በሳንጃ፣ በእንቃሽ፣ በጋይንት በአጠቃላይ በወልቃይት፣ በዳባት፣ በአርማጭሆ በጠገዴ ያሉትን እንቅስቃሴዎች በሙሉ መርቷል ነው የተባልኩት። እንዲሁም በባህር ዳርና በኦሮምያ ክልል አንዳንድ ቦታዎች የነበሩትን አመፆችን ሲመራ ነበር ነው የሚለው።

ግዮን፡- ከእስር በኋላ ወደ ፍርድ ቤት ነው የሄዳችሁት። የፍርዱ ቤቱ ሂደቱስ እንዴት ነበር የታዘብከው?

ማሙሸት፡- በመጀመሪያ ደረጃ በአገሪቱ ላይ እኮ ፍርድ ቤት ሲኖር ነው። ህግ ሲኖር ነው። አሁን እኮ እዚህ አገር በአጠቃላይ የሞተው የህግ ስርአቱ ነው። የህግ ስርአቱ ሞቶ ተቀብሯል። ያ ቢኖር ኖሮ ዜጎች መብታቸው ህልውናቸውን አቅማቸውን በፍርድ ቤት በህግ ፊት እኮ ማስከበር ይችሉ ነበር። ፍርድ ቤት ብትሄዱ በአጠቃላይ ተመርጠው የተቀመጡት ዳኞች የስርአቱ ሰዎች ናቸው። ዳኛ የለም። ዳኛው ቢኖር ኖሮ ለምሳሌ የኔ ክስ አንድ ቀን እንኳ ልታሰርበት የምችልበት ጉዳይ አልነበረም። ምክንያቱም ያንን አንድ ሰው ብቻውን ሊያደርግ ይችላል ወይ ተብሎ ቢታሰብ አዕምሮ ያለው ሰው ሊያየው የሚችለው ጉዳይ ነው። አንድ ደህንነት ዝም ብሎ ፅፎ የሰጠውን ብቻ የሚቀበል ዳኛ ነው ያለው። የሰው ማስረጃ የለም የሰነድ ማስረጃ የለም ይህ በሌለበት ነው ዳኛ የሚፈርደው ህግና ህግ የሚያስፈፅሙ ሰዎች ባለመኖራቸው ስታናግራቸው አይሰሙህም።

ግዮን፡- በእስር ቤት የተፈታከው የክስ ሂደትህ ተቋርጦ ነው ወይስ ተወስኖ ነው?

ማሙሸት፡- ክሴ ተቋርጦ ነው የወጣሁት።

ግዮን፡- አንተ ላይ የነበረው አስቸጋሪ የፖለቲካ ፈተና ቤተሰቦችህንም ችግር ላይ መጣሉ አይቀሬ ነው። በቤተሰብህ ላይ የነበረው ፈተና ምን ይመስል ነበር?

ማሙሸት፡- እንግዲህ እንደሚታወቀው ቤተሰቦቼ ለጥየቃ ሲመጡ በከፍተኛ ሁኔታ ነው የሚፈተሹት ከባድ እንግልት ነው የደረሰባቸው። ከታናሽ ወንድሜ ጋር አብረው ነው ያሰሩኝ። ማዕከላዊ አራት ወር ከወንድሜ ጋር ታስረናል። የእኔን ህመም እየተከታተለ ሳለ ከፀበል ቦታ ወንድሜንም አብረው ነው ያሰሩት። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እህቶቼን ሁሉ ከፊት ጊዜ ጀምሮ ስለሚታወቁ ክትትሉ ከባድ ነበር የነበረው።

ግዮን፡- አንተ እንግዲህ በፖለቲካ ውስጥ ነው ያለኸው። ታናሽ ወንድምህም በፖለቲካው ውስጥ ነው ያለው?

ማሙሸት፡- በጭራሽ። ከእኔ ጋር እኔን ሊያስታምም አብሮኝ ስለነበረ ነው እንጂ። በዚህ 27 አመት ውስጥ ምንም አይነት የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ፈፅሞ አልነበረም። እሱ የግል ስራ ነው የሚሰራው። ከእኔ ጋር ስለተገኘ ብቻ አራት ወር ሙሉ በእሱ ላይ በቤተሰቦቹ ላይ ምርመራው ተጧጡፎ ምንም ነገር ሲያጡ 4 ወር ታስሮ ነው እንደእኔው መከራውን አይቶ የወጣው። እጅግ ብዙ መከራ ነው ያደረሱበት።

ግዮን፡- ማሙሸት እድሜውን ሙሉ በፖለቲካ ትግል ውስጥ አሳልፈሃል ማለት ይቻላል። በተለይ በዚህ ስርአት ውስጥ ያሳለፍከው የፖለቲካ ህይወት ስታስበው ምን ይሰማሃል?

ማሙሸት፡- በአጠቃላይ 27 አመት ሙሉ ነው በዚህ መንግስት መከራ ያየሁት። ለ12ኛ ጊዜ ነው የታሰርኩት። የደረሰብኝ መከራ እጅግ በጣም ከባድ ነው። እኔም ቤተሰቤንም ጓደኞቼንም አጠቃላይ ደግሞ የምታገልላትን አገሬን ነው መከራ ግፍና ሰቆቃ ሲያደርሱ የኖሩት።

ግዮን፡- እስር ቤት በነበርክባቸው አመታት እንዴት ነበር ጊዜህን የምታሳልፈው? ውጪ ያሉትን መረጃዎች የማግኘት እድሉ ነበረህ ወይ?

ማሙሸት፡- መረጃ ለማግኘት በጣም እቸገራለሁ። እንደማንኛውም እስረኛ እስር ቤት ውስጥ ካሉት እስረኞች ጋር እግባባለሁ። የኦሮሞ ወጣቶችና የአማራ ወጣቶች ናቸው እዚያ ውስጥ

ያሉት። ሌላ ብዙ እስረኛ አታገኝም። ስለዚህ ከነሱ ጋር ልብ ለልብ እንግባባለን። እናወራለን። መፅሐፍ እናነባለን። አንዳንዴ እየከለከሉን እየተደበቅንም ስፖርት ጠዋት ጠዋት እየሰራን ከእነሱ ጋር ነው አሳልፍ የነበረው። በውጪ ያሉትንም የሚዳረጉ እንቅስቃሴዎች አልፎ አልፎ ከሚጠይቁት ሰዎች አገራችን ያለችበትን ሁኔታ እንሰማ ነበር።

**ግዮን፡- የእናንተ ከእስር ቤት መፈታት የፖለቲካ ምህዳሩን ያሰፋል ብለህ ታስባለህ? የተሻለ ነገር ይታያል ብለህ ትጠብቃለህ?**

ማሙሸት፡- እንዴ... ይሄማ እንዳይሆን ገና ከእስር ቤት እንደወጣን አስቸኳይ አዋጅ ብለው ኮማንድ ፖስት አወጁብን። አሁን ከዚህ የወጣው ሃይል አንደኛ አቅም ያላቸው ወጣቶች አሉበት፣ በጣም ጎበዞች አሉ። የምወዳቸው ለህዝቡ ብዙ ዋጋ የከፈሉ ለአገር መስዋዕት ለመሆን የተዘጋጁ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ወጥተው ተሰባስበው የአገራችንን እጣ ፈንታ በጋራ ቁጭ ብለን እንዳንወያይ እንዳንነጋገር እኮ ሌላ መሰናክል ከፊታችን አምጥተው ደቀኑብን። የፖለቲካ ምህዳሩ የሚሰፋ ቢሆን ኖሮ አሁን ከእስር የወጣውን ሃይል ያልተፈታውን ሃይል ፈትቶ አጠቃላይ አገራዊ እውነተኛ የሆነ እርቅ ተፈጥሮ ፖለቲካዊ መግባባት ሲፈጠር ነው የፖለቲካ ምህዳሩ ሰፍቷል የምንለው።

**ግዮን፡- ከዚህ በኋላ በነበረህ የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ነው የምትቀጥለው? ምንድነው ቀጣይ አቋምህ?**

ማሙሸት፡- እኔ እንግዲህ ዞሮ ዞሮ የዚች አገር ጣጣ እንዲህ በቀላሉ ገሸሽ የሚደረግ አይደለም። የግል ኑሮየን ልኑር ብል አገር አለ። ይህች አገር የሁላችንም ናት። ይህች አገር አሁን አደጋ ላይ ነች። ይህን አደጋዋን ለማክሰም ከሌሎች አካላት ጋር ተባብሮ መስራት ይኖርበታል። እንግዲህ ድካሙ አለ የቤተሰብ መጎዳት አለ። ደግሞ የራስ አካል ህመምና ጉስቁልና አለ። አዕምሮህ ተጎድቷል። በብዙ ነገር ጉዳት አለ። ይችን አገር ለማን ተትቶ ነው ልረፍ የሚባለው።

**ግዮን፡- እንዲህ ከሆነ በየትኛው የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ እንጠብቅህ?**

ማሙሸት፡- እኔ አሁን ገና በዚህ ፖለቲካ ውስጥ እሳተፋለሁ ወይም እንግዲህ ካሁን በኋላ የግል ኑሮዬን ልኑር የሚለውን ገና አልወሰንኩም። ሁላችንም ያለንን አቅም አስተባብረን እንደው አገራችን አንድ መስመር ላይ እንደ አገር ቆማ ባያት ደስ ይለኛል። መተባበር አለብን ወደፊት በጋራ መስራት አለብን ይህን ገና አይቼ ነው ወደፊት የምወስነው። ከማን ጋር ነው የምታገለው የሚለውን ማየት አለብኝ። እንደምታውቀው የፖለቲካ ፓርቲዎችን እየተዘጉ ለአንዳንድ ግለሰብ እየተሰጡ እነሱም እንዳሉት የፖለቲካ ማህደሩን አጥበነዋል። ተቃዋሚዎችን በድለናቸዋል። እንዳሉት ሁሉ ይሄን አውቀው ፓርቲዎችን ወደነበሩበት እንዲመለሱና ለአገርና ለህዝብ ያበረከትነው አስተዋፅኦ እንደቁምነገር ተቆጥሮ የሚታሰብ ከሆነ ያለንን አቅም አሟጠን አገራችንን ብናድን ደስታውን አልችለውም። ግን...

**ግዮን፡- ግን ምን?**

ማሙሸት፡- ግን የት ሄደን ነው ይህን የምናደርገው? ለነማን ነው የተሰጠው ፓርቲዎቹ ውስጥ እነማን ናቸው? ምንድነው እየተሰራ ያለው? እውነት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እየተነጋገርኩ የሚለው ምን ያህል ሀቅ አለው? እውነት ከፓርቲዎች ጋር እየተነጋገረ ነው ያለው ወይስ ከግለሰቦች ጋር ነው? እነዚህ ሰዎች ህዝቡ የተቀበላቸው ናቸው? ህግና ስርአቱን መሰረት አድርገው የመጡ ናቸው? የሚለው አስተሳሰብ ሁሉ መፈተሽ ይገባዋል። እነዚህ ሰዎች ወደ አዕምሮአቸው ተመልሰው በአገራችን ጉዳይ ላይ ሁላችንም የየአቅማችንን ብናበረክት ጥሩ ነው።

**ግዮን፡- ይህ ካልሆነስ ምን አማራጭ አለ?**

ማሙሸት፡- ይህ ካልሆነ ደግሞ ህዝቡ ከፈቀደ ከህዝቡ ጋር ሆነን አገራችንን በጋራ የምናድንበት መስመር ይኖረናል ማለት ነው።

**ግዮን፡- ከእስር እንደምትወጣ ሲነገርህ ምን ተሰማህ? ኢህአዲግ የፖለቲካ እስረኞችን እፈታለሁ ሲል አምነህ ነበር?**

ማሙሸት፡- አይ እኔ ይሄን ስርአት በምንም አይነት መንገድ አላምነውም። ለምን ብትለኝ የሚናገሩትንና የሚያደርጉትን አያውቁም። ምክንያቱም አንድ መቶ ሚሊየን የሚያክል ህዝብ እመራለሁ የሚል ጠቅላይ ሚኒስተር በ27 አመት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እነዚህን ሁሉ የፖለቲካ እስረኞች እፈታለሁ ካለ በኋላ አንደኛው ደግም ተነስቶ የፖለቲካ እስረኛ የሚባል የለንም ይሄ ሊሆን አይችልም ብሎ እንደገና ሌላ መስፈርትና መመዘኛ ሲያወጣ ስታይ አያስገርምም?

**ግዮን፡- ምንድን ነበር የእናንተ እሳቤ?**

ማሙሸት፡- እኛ አስበን የነበረው ምንድነው ሃገራዊ እርቅ ሊፈጠር ነው። የህዝቡ ጫና የአለም አቀፍ አካላት ጫና አለ። በተጨማሪም ራሱ ገዢው እርስ በርስ መተረማመስ አገሪቱን ለመምራት የሚያስችላቸው አቅም ቁመና ያለመኖር። ጋር ተዳምሮ የህዝባችን ትግል መስዋዕትነት ለዚህ እንዳበቃን ነው የተረዳነው። የነሱ በጎነትመልካምነት ይሄንን ያመጣል ብዬ አላስብም። ለብዙ አመታት አውቃቸዋለሁ። የተናገሩት ነገር የማይፈፅሙ ማድረግ የማይፈልጉ እጅግም ሲበዛ ቂመኞች ናቸው። በቂም ላይ ነው ብዙው ነገር የመሰረቱት ከጥቅማቸዉ ጋር እንጂ ከህዝቡ ፍላጎትና ስሜት ጋር አዋህደው የሰሩበት ዘመን እኔ አላውቅም።

**ግዮን፡- ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከእስር ስትወጣ የነበረውን አቀባበል የተሰማህን ስሜት ግለፅልኝ?**

ማሙሸት፡- ከዚህ በፊት ህዝቡ አማራጭና አቅም ስላነሰው ነው እንጂ። ማን እንዲመራው እንደሚፈልግ ማን እንደሚያደራጀው ማን ከፊት ሆኖ እንደሚቆምለት ያውቃል። ስለዚህ ከአቅማቸው በላይ ሆኖ እኛን ለመንከባከብ ሃሳባችንን ደግፎ ለመሄድ የአደረጃጀት ሁኔታ ህዝቡንም በቋንቋ በብሄር ለያይተው ስለነበር ይሄ አቅሙን አሳንሶት ነበር። ለዛም ነው በወቅቱ እኛን ለመጠየቅ ለመደገፍ ወደኋላ ሲል የነበረው። አሁን ግን ህዝቡ ነቅቷል። ወደጋራ አላማና አስተሳሰብ እየመጣ ነው። “ኢትዮጵያ” የሚለው አስተሳሰብ አሁን ጎላ እያለ እየተሰማ ይመስለኛል። በተለይም ደግሞ በአማራውና በኦሮሞው ህዝብ መካከልም የተፈጠረው መግባባት የተሻለ አገራዊ አጀንዳ ይመስለኛል። በዚህ ምክንያት ህዝቡ ለኛ የነበረው አቀባበል በጣም ደስ ይላል።እኛማ ያው ትንሽ ቤተሰብም ስላሉን ይመጡ ነበር ጓደኞቻችን በአገር ውስጥም በአገር ውጪም ይንገላቱልን ነበር። አሁን ያለውን አቀባበሉንም ስታየው እጅግ ብጣም ደስ ይልሃል ጥሩ ነው። ለካ ወገንም አለን እውነትም ህዝቡ አልረሳንም ለካ የሚል ነገር አለ።

**ግዮን፡- አሁን ያለው ትግል ቢስተካከል ቢያሻሽለው የምትለው ነገር ምንድን ነው?**

ማሙሸት፡- የተበተነ ቤተሰብ ይኖራል ያን የተበተነ ማን ሲከታተለው ቆየ? ማን ሲደግፈው ቆየ? በውስጥ የነበረብንን ችግር እንዴት አሳለፍነው? እንዴት ተፈታ? ከኛ በባሰ ደግም ቤተሰብ የማይጠይቃቸው፣ ፓንትና ሲልፐር መቀየሪያ የሌላቸው አንድ ቀን እንኳ አይዟችሁ የሚላቸው ሰው የሌላቸው፣ ስማቸው ያልተነሳ፣ ያልተዘመረላቸው የከፈሉት ዋጋ ያልተቆጠረላቸው ሰዎች እነሱ ናቸው የሚያሳዝኑኝ። ይሄ ቢስተካከል ደስ ይለኛል። በአንድ በኩል የታሳሪ ቤተሰቦችን የመርዳት እጥረት አይዟችሁ የሚል ቢኖር ደግም የበለጠ ጥሩ ነበር። የአቅምም ጉዳይ ነው። ፍርሃቱም ነው። አንድ አለመሆኑም ነው። በዚህ ዙሪያ ላይ ወቀሳም አላበዛም ግን ዞሮ ዞሮ ሕዝባችን አዕምሮው ያለው ሁሌም እስር ቤት ውስጥ መሆኑን ያየሁበት አቀባበል ነው።

**ግዮን፡- በምህረትና ክስ በማቋረጥ ከእስር በመፈታቱ ኢህአዲግ ከዚህ ምን ያገኛል? ምን ይጠቀማል ትላለህ?**

ማሙሸት፡- እንግዲህ ከእስር ቤት ውስጥ ያሉ በጥቂቱም ቢሆን መፍታቱ አንደኛ የህዝቡን የልብ ትርታ የህዝቡን ፍቅር እንዲያገኝ ያደርገዋል። ሁለተኛ የተፈታው ሰው አቅም ያለው ሃይል ነው በጉልበት፣ በአዕምሮ፣ በፖለቲካ፣ በተለያየ መንገድ ይሄን ሃይል ብታስበው ጥቅም አለው ትርፍ አለው። ሶስተኛው በተለይም አሁን ሽብርተኛ ተብሎ የተከሰሰው የአማራና የኦሮሞ ህዝብ ስለሆነ 70 ሚልየን ወይም ከ70 በመቶ በላይ የሆነ ህዝብ ወንጅለህና ተጋጭተህ ልማት ማልማት አትችልም፡ ፡ አስኮርፈህና ሽብርተኛ ብለህ እድገት ማምጣት አትችልም። አሁን እየተሄደበት ያለው ጅማሮ ጥሩ ቢሆንም እስር ቤት ገና ገና በጣም ብዙ የዚህን ሃያ ሰላሳ እጥፍ ያልተፈታ ህዝብ በገፍ በቃሊቲ፣ በቂሊንጦ፣ በዝዋይ፣ በማዕከላዊ፣ በሸዋሮቢት በሽብር ስም ብቻ የታሰረ ገና አልተነካም። ትንሽ ሙከራ ነው አሁን የተወሰደው። ገና 1 ፐርሰንት የምትሆን ነች። ይሄ በደንብ ተደርጎ በገቡት ቃል መሰረት ወደ ተግባር መለወጥ አለባቸው።

**ግዮን፡- ምናልባት መንግስት ሁሉንም ከፈታሁ ጉዳት አለው ብሎ አስቦ ይመስለሃል?**

ማሙሸት፡- ቢፈታ ምንም ጉዳት የሚያመጣ ህዝብ አይደለም። እስር ቤቶች ውስጥ ያለው ህዝብ የበሰለና የሚያገናዝብ በአስተሳሰብ የተሻለ ህዝብ ነው። ሁሉም በአንድ አይነት ክስ ነው የተከሰሰው። አማራ ከሆነ ግንቦት ሰባት ተብሎ ኦሮሞ ከሆነ ኦነግ ነህ ተብሎ ነው የተከሰሰው። ስለዚህ ይህን አሁን ሰው ገደለ ምናምን የሚባለው መንስኤው እኛ ነን ብለዋል ልክ ነው እነሱ ናቸው። በሽብር ብቻ አይደለም በሙስና ሰበብ የታሰሩ አሉ። እውነት እነዚያ ሰዎች የሙስና ሰዎች ናቸው ተብሎ ግን እውነተኛ ህግና ፍትህ ቢኖር ቢታይ አንዳቸውም በዚያ ሊያስከስሳቸው የሚችል ወንጀል የሰራ የለም። እዚያ ውስጥ በሌላ መልኩ በስርቆት ተብለው የታሰሩ ወጣቶች አሉ። ይሄ ሁሉ ወጣት ለምን ሰረቀ ተብሎ ያንን የወጣቱን አስተሳሰብና አቅም ሊፈትሽ የሚችል የህግ ስርትአና የተቋቋመ አካል የለም። የሚበሉት ሲያጡ የሚያድሩበት ሲያጡ ጥቂቶች እንደፈለጋቸው የአገሩን ሀብትና ንብረት ሲፈነጩበት እነዚህ ደግሞ ህይወታቸውን ለማቆየት ያደረጉት ነገር ነው። አጠቃለይ የተሄደበት ሂደት ሁሉ ስህተት ነበር። እነሱ እንዳሉት ደግሞ የሄድንበት በውሸት ሪፖርት ነው ብለዋል። ደህነቱ ፖሊሱ አቃቤ ህግም ፍርድ ቤቱም በለው በአንድ ትንፋሽ ብቻ የሚመራ ስለሆነ የግድ ወንጀለኛ ተብለው እስር ቤት የታጎሩበትን መንገድ ፈትሾ ሁሉንም የሚወጡበትን መንግድ ማመቻቸት የእነሱ ሃላፊነትና ግዴታ ነው። ይሄ ሁሉ ጦስና ጣጣ ስርአቱ በመበላሸቱ የመጣ ጣጣ ነው እንጂ ወጣቶች ስርቆት ነፍስ መግደል ፍላጎታቸው አልነበረም። እስር ቤት ውስጥ ያለው ህዝብ እጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ይሄ ህዝብ ሀብትም ስለሆነ ሊያስቡበት ይገባል።

**ግዮን፡- በእስር ቤት የሚናፍቅህ?**

ማሙሸት፡- እውነተኛ ዳኛ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ውስጥ ተቀምጦ ማየት አገር የሚባል ነገር መኖሩን የማውቀው በትክክል እውነተኛ ዳኛ ብቻ ሳይ ነው

**ግዮን፡- በመጨረሻም የቀረ ነገር ማለት የምትፈልገው ነገር ካለ?**

ማሙሸት፡- እኔ ማለት የምፈልገው እስካሁን ድረስ እስር ቤት በነበርንበት ጊዜ ለእኔም ይሁን ለጓደኞቼና በመላው አገሪቱ ለታሰሩት ብለው በየቦታው ዋጋ ለከፍሉ ህይወታቸው ላለፈው የነፃነት ጎህ መምጣቱ አይቀርምና እግዚአብሄር ነፍሳቸውን በመንግስተ ሰማያት ያኑርልን። በህይወት ኖረው ደግሞ ለእኛ ሲሉ የጮሁትን አካል ያጡትን የደሙትን የቆሰሉትን የተሰቃዩትን ገንዘብ እውቀታቸውን የሰጡትን የደከሙትን ሁሉ በዚህ አጋጣሚ ልባዊ ምስጋናዬን መግለፅ ነው የምፈልገው። እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ አገራችን ከጥፋት ያድንልን ነው የምለው አመሰግናለሁ።

# “ኢህአዴግ ይታረማል ብዬ አላስብም”

ተስፋሚካኤል አበበ (አበበ ቀስቶ)

ግዮን፡- ለእስር የተዳረግክበት ቀን መቼ ነው? ያንን ወቅት ታስታውሰዋለህ? የነበረውን ሁኔታ እስኪ ንገረኝ?

ተስፋሚካኤል፡- መስከረም 11/2004 ዓ.ም ነው የተያዝኩት።

ግዮን፡- ከየት ነበር የወሰዱህ?

ተስፋሚካኤል፡-የወሰዱኝ ኮልፌ መብራት ሃይል ከሚባል አካባቢ ነው።

ግዮን፡- ከዛ በኋላ ወዴት ነበር የሄድከው? ማዕከላዊ ነው?

ተስፋሚካኤል፡- አይደለም። የያዙኝ ሰዎች ፖሊሶች ስላልነበሩ መሽቶም ስለነበር አቅራቢያ ባለ ፖሊስ ጣብያ ውሰጥ ባዶ ክፍል ውስጥ ነው አስገብተውኝ የሄዱት።

ግዮን፡- ማታ ላይ ነው የተያዝከው?

ተስፋሚካኤል፡-አዎ ማታ ነው ከምሽቱ አንድ ሰአት ከሩብ።

ግዮን፡- የፍርድ ቤት ማዘዣ ወረቀት ነበር?

ተስፋሚካኤል፡-የለም።ምንም የለም ፖሊሶችም አይደሉም የያዙኝ ደህንነቶች ናቸው።

ግዮን፡- ደህንነቶች የፍርድ ቤት ወረቀት አልያዙም?

ተስፋሚካኤል፡-አልያዙም። ከዛ በኋላ እየደበደቡ ነው የወሰዱኝ። ሰው ባለበት ከግራ ከቀኝ በመኪና ከበውኝ ልብሴን አውልቀው እየበረበሩ እያለ ታጣቂ ፌዴራሎች መጥተዋል ግን እነሱ ምንም እገዛ አልሰጡም። መኪናውን አጅበው ጣብያ ድረስ ከማድረስ ውጭ።

ግዮን፡- ባዶ ክፍል ውስጥ ቆየህ?

ተስፋሚካኤል፡- ባዶ ክፍል ውስጥ ሁለት ቀን አደርኩና ምርመራ ተካሄደብኝ። ደህንነቶችም መጥተው ምርመራ ተካሄደ። አንዳንዶችም መቱኝ። ከዛ በኋላ ቅዳሜ ቀን መሳለሚያ የሚገኝ አንድ ፍርድ ቤት ከሌሎች ከተያዙ ከኛ አባላት ጋር ፍርድ ቤት አቀረቡኝ። የ7 ቀን ጊዜ ቀጠሮ ጠየቁ። መስከረም 13 ቅዳሜ ማታ ወደ 1:30 ላይ አዲስ አበባ ፖሊስ ወሰዱኝ።

ግዮን፡- ወደ ፍርድ ቤት የቀረብክ እለት ክሱ ምንድን ነበር የሚለው?

ተስፋሚካኤል፡-ክሱ የሚለው በህገወጥ እንቅስቃሴ ላይ ተገኝተዋል ነው። እኛ ያልነው አንደኛ ሰልፉ ሕጋዊ ነው። ሕጋዊ ለመሆኑ አዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ጥያቄ አቅርበናል። በጥያቄአችን መሠረት አሳውቀናል። ለሰልፉ የሚረዳ እንቅስቃሴ እያደረግን ሳለ ተያዝን።

ግዮን፡- ከእናንተ በኩል ምን መልስ ሰጣችሁ?

ተስፋሚካኤል፡- እኛ ሰላማዊ ሰልፍ ነው የምናካሂደው። ይሄ ደግሞ በሕገ መንግሥቱ የተፈቀደ መብት ነው። ለዚህ ደግሞ የምጠየቅ ከሆነ ኃላፊነት ስለምወስድ አብረውኝ ያሉት ሰዎች እኔ ያዘዝኳቸው ስለሆኑ ሥራውንም የሰጠኋቸው እኔ ስለሆንኩኝ እነሱን ልቀቋቸው። የሚያስጠይቅ ከሆነ እኔ እጠየቃለሁ።በሕግ የሚያስጠይቀን ነገር ስለሌለ ነፃ ነን ብለን ነው የተከራከርነው።

ግዮን፡- ቀነ ቀጠሮ ከሰጧችሁ በኋላ ወዴት ወሰዷችሁ?

ተስፋሚካኤል፡- ቀጠሮ ሰጡንና መስከረም 13



ቅዳሜ ማታ አዲስ አበባ ወሰዱን። አዲስ አበባ እንደገና እንደ አዲስ ሌሊቱን ሲደበድቡኝ ፡ ጆሮዬም ደማ ጉዳት ደረሰብኝ።

ግዮን፡- ያኔ ነው የጆሮ ጉዳቱ የመጣው?

ተስፋሚካኤል፡- አዎ ደብድበውኝ ነበር በሽቦም ሲገርፉኝ ነበር ያን ጊዜ ነው ጆሮዬ የተጎዳው።

ግዮን፡- በእስር ቤት እያለህ የህክምና አገልግሎቱ እንዴት ነበር?

ተስፋሚካኤል፡- ህክምና ማጣት የእስር ቤት ታላቁ ፈተናና ስቃይ ነበር። እውነት እንደ ዜጋ ሕዝብን አስተዳድራለሁ ከሚል መንግሥት የማይጠብቅ በእኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ላይ እየተከሰተ ያየነውና አንድን በፖለቲካ አቋሙ ምክንያት የተያዘን ሰው ለማንበርከክ ህክምና መሰረዝ የህክምና ቀጠሮ ማስተላለፍ ዓመታት ቆይቶ እንደገና ማስጀመር የመሳሰሉት ግፎች ማረሚያ ቤት ውስጥ ይፈፀማሉ። እነኚህ ነገሮች በጣም ያማሉ።ይህ በእኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ላይ ይፈፀማል። በወቅቱ ብታከም በቀላሉ ይድን የነበረው ነገር አሁን ግን ህክምና ሳላገኝ ሶስትና አራት አመት በመቆየቱ ምክንያት የማይድንበት ደረጃ ላይ ደርሶ ዛሬ ቀኝ ጆሮዬ የማይሰማ ሆኗል። ይሄ በጣም ያማል አንድን በፍርድ የታሰረን ሰው የምትቀጣው መብቶቹን በመቀማትና በመገደብ ወይም ሊያገኝ የሚገባውን ከለላ በመንጠቅ አይደለም።

ግዮን፡- ስትያዙ በወቅቱ ስንት ነበራችሁ?

ተስፋሚካኤል፡- አምስት ነበርን። የተለያየ ክፍል ለያይተው አስገቡን። እስከ ሰኞ ድረስ አዲስአበባ ፖሊስ አደርን። አዲስአበባ ፖሊሶች ሰኞ ዕለት በድጋሚ ሌላ ፍርድ ቤት ይዘውን ሄዱ። እዛ ስንሄድ ጉዳዩን በድጋሚ አስረዳናቸው። ሰልፉ ሕጋዊና ሰላማዊ ነው። በሕገ መንግሥቱ የተፈቀደ ነው። አንድ ፓርቲ ይሄን ካልሠራ ዕድር ወይም ዕቁብ አይደለም። ሕዝቡን አደራጅቶ ሃሳቡን በነፃ ገልፆ ወደ ሕዝቡ መንቀሳቀስ ካልቻለ ይሄ በጣም አሳፋሪ ሥርአት ነው ብለን ተከራከርን። ያን ጊዜ ዳኛዋ “ፓርቲው ሕጋዊ ነወይ„? አለች። አዎ ሁለት ፓርቲዎች ነን ሰልፍ የጠራነው ሕጋዊ ነን። ሰላማዊ ትግል ነው የምናካሂደው በምርጫ ቦርዱ የተመዘገብን ነን ብለን መልስ ሰጠናት። ይሄን ጊዜ ዳኛዋ ይሄ ከሆነ ሰልፍ መጥራት መብታቸው ነው አለች። የሚቀጥለው ሐሙሰ በዋስ ይወጣሉ። መርማሪ ፖሊሱንም ሕጋዊ ፓርቲ መሆናቸውን ብቻ አረጋግጠህና ብላ አዘዘችው። አዲስ አበባ ፖሊስ ከተመለስን በኋላ ይሄ እኛን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም አሉና መስከረም 15 ቀን ማዕከላዊ ረታ የሚባል መርማሪ ጋር አስረከቡን።

ግዮን፡- ማዕከላዊ ምን ጠበቃችሁ?

ተስፋሚካኤል፡- ማዕከላዊ ልክ እንደገባን እንደ አዲስ ነው የምትመረመረው። እንደ አዲስ ነው የምትደበደበው። እንደ አዲስ ነው የምትከራከረው። የኔ ክርክር ከላይ እንደገለፅኩልህ የማይቀየር ፅኑ አቋሜ ነው። ሰልፉ ሕጋዊና ሰላማዊ የአገሪቱን ሕገመንግሥት ያከበረ ነው የሚል ነበር።

ግዮን፡- በሁለተኛው ፍርድቤት ስትቀርብ የዋስትና መብትህ እንዲከበር ተወስኖ ነበር። እሱ ተግባራዊ አልሆነልህም?

ተስፋሚካኤል፡- ሐሙስ ምርመራ ነው ብለው ሲያስቃዩን ከረሙና ሐሙስ ዕለት ፍርድ ቤት አለኝ የዋስትና መብቴ ሊከበር ስለሆነ አቅርቡኝ ብዬ ጠየኩኝ። ያን ጊዜ ሐሙስ ከሰአት ፍርድ ቤት ትሄዳላችሁ ብለው አወጡንና አራዳ ፍርድ ቤት በሳምንቱ ውስጥ ሌላ ሶስተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው አዲስ የሽብርተኝነት ክስ መሠረቱብን።

ግዮን፡- ከማዕከላዊ መቼ ሄዳችሁ?

ተስፋሚካኤል፡- ማዕከላዊ መስከረም 15 ገብተን ኅዳር 1 ቀን ቃሊቲ ወረድን። ከፍተኛ ወንጀል ችሎት ጥቅምት 30 ከሰአት በኋላ ቀረብን። ከዛ በኋላ ተመልሰን ስምንታችንም ወደ ማዕከላዊ ገባን። በማግስቱ ከማዕከላዊ ተጭነን ቃሊቲ ገባን።

ግዮን፡- ቃሊቲ በነበረህ ቆይታ ከማን ጋር ነበር የምታሳልፈው?

ተስፋሚካኤል፡- ቃሊቲ መጀመሪያ ከአንዷለም አራጌ ጋር ታንከር ጨለማ ቤት ገባን። እስክንድር እና ደምሰው 6ኛ ላይ ተመደቡ፤ አንዷለም አያሌው ደግሞ አሁን እኛ የነበርንበት ዋይት ሃውስ የሚባል ቤት ሄደ። አምስታችን ግን አንድ ላይ ዞን አንድ ነው በወቅቱ የተመደብነው። እዛ ነው ከህዳር አንድ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ሶስት ቀን ጠዋት ፍርድ ቤት የምንመላለሰው።

ግዮን፡- የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ምን ሆነ?

ተስፋሚካኤል፡- እስከ ሐምሌ 24 ድረስ እዚያ ነበርን። ሐምሌ 24 ከተፈረደብን በኋላ ወዲያው ቂሊንጦ ወረድን። ቂሊንጦ 10 ወር ያህል እንደተቀመጥን ዝዋይ ሄድን። ዝዋይ ሄደን ጨለማ ቤት ነው የገባነው።

ግዮን፡- የፍርድ ውሳኔውን ይግባኝ ለማለት ወይም ሌላ ነገር ለመጠየቅ አልፈለጋችሁም?

ተስፋሚካኤል፡- በመጀመሪያ ፍርዱ ላይ ይግባኝአልነበረኝም። ምክንያቱም የእስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ቀልብሶ የላይኛው ፍርድ ቤት ነፃ ያወጣናል የሚል እምነት ፈፅሞ አልነበረንም።

ሥርዓቱ ከላይ እስከ ታች ተበላሽቷል ብለን እናምናለን። በዛ የተነሳ የይግባኝ ፍላጎት አልነበረንም። ነገር ግን በሙሉ ልብም ባይሆን ወደላይኛው ፍርድ ቤት ሄደን ያመጣነው ለውጥ የለም። ያው ከሽብር ጋር የተያያዘውን ነገር የላይኛው ፍርድ ቤት አፅድቆታል። ይሄ የሆነው ደግሞ ሚያዝያ 24 ነው ከዛ በኋላ ዝዋይ ነው የሄድነው። ዝዋይ ደግሞ የነበርነው ምንም ብርሃን የሌለው ጨለማ ቤት ውስጥ ነው።

**ግዮን፦ እንደምትፈቱና ይቅርታ እንደሚደረግላችሁ የሰማችሁ ጊዜ ምን ተሰማህ?**

ተስፋሚካኤል፦ በግሌ ምንም አልተሰማኝም። ምክንያቱም ኢህአዴግ በብዛት በሚናገራቸውና በሚሰራቸው መካከል ብዙ ጊዜ የሚቃረኑ ነገሮች ስለሚፈፅም እንደ ልማዱ ፕሮፖጋንዳ በመንዛት የሕዝቡን ትኩረት ለመቀየር ወይም ለመዋሸትና ያለውን ትኩሳት ለማብረድ ፈልጎ ይሆናል የሚል እምነት አድሮብኝ ነበር። ሁለተኛ ደግሞ ሳንፈርም ይፈታናል ብዬ አስቤ አላውቅም። ምክንያቱም ኢህአዴግ ሁልጊዜም አሸናፊ መሆን ስለሚፈልግና ሁሉንም አንበርክኮ መግዛት ባሕሪው ስለሆነ ፈርሙ ሲለን እምቢ ስላልን እንወጣለን ብለን አላሰብንም።

ስለዚህም እንደአጋጣሚ ሆኖ ከእስክንድር ጋር እያለን ከመጀመሪያውም ፅኑ አቋም ስለነበረው ይቅርታ ጠይቆ የመውጣት ፍላጎት እንደሌለውና ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ እንዳልነበረ የሚታወቅ በመሆኑ ሳንነጋገር የጋራ አቋም በውስጣችን ስለነበር ያንን በተግባር አድርገናል። በኢህአዴግ ይቅርታና ምህረት ሳይሆን በሕዝቡ ጫና ፤ትግልና መስዋዕትነት ምክንያት መፈታት እንደቻልን ተረድተናል።

**ግዮን፦ አንዳርጋቸው ፅጌስ እናንተ ጋር ነበር?**

ተስፋሚካኤል፦ አንዳርጋቸው ፅጌ ከሁለት ሰዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ነው ያለው። ሁለቱ ሰዎች አሰፋ ንጉሴ እና ዳዊት ድባቤ ይባላሉ፤ ከአንዳርጋቸው ፅጌ ጋር አንድ ላይ በአንድ ክፍል ውስጥ አሉ።

**ግዮን፦ ከእስር መፈታታችሁ ጋር ተያይዞ የፖለቲካው ምህዳር ይሰፋል ትላለህ? ኢህአዴግስ ተለውጧል ብለህ ታስባለህ ?**

ተስፋሚካኤል፦ በግሌ ኢህአዴግን 26 ዓመት ብቻ ሳይሆን ከዛ በፊት ባለው ባሕሪው ነው የምገመግመው። የባሕሪ ለውጥ አምጥቷል ብዬ ፈፅሞ አስቤ አላውቅም፤ አንድም ቀን። ቢለውጥ ኖሮ እስረኛ መፍታት ብቻውን በራሱ ቁምነገርና ስኬት አያደርገውም ነበር። እስረኛ መፍታት አንድ ነገር ሆኖ ዋናው ነገር ግን የፖለቲካ ስነምህዳሩን ለማስፋት የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ከሚሉ በአገር ውስጥም ካሉ በውጪ አገራትም ካሉ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ከሚታገሉትም፤ ነፍጥ አንስተናል ከሚሉት ጋርም መደራደር ነበረበት። ተደራድሮ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ወደ ጠረንጴዛ አምጥቶ ወደፊት ኢትዮጵያ በምን መንገድ ትሂድ? የወደፊቷ ኢትዮጵያ የተሻለ የዴሞክራሲ የፍትህና የእኩልነት ሥርዓት እንዴት ትገንባ? የሚለውን ሁላችንም ተሰብስበን መክረን ዘክረን ማስቀመጥ ይገባን ነበር። ኢህአዴግ ለዚህ ፈቃደኛ አይደለም፤ ለወደፊትም የሚሆን አይመስለኝም።

**ግዮን፦ ስለዚህ እስረኞች የተፈታችሁት ኢህአዴግ ተለውጦ አይደለም እያልክ ነው?**

ተስፋሚካኤል፦ ኢህአዴግ እያደረገ ያለው የማጭበርበር መንገድ ነው። በውስጡ የተፈጠረው መፍረክረክ፣ የፖለቲካና የስልጣን ሽኩቻ ለመሸፈን የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት የፖለቲካ ደመናውን በሌላ አቅጣጫ በማስቀየር ሕዝቡ ስለተፈቱ ሰዎች በማውራት የኢህአዴግን የጥፋት መንገድ እንዲረሳ ለማድረግ ይመስለኛል። አንድ ጊዜ ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች በመፍታት መገላገል ሲችል በየጊዜው እየቆነጠረ በመፍታት ወሬውን አየር ላይ በማጋል አቅጣጫውን ወደዚያ እንዲዞር በማድረግ ሕዝቡ በኢህአዴግ ውስጥ ያለው መበስበስ ተከታትሎ የራሱ እርምጃ እንዳይወስድ እያደረገ ይመስለኛል። ኢህአዴግ ይታረማል ብዬ አላስብም። የውስጥ ችግሩን ለማረሳሳትና ጊዜ ለማግኛ ሊጠቀምበት መሆኑን ነው የምረዳው።

**ግዮን፦ በቀጣይ አንተን በምን እንጠብቅህ? ምንድነው የምታስበው?**

ተስፋሚካኤል፦ እንግዲህ ትግሉ ተጀመረ እንጂ አላለቀም። የተነሣንበት ትግል ከግብ አልደረሰም። ከግብ ያልደረሰን ትግል አውላላ መንገድ ላይ ጥለህ ወዴትም አትሄድም። አንድ ነገር የሚረጋግጥልህ ከትግሉ አልርቅም። አዲስ ፓርቲም የማቋቋም ፍላጎም የለኝም። የኔ እምነት ሁልጊዜም ያሉትን ፓርቲዎች በማጠናከር የተቻለው ሁሉ ተደርጎ አንድ ጠንካራ ፓርቲ ተፈጥሮ አገሪቱ በአስቸኳይ ከኢህአዴግ ጭቆናና የበደል ግፍ እንድትገላገል ማድረግ ነው። ሕዝቡ የሚያምነውም አንድ ጠንካራ ፓርቲ እንዲፈጠር እምነት አለኝ። ካሉት ፓርቲዎች አንዱ ጋር ተቀላቅለህ ትታገላለህ። በቀጣዩ ለሚመጣው ለውጥ መሪ ፓርቲ እንዲኖር የበኩሌን ለመወጣት ዝግጁ ነኝ።

**ግዮን፦ አሁን ያሉት ፓርቲዎች የሕዝብ ቅቡልነት አላቸው ብለህ ታምናለህ?**

ተስፋሚካኤል፦ ‹ሕዝቡ ምን እናድርግ? እነሱኮ ተበጣጥሰው ትናንሾች ሆኑ እኛኮ አማራጭ አጣን ፡፡› እያለ መሆኑን ሊጠይቁን ከሚመጡ ብዙ ሰዎች እየሰማሁኝ ነው። እንደውም አንድ ከሩቅ ቦታ ልትጠይቀኝ የመጣች ሴት ምን አለችኝ "እንደ ሴት ዕድር በየመንደሩ አንድ አንድ ማህተም ይዛችሁ ቀለዳችሁብን" የሚል ነገር ስላለ ይሄን ጉዳይ ለመለወጥ እኔም ብቻ ሳልሆን ታስረው የወጡትም ሆነ ያልታሰሩትም ተነጋግረን አንድ መፍትሔ ማምጣት አለብን። እናንተም ብትሆኑ ጋዜጠኞች ኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ በኋላ በተበጣጠሰ መልኩ ለውጥ ሊመጣ እንደማይችል አሁን እየተካሄደ ያለው ትግል ትምህርት የሰጠ ይመስለኛል። ከዚህ በላይ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ውስጥ ተካሂዶ አያውቅም። ከዳር እስከዳር ህዝቡ እየተነቃነቀ ይገኛል። ግን እኔነኝ የምመራው ተከተሉኝ። ይሄ ነው መንገዱ። የሚል ፓርቲ ባለመኖሩ በቀላሉ ባልተፈለገ መንገድ ትግሎች እየተኮላሹ ነው።

**ግዮን፦ በኢህአዴግ ፓርቲውስጥ እየተካሄደ ያለው የአመራሮች መቀያየር በተለይ አቶ ኃይለማርያም ከጠ/ሚኒስትርነታቸውና ከእናት ድርጅታቸው ደሕዴንየሥልጣን መልቀቂያ ማስገባታቸውን እንዴት ታዘብከው?**

ተስፋሚካኤል፦ ኢሕአዴግ አሁን የሰው ለውጥ በማድረግ ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል እየሞከረ ነው። ስለዚህ አቶ መለስ ዜናዊ በአቶ ኃይለማሪያም መቀየር ለውጥ እንዳላመጣው ሁሉ አቶ ኃይለማሪያምን በዶ/ር አብይ ወይም በአቶ ደመቀ መተካት ቅንጣት ለውጥ አያመጣም። ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው ያለውን ሕግና የጎደለብንን ሕጎች በማቀናጀት የተሻለ ሕጋዊ መደጋገፍ በመፍጠር ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ተሳታፊ ሆነው በነፃ ምርጫ ቦርድ ነፃ ምርጫ ተካሂዶ ሕዝቡ በመረጠው መንግሥት አገራችን ስትተዳደር እንጂ የውስጥ ችግርን ለመፍታት አንድ ሰው በአንድ ሰው ስለቀየርክ የኢትዮጵያን ችግር ይፈታል ብሎ ሕዝቡም እንዳይጠብቅ፤ ለነገሩ ሕዝቡም ጠብቆ አያውቅም። ኢህአዴግም ይህንን ስልት እንደማታለያ ቆጥሮ ለዶ/ር አብይ ሥልጣን ሰጥቶ ኦሮሞ ሥልጣን ያዘ ወይም ለአቶ ደመቀ ሥልጣን ሰጥቶ አማራ ሥልጣን ያዘ የሚል የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ እንዳይጀመር መልዕክቱን አስተላልፋለሁ። ይሄም አያዋጣውም። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን አገሪቱ አደጋ ውስጥ ብትወድቅ ተጠያቂው ኢህአዴግና የኢህዴግ አመራሮች፣ በውስጡ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። አሁን አገሪቱን አደጋ ላይ የሚጥል እንቅስቃሴ የሚታይ ይመስለኛል።

> ...በወቅቱ ብታከም በቀላሉ ይድን የነበረው ነገር አሁን ግን ህክምና ሳላገኝ ሶስትና አራት አመት በመቆየቱ ምክንያት የማይድንበት ደረጃ ላይ ደርሶ ዛሬ ቀኝ ጆሮዬ የማይሰማ ሆኗል...

**ግዮን፦ አብዛኛው የፖለቲካ እስረኞች ከመደበኛው ይልቅ በሽብር ሕጉ ነው የተዳኙት። የሽብርአዋጁን እና ኢህአዴግ እያደረገ ያለውን እንቅስቀሴ እንዴት ትገመግመዋለህ?**

ተስፋሚካኤል፦ ይሄ ሥርአት በሰላማዊ መንገድ ታግለህ መብትህን ለማስከበር ስትንቀሳቀስም ሽብርተኛ ይልሃል። በትጥቅ ትግል ያሉትንም ሽብርተኛ ይሏቸዋል።ነገር ግን በጣም የሚገርምህ ነገር ደቡብ ሱዳን ሄዶ ሳልቫኪርን ከታጣቂዎች ጋር ያደራድራል። እዚህ አገር ታጣቂዎች ሽብርተኛ ከሆኑ እዛም ከሄድን ሳልቫኪር ላይ የሚተኩሱት ታጣቂዎችም ሽብርተኛ ናቸው ማለት ነው።ነገር ግን ለደቡብ ሱዳን ሰላም ታጣቂዎች ከመንግሥት ጋር በደቡብ ሱዳን ጉዳይ ላይ የሚያገባቸው በመሆኑ ሁሉም ወገኖችን አዲስ አበባ እየጠራ የሚያደራድር መንግሥት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያገባናል የሚሉ ኃይሎችን አንዱን መርጦ አንዱን መተው፣ አንዱን ጠልፎ አንዱን መውደድ፣ አንዱን ገፍቶ አንዱን ማቅረብ፣ እንደዚህ አይነት ግራ የሚያጋባ ነገር የሚያራምድ ሥርዓት ስለሆነ ቢያንስ ከደቡብ ሱዳን በላይ ለኢህአዴግ ህልውናም ቢሆን የኢትዮጵያ መኖር ፤ዲሞክራሲያዊ ፍትሃዊ መሆን አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ኢህአዴግ ለረጅም ዓመታት እንገባለሁ ያለውን ሥርወ መንግሥት ሊያጣው ስለሚችል እሱም እንደ አንድ ፓርቲ እንደሚያገባው ሆኖ ተቆጥሮ ተሳታፊ ሆኖ መቀጠል ከፈለገ ከሁሉም ያገባናል የሚሉ ኢትዮጵያዊያን አካላት ጋር መደራደርና ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ የአገሪቱን የፖለቲካ ሥነ-ምህዳር ማስፋት ብቻ ሳይሆን የተደላደለ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ግዮን፦ ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን ታልማለህ?**

ተስፋሚካኤል፦ እስር ቤት የሌለው አገር ወይም መንግሥት የለም። ነገር ግን አንድና ሁለት ሰው ለብቻው የሚታሰርበት የግፍ እስር ቤትና ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ከጓደኞቻቸው ከወዳጆቻቸው ተገልለው ለዓመታት ጨለማ ክፍል ታስረው፣ ከንባብ፣ ከመረጃ ከምንም ነገር ተገልለው፣ የፀሃይ ብርሃን ናፍቋቸው የሚሰቃዩባት አገር ባትሆን፤እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ዜጋ በፖለቲካ አስተሳሰቡና አቋሙ ምክንያት ወደ እስር ቤት የማይገባበት አገር እንድትሆን ሁላችንም የበኩላችንን ጥረት የምናደርግባትን አገር እናፍቃለሁ።

**ግዮን፦ በመጨረሻ እስቲ ቀረ የምትለው ሃሳብ የምታስተላልፈው መልዕክት ካለ?**

ተስፋሚካኤል፦ የህዝቡ ጫና የሕዝብ ትግልና መስዋዕትነት በኅብረት ሆኖ መሪ አግኝቶ ተቀናጅቶ ቢሆን ኖሮ እንኳን እኛን ማስፈታት አገራችንን ነፃ ማውጣት እንደሚችል በተግባር የተረጋገጠበት ጊዜ ስለሆነ ላደረገው ትግልና ለከፈለው መስዋትነት ለሕዝባችን ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ። ሕዝቡ ባደረገው ትግል በመላ ሀገሪቱ ደምን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ውድ ሕይወቱን ሰውቶ ስለኛ ፍትህ ብሎ ጮሆ በገኘው ላይ ጫና አሳድሮ እያስፈታን ስላለ ይሄ ሕዝብ ታላቅ የአክብሮት ምስጋናችንን ይድረሰው።

# «ፖሊስ ባጠፋው ጥፋት፣ ባወደመው ንብረት ልንከሰስ አይገባም ነበር»



አህመዲን ጀበል

አህመዲን ጀበል የ38 ዓመት ጎልማሳ ነው፡፡ የመጀመርያ ዲግሪውን በኬሚስትሪ ሁለተኛ ዲግሪውን ደግሞ በፊሎሎጂ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተቀብሏል፡፡ በርከት ያሉ ሃይማኖታዊ መጽሐፎችን ጽፏል፡፡ «የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የጭቆናና የመከራ ታሪክ» በሚለው መጽሐፉ በየበልጥ ይታወቃል፡፡ በሙስሊም የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ውስጥ በመሳተፉ ለ2030 ቀናት በእስር ቆይቷል፡፡ በእሥር ቆይታውም ሌሎች መጽሐፎችን አዘጋጅቶ ለአንባቢያን አቅረቧል፡፡ አህመዲን ጀበል ሙሐመድ በአሸባሪነት ተከሶና የ22 ዓመታት ጽኑ እሥራት ተፈርዶበት በእሥር ከቆየ በኋላ የካቲት 7 ቀን ከወህኒ የወጣ ሲሆን ከባልደረባችን ሁሴን ከድር ጋር ያደረገውን ቆይታ እነሆ ብለናል፡፡

**የት እና መች ነበር የታሰርከው?**

አህመዲን ጀበል፡- ሐምሌ 13 ቀን 2004 ከአንድ ጓደኛዬ ቤት ነው የተያዝኩት፡፡

**የተከሰስክበት ጉዳይ ምንድነው?**

አህመዲን ጀበል፡- ክሱ ሁለት ነው፡፡ አንደኛው ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል መናድ፣ ሁለተኛው በጸረ-ሽብር አዋጅ 652/2001 አንቀጽ 3 እና 4 የሽብር ወንጀል መፈጸም እና የሽብር ወንጀል ማነሳሳት የሚል ነው፡፡ መንግሥት የሚለው ሐምሌ 6ቀን 2004 የሽብር ወንጀል ተፈጽሟል ነው፡፡ የሽብር ወንጀል የተባለውም አንዳንዱ በዝርዝር ሲገለጽ፡- አንዳንዱ የመንግሥት ወታደሮች ራሳቸው የወሰዱትን ርምጃ የሚያመለክት፣ አንዳንዱ ደግሞ እኛ ከታሠርን በኋላ ሐምሌ 14 ቀን 2004 በኋላ የተፈፀመን ድርጊት የሚያሳይ ነው፡፡

**ክሱን እንዴት ተከላከላችሁት?**

አህመዲን ጀበል፡- በበቂ ተከላክለናል፡፡ በርካታ ምስክሮችን አዘጋጅተን ነበር፡፡ 150 ምስክሮች እንዲደመጡ አድርገናል፡፡ እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ በየመስጅዱ የተናገርነውን በቪዲዮ አቅርበናል፡፡ እነሱ እንደሚከሱት ሳይሆን ከነሱ የሃሰት ውንጀላ ምን ያህል የራቀ እንደሆነ አሳይተናል፡፡ 46 ኦዲዮና ቪዲዮዎችን ፍርድቤት አስገብተናል፡፡ በሰደቃና የአንድነት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊ የነበሩ ክርስቲያን ወገኖቻችን ለምስክርነት መጥተውልናል፡፡ ቀሳውስትና ፓስተሮች የተገኙበት የሰደቃና የአንድነት ፕሮግራሞችን በማሳየት የተናገሩትንና የጻፉትን አስተያየት አቅርበናል፡፡ በየሚዲያው የቀረቡ (የሀገር ውስጥም የውጭም) ቃለ-ምልልሶችን፣ መጽሐፍ ፣ የኮሚቴውን መግለጫ፣ሌሎችንም አቅርበናል፡፡ ገና ክሱ እንደተጀመረ ዳኞች አንዱን ክስ ውድቅ አድርገውታል፡፡ ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የሚለውን ሰርዘው በሽብር ክሱ ተከላከሉ ብለውናል፡፡... ፖሊስ ባጠፋው ጥፋት ባወደመው ንብረት እኛ ልንከሰስ አይገባም ነበር፡፡ ይህን ደግሞ መጅሊስ በጻፈው ደብዳቤ አምኗል፡፡ የከተማ አውቶብስም የሁለቱ ሰዎች ክስም እኛ ከታሰርን በኋላ ተፈጸመ መባሉን ያቀረቧቸው ማስረጃዎችም ምስክሮችም ያረጋገጡት ነው፡፡ ሁለት ዓመት ተኩል ከተከራከርን በኋላ ነው ሐምሌ 27 ቀን 2007 ነው የተፈረደው፡፡ ይግባኝ ስንጠይቅ እንኳ ሙሉ ፋይሉን ማግኘት አልቻልንም፡፡ .....ብቻ ትልቅ ቀልድ ነበር፡፡ በጉዳዩ 14 ዳኛና 14 አቃቤ ሕግ ነው የተፈራረቀበት፡፡ ፍርድ ሲሰጡ ከመጀመርያው ቀን ጀምሮ የነበረ አንድም ዳኛ አልነበረበትም፡፡

**የእስር ቤት ቆይታህ ምን ይመስል ነበር?**

አህመዲን ጀበል፡- እስከ ነሐሴ ሦስት ቀን 2004 ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ ነበር፡፡ ነሐሴ 3 ጨለማ ክፍል አስገቡኝ፡፡ 13 ቀን እዚያ አቆዩኝ፡፡ እጄን ወደላይ አሥረው ለ12 እና 13 ሰዓታት ግርፊያና ማንገላታት ፈጽሙብን፡፡ እንግዲህ ጊዜው ረመዳን የመጨረሻዎቹ 10 ቀናት በይበልጥ ወደ ፈጣሪህ የምትቃረብበት ጊዜ ነው፡፡ እኛ በመከራና ሥቃይ ነበር ያሳለፍነው፡፡ ቤተሰብ እንኳ ማግኘት አልቻልንም ነበር፡፡

**እሥር ቤት ውስጥ አስከፊና የሚያማርር ጊዜ ነበር የምትለው መች ነበር?**

አህመዲን ጀበል፡- እኔ ጨለማ ቤት ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በወንድሞቼ (በእነ አቡበከር) ላይ ይደርስ የነበረው ግፍና መከራ የሚያሳቅቅ ነበር፡፡ የአቡበከር መታመም ሕክምና እንዲያገኝ ሌሊት በር እየደበደብን ስንጮህ ሰሚ ማጣታችን፣ እስልምናን በማንቋሸሽ መርማሪዎች ያደርሱብን የነበረው የሥነልቦና ቀውስ፣ እኛን በማንቋሸሽ ይደርስ የነበረው ስቃይ መቼም የማይረሳ ነው፡፡

**‹‹ምነው እንዲህ ዓይነት ጣጣ ውስጥ ባልገባሁ›› ብለህ አማርረህ ታውቃለህ?**

አህመዲን ጀበል፡- እኔ ከጅምሩ እንደምያዝና ከእሥር በላይ የሆነ ነገርም ሊገጥመኝ እንደሚችል አውቃለሁ፡፡ ከመታሠሬ አንድ ሳምንት በፊት እንደምታሰር ለእናቴም፣ ለአባቴም፣ ለባለቤቴም ነግሬያቸዋለሁ፡፡

**ለምንድነው ከ17 ተከሳሾች አንተ አህመድ ሙስጠፋ፣ሙሐመድ አባተና ኻሊድ እንድትቀሩ የተደረገው?**

አህመዲን ጀበል- የማረሚያ ቤት ደህንነቶች እናቴ እኔን ለመጠየቅ ስትመጣ ‹‹እሱ ከሚፈቱት ይሆን ነበር፡፡ እዚህም ቁጭ ብሎ ሐሳብ አልቀየረም፡፡ ይኸው መጽሐፍ እየጻፈብን ሕዝብን ይቀሰቅሳል፡፡ ወጥቶ ቢሠራ አይሻለውም ወይ? አህመድንም ወጥቶ ቢነግድ አይሻለውም ወይ›› ይሏት ነበር፡፡ ካሳ ተክለ ብርሃንጋ ለሽምግልና ለሄዱ ሰዎችም ‹‹እነዚህ አራቱ ሰዎች ናቸው የቀሰቀሱብን፣ ይሄ ሁሉ ጉዳትም ያደረሱብን፡፡ እነዚህን ፍቱ ብላችሁ አትጠይቁን›› ብሎ የፌዴራል ጉዳይ ሚኒስትር ካሳ ተክለብርሃን ራሱ መናገሩን ሰምተናል፡፡ አንድ ደህንነትም ‹‹ፈርኦን›› የሚለውን መጽሐፌን አንስቶ ‹‹ተመልከቱ ሙስሊሙን በቁርአን፣ ክርስቲያኑን በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ዕምነት የሌላቸውን በጥቅስ እያደረገ እንዴት እንደሚቀሰቅስብን ተመልከቱ፡፡ እስርቤት ሆኖ ብሶበታል፡፡ እንዴት ፍቱት ትሉናላችሁ›› ማለቱን የሰሙት ነግረውናል፡፡

**የተፈታችሁት በምህረት ነው በይቅርታ ነው?**

አህመዲን ጀበል፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ምህረትና ይቅርታ እየተደበላለቁ ነው፡፡ ሐሙስ ዕለት እነአንዱዓለምና እስክንድር በኃማኖት የተከሰሱም ይፈታሉ የሚል ነገር በሚዲያ ሰማን፡፡ በማግስቱ ጁምኣ ሰግደን ስንወጣ ጠሩንና ‹‹እንኳን ደስ አላችሁ መንግሥት ማታ ያለውን ሰምታችኋል፡፡ እናንተም ከሚፈቱት ናችሁና እዚህች ጋር ፈርሙ›› አሉን፡፡ ወረቀቱን ስናይ ርዕሱ ይቅርታ ስለመጠየቅ ይላል፡፡ እኔ እከሌ የተባልኩ ሰው የተከሰስኩበት ወንጀል በማስረጃ ተረጋግጦብኝ ጥፋተኛ መሆኔ ፍርድቤቱ ወስኖ ይህን ያህል ዓመት ፈርዶብኝ እስር ላይ እገኛለሁ፡፡ በመሆኑም የፈጸምኩት ነገር ሥህተት መሆኑን አምኜ... መንግሥትን ይቅርታ እጠይቃለሁ ይላል፡፡ እኛ የፈጸምነውም ስህተት የለም አንፈርምም፡፡ በሕጉም በጸረ-ሽብር የተከሰሰ ይቅርታ መጠየቅ አይችልም አልን፡፡ ትተውን ሄዱ፡፡ ከአንድ ሰዓት በኋላ አዳራሽ ውስጥ ጠሩን፡፡ የፈረመም ያልፈረመም ተራ በተራ ወደ ውጪ ተጠራ፡፡ እኛ አቋም ካልለወጡት ሆንን፡፡ ከሁለት ቀን በኋላ የፈረሙትን ወደስልጠና ወሰዷቸው፡፡ በተፈታንበት ቀን እቃችሁን ይዛችሁ ውጡ ተባልን፡፡ ይዘን ስንወጣ አዳራሽ ውስጥ አስገቡን፡፡ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ዝም ብለን ተቀመጥን፡፡ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ ሰንዳፉ ስልጠና የሄዱ ሰዎች መጡ፡፡ አዳራሽ ውስጥ አንፈርምም ብለን የተቀመጥነው 24 ሰዎች ነበርን፡፡ እስክንድር አንዱአለምና አበበ ቀስቶም አንፈርምም ካሉት ውስጥ ናቸው፡፡ ወደ አዳራሹ ግን አላመጧቸውም፡፡

ከዚያ የማሕደር ማጣርያ አደረጉ፡፡ ሌላ ወረቀት አመጡና እዚህች ፈርሙ አሉን፡፡ አሁንም አንፈርምም አልን፡፡ ከዚያ ትንሽ ቆይተው እንኳን ደስ አላችሁ ፕሬዝዳንቱ ይቅርታ አድርገውላችኋል ውጡ አሉን፡፡ ስንወጣ ያልጠበቅነው ሕዝብ ተሰብስቧል፡፡

**የጅማ ሕዝብ በጉጉት እየጠበቀህ በጸጥታ ምክንያት መሄድ አልቻልክም፡፡ የምስራቅ ሐረርጌ ሕዝብ ግን ሽልማት አድርጎልሃል እስቲ ስለዚህ ሁኔ ንገረኝ?**

አህመዲን ጀበል፡- የሸለሙኝ ኒሳን 2017 ምንም ያልተነዳ አዲስ መኪና ነው፡፡ ያልጠበቅኩትና ያስደነገጠኝ ነበር፡፡ ከሐረር የመጡት ሰዎችና አባገዳ በቀለ ሰንበቶ ‹‹እኛ ፈር ቀዳጅ መሆን አለብን፡፡ ለሕዝብ ጉዳይ የታገሉ ሰዎች የሕዝብን ጉዳይ ጉዳያችን ነው ብለው መስዋትነት ሲከፍሉ አካላቸውን፣ ሕይወታቸውን፣ እድሜያቸውን ሲሰው፤ እኛም ለነሱ ማሰብ አለብን›› ብለው ነበር፡፡ እኔ አህመድ ሙስጠፋ ቤት ምሳ ተጠርቼ ለባብሼ ልወጣ ስል ነው በድንገት የመጡብኝ፡፡ እኔ ፊት ለፊት ስለተናገርኩ እንጂ የተለየ ያደረግኩት ነገር የለም፡፡ በየቦታው ለሕዝብ እየታገሉ የተረሱ ሰዎች አሉ፡፡ ይህንን ሽልማት ሕዝብን በጽሑፍ እንዳገለግልበት ማተሚያ ቤት እንድከፍትበት ላውለው ብላቸው፤ አይቻልም ሽልማታችን እንዲነካብን አንፈልግም፡፡ ማተሚያ ቤቱንም ላልከው ዓላማ እናቋቁማለን አሉኝ፡፡ እጅግ ነው ያስደሰቱኝ፡፡ ለነ ዶክተር መረራ፣በቀለ ገርባም አቅማችን በፈቀደ መጠን እንቀጥላለን፡፡ የሕዝብ ትግል በቅድሚያ አወልያ ስለተጀመረ ነው አንተን ያስቀደምነው ነው ያሉኝ፡፡

**ወደፊት ምን እንጠብቅ?**

አህመዲን ጀበል፡-ከጥቂት ወራት በኋላ የሚወጣ መላው ኢትዮጵያውያን የሚያነቡት መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁና ጠብቁኝ፡፡

# “በግፍ መታሰራችን ትግላችንን የበለጠ አጠናክረን ለመቀጠል ምክንያት ይሆነናል”

ናትናኤል መኮንን

*ግዮን፡- መስከረም 3/2000 ዓ.ም ስትያዝ የነበረውን ሁኔታ እስኪ ግለፅልን?*

ናትናኤል፡- ስያዝ የነበረው ሁኔታ አንድ ሰላማዊ ፖለቲከኛ የሚይዙ ሳይሆን አንድ የሆነ ትልቅ ጄኔራል የሚይዙ ነበር የሚመስለው። የደህንነቶች ብዛት ካሜራው የሠራዊቱ ግርግር ከፍተኛ ነበር።

*ግዮን፡- ከተያዝክ በኋላ ከዛ ወዴት ሔድክ?*

ናትናኤል፡- ቀጥታ ወደ ቤቴ ነበር የወሰዱኝ ፍተሻ ተካሄደ። እቤት ተዘጋጅተው የጠበቁኝ ታዛቢዎች ነበሩ፤ እነሱን አስገቡና ፍተሻ ጀመሩ። ፍተሻው አምስት ሰዓት የፈጀ ነበር። ፍተሻው ሲያልቅ ቀጥታ ወደ ማዕከላዊ ነው የወሰዱኝ።

*ግዮን፡- እስኪ ማዕከላዊ የነበረህን ቆይታና የምርመራ ሂደቱን ግለፅልኝ?*

ናትናኤል፡- ማዕከላዊን ከመጀመሪያው እግሬ ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ ነው ማስፈራሪያው ዛቻው የተጀመረው። በነጋታው ፍርድ ቤት አቀረቡኝ። ከፍርድ ቤት ከተመለስኩበት ቀን ጀምሮ ነው ድብደባና ማሰቃየቱ የተጀመረው። አንድ ሌሊት ብቻ ይመስለኛል ሳይገርፉኝ በሰላም ያደርኩት ። እነሱ የሚፈልጉት ግንቦት ሰባት ነኝ እንድል፣ ከግንቦት ሰባት አመራሮች ጋር በድብቅ እየተገናኘህ ሽብር ለመፍጠር ትንቀሳቀስ ነበር ብለውኛል። እነ ብርሃኑ ነጋን እነ ሙሉነህን እየጠሩ ከነሱ ጋር ግንኙነት አለህ ነው። ይሄን እመን እያሉ ነው ይደበድቡኝና ያሰቃዩኝ የነበረው።

*ግዮን፡- ማዕከላዊ ምን ያህል ጊዜ ቆየህ?*

ናትናኤል፡- እስከ ህዳር አንድ ድረስ እዛ የቆየሁኝ ይመስለኛል ካልተሳሳትኩ። ሳይቤሪያ የሚባለው አካባቢ ብቻዬን አንድ ክፍል ውስጥ ታስሬ ነበር።

*ግዮን፡- ሳይቤሪያ ምንድ ነው?*

ናትናኤል፡- ሳይቤሪያ ማለት በማዕከላዊ ውስጥ የሚገኝ በጣም ቀዝቃዛና እጅግ አደገኛ የሆነ ቦታ ነው። እስከ አስር የሚደርሱ ክፍሎች አሉት። አንደኛው ክፍል ውስጥ ነው የነበርኩት።

*ግዮን፡- በማዕከላዊ በነበርክበት ጊዜ የገጠመህን ችግር እስኪ ግለፅልን?*

ናትናኤል፡- ብዙ ግፍ ተፈፅሞብኛል። ብዙ ስላሰቃዩኝ በራሴ ላይ ምግብ የማቆም እርምጃ እስከመውሰድ ደርሼ ነበር። እነሱ ግን ግድ ሳይሰጣቸው ወደ ምርመራ ክፍላቸው እየወሰዱ ይገርፉኝ ነበር። ስደክምባቸው ሊሞት ይችላል ብለው ተውኝ። እንደገና ሳገግም ድብደባቸውን ቀጠሉ። የነበረው ሁኔታ እጅግ በጣም ዘግናኝና በሕይወት ለመኖር የማያስመኝ ነበር።

*ግዮን፡- ቃሊቲ የነበረህን ቆይታ እስኪ ንገረኝ?*

ናትናኤል፡- ቃሊቲ ከወረድኩኝ በኋላ ከጓደኞቼም ጋር ለያይተው በተለያየ ክፍል ነው ያሰሩን ። ቃሊቲ ውስጥ ጨለማ ቤት የሚባል አለ፤ ብዙ ማጎሪያ ቤቶች አሉ። እነሱ የሚፈልጓቸውን ሰዎች ለይተው የሚያስቀምጡበት ቤቶች ናቸው። የሞራልም ሆነ የሥነ ልቦና ጫና የበለጠ የሚፈጥሩ ናቸው። ከሌላው ጋራ ተቀላቅለን አይደለም የታሰርነው። ስለዚህ “ታንከር” የሚባል ጨለማ ቤት ውስጥ ነው ያስገቡን።

*ግዮን፡- ረጅሙን የእስር ጊዜህን በዝዋይ ነው ያሳለፍከው?*

ናትናኤል፡- አዎ ግን እንደገና ወደ ቃሊቲ ተመልሻለሁ። ከዛ በኋላ ወደ ዝዋይ ወሰዱኝ 3 ዓመት ቆይቻለሁ። በዚህ እስር ቤት ውስጥ የሚፈልጉትም ሰው የሚቀጡበት ክፍሎች አሉ። ዘጠነኛና ስምንተኛ ቤት የሚባሉ ሁለት ክፍሎች ከሌሎች እስረኞች ተነጥለን የታሰርንባቸው ክፍሎች ናቸው። መጀመሪያ ከእነ ተፈራ ማሞ እና ሌሎችም ጀግኖች ጋር ነው የቆየሁት። በማዕከላዊ



ቆይታዬ ወቅት ጆሮዬን ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ ስለነበር ህክምና ጠይቄ ወደ አዲስ አበባ ላኩኝ። በአጋጣሚ ግን ቃሊቲ የተቀበለኝ አስተዳዳሪ የነበረው ሃጎስ የሚባል ሰው ከእኔ ጋር በነበረው የተለየ አለመግባባትና ፀብ አልቀበልም ብሎ ወደ ዝዋይ መለሰኝ ። ወደ ቃሊቲ ለመመለስና ለመታከም ወደ ሁለት ዓመት ፈጅቶብኛል። ዝዋይ ምንም አይነት ህክምና የለም ማለት ይቻላል። ደካማ የህክምና አገልግሎት ነው ያለው። ከሁለት ዓመት በኋላ እንደገና ወደቃሊቲ ለ2ኛ ጊዜ ተላኩ። አጋጣሚ ተቀብለው በፊት የነበርኩበት የቅጣት ቤት “ታንከር” አስገቡኝ። ከዛም ለህክምና ወደ ሆስፒታል ላኩኝ። ተከታታይ ወደ ሶስት ዓመት ያህል ታክሜ አሁን ደህና ነኝ ማለት ይቻላል።

*ግዮን፡- ወደ ፍርድ ቤት ጉዳይ ልመልስህና የክስ አመሰራረቱ የምስክሮች ሁኔታ በአጠቃላይ የፍርድ ሂደቱ ምን ይመስል ነበር?*

ናትናኤል፡- የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የምታውቀው ነው። በማስረጃና ተጨባጭ እውነት ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ የፍርድ ውሳኔ የለም። ይልቁኑ የገዥዎችን ፍላጎትና ትዕዛዝ ለማስፈፀም ነው የቆመው። ስለዚህ መጀመሪያውኑ የፈጠራ ክስ ነበር። እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ወንጀል ይጻፋል ወይም እንደማንኛውም ድርስት ይደረሳል እንጂ ይፈፀማል ይሰራል ብዬ አላምንም። የፈጠራ ክሱ ፍርድ ቤት ቀረበ፡ ፡ ፍርድ ቤት ደግሞ ያን የፈጠራ ክስ ተቀብሎ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ በሌለበት ተፈረደብን፡ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ የቀረበብን በአደባባይ የተናገርናቸው ጥያቄዎች በፖለቲካ ድርጅታችን ውስጥ ያደረግናቸው ትግሎች፣ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው እንጂ በፍፁም ከሽብር ወንጀል ጋር በተያያዘ የቀረበብን ተጨባጭ ማስረጃ የለም። ስለዚህ እንድንታሰርና እንዲፈረድብን ስለተፈለገ ሽብርተኛ የሚል ተቀፅላ ተለጥፎብን ተፈረደብን። የተፈረደብን ስለተከሰስን ብቻ ነው እንጂ ማስረጃ ስለቀረበ አይደለም። መጀመሪያ እኔ፣ እስክንድር፣ አንዷለምና አበበ እንከራከር ወይስ አንከራከር ብለን ተወያይተን ነበር። እስክንድር እንኳን የሽብር ክስ አይደለም፣ ባለቤቴን ለማሳመን መከራከር አለብኝ። አሸባሪ እንዳልሆንኩ ለዓለም ማሳወቅ አለብኝ፤ የሚል ጠንካራ ሃሳብ ይዞ ቀርቦ ወደ ክርክር እንድንገባ ሆኗል።

መጀመሪያውኑ ላለመከራከር የፈለግንበት ምክንያት ፍርድ ቤቱና የፍትህ ሥርዓቱ ለአንድ ፓርቲ የወገነ በመሆኑ ነው። ስለዚህ በሽብርተኛ ታፔላ እንዲፈረድብን የተከሰስነው በፖለቲካ ትግሉ ውስጥ የኛ መኖር ስላላስፈለገ እንጂ ወንጀለኞች ስለሆነ እና ማስረጃ ስለቀረበብን አይደለም።

*ግዮን፡- ይቅርታ ሠነዱ ላይ ፈርሙ ተብላችሁ አንፈርምም ብላችኋል ፤ ብትፈርሙ ምንድን ነበር ችግሩ?*

ናትናኤል፡- ይኸውልህ እኛ የፍርድ እስረኞች ነን። ይህ የግፍ እስር መጀመሪያውኑም አንድም ቀን ልንታሰርበት የሚያስችል ጉዳይ አልነበረም። እንደገና ሕዝባችን ወገናችን ከፍተኛ ጉዳት የሕይወት የአካል የንብረትና የሞራል ጉዳት ከደረሰበት በኋላ የተገኘው የእስር መፈታት ውጤት እንጂ ኢህአዴግ በራሱ ተነሳሽነት ይቅር ባይ ሆኖ የፈፀመው አይደለም። ማነው ይቅርታ መጠየቅ ያለበት? ለምንድነው ይቅርታ የምንጠይቀው? ምን ስላጠፋን ነው ይቅርታ የምንጠይቅው? እንዲያውም የእውነት ይታይ ከተባለ ፍትህ ቢኖር ኖሮ እነሱ ናቸው ይቅርታ ሊጠይቁን የሚገባው። ይቅርታ ጠይቅ ሲባል እንደ ድፍረትም ነው የቆጠርኩት። ስለዚህ እንደሌሎቹ ባልደረቦቼ አልፈርምም ብያለሁ። ይሄን እምቢ ማለት አለብን፤ በፍፁም ለእውነት ብቻ መቆም አለብን፤ በዚህ ምክንያት የሚከፈልን ዋጋ ሁሉ መክፈል አለብን፤ የሚል የጋራ ስምምነት ስለነበረን ይሄን የጋራ አቋም ነው ወደ ተግባር ቀይረን ያለ ይቅርታና ምህረት የወጣነው።

*ግዮን፡- ቤተሰብ መስርተሃል?*

ናትናኤል፡- አዎ ባለትዳር ነኝ ሁለት ልጆች አሉኝ።

*ግዮን፡- ቀድሞ የነበረህ የፖለቲካ ተሳትፎ አሁንም ይቀጥላል? ወደፊት ምንድነው የምታስበው?*

ናትናኤል፡- እንግዲህ የጀመረውን የማይጨርስ ሰው እንደ ዓላማ ቢስ ሰው ይቆጠራል፤ ሳንታሰር የነበረው የለውጥ ጥያቄአችን እንደ ሕዝብም እንደ ድርጅትም አሁንም አለ አልተመለሰም። ስለዚህ በግፍ መታሰራችን ትግላችንን የበለጠ አጠናክረን ለመቀጠል ምክንያት ይሆነናል እንጂ ትግሉን እንድናቆም አያደርገንም።

*ግዮን፡- መስዋዕትነት እየከፈልክላት ላለችው አገርህ ምን ትመኝላታለህ?*

ናትናኤል፡- ለሕዝባቸውና ለአገራቸው ልዕልና የቆሙ ተቋማት ባለቤት እንድትሆን እመኛለሁ። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማኀበራዊ እሴቶችም የቀደመ ዝናና ክብሯን መልሳ የምታገኝበትና የዓለም ከፍታ ላይ የምትደርስበት ዘመኗን እመኝላታለሁ። የአገሬን ህልውና በጎሰኛና በአንድ ፓርቲ ይሁንታ ፍቃድ ላይ መሆኑ ቀርቶ በተቋሞቿ ጥንካሬና አቅም ላይ የሚመሰረትበት እንዲሆን ምኞቴ ነው። ሁሌም አንድ ገዥ ሥርዓት ችግር ላይ በወደቀ ቁጥር አደጋ ላይ የምትወድቅ አገር ሳትሆን ጠንካራ ተቋማዊ መሠረት ያለው ኅልውና የፈጠረች ዜጎችን የምታከብር አገር እንድትኖረኝ እፈልጋለሁ። እኔም ወዳጆቼም በመላ አገሪቱ ያሉ ዜጎች ዋጋ እየከፈሉ ያሉት ለዚህ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከተያዝኩበት ጊዜ ጀምሮ በአገር ውስጥም ከአገር ውጪም የምትገኙ ኢትዮጵያውያን፤ በወቅቱ የነበረው የአንድነት አባላትና አመራሮች የኔን ሞራል ለመጠበቅ ቤተሰቦቼን በመደገፍ ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ድጋፍ በእውነት ምስጋናዬን ለመግለፅ ቃላት የለኝም። በጣም ነው የማመሰግነው። ቤተሰቦቼን ባለቤቴንና ልጆቼ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። በየፍርድ ቤቱና በየእስር ቤቱ ተንገላተዋል። ከኔ በላይ ታስረዋል ማለት እችላለሁ፤ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

# “ሁሌም ነፃነት ይናፍቀኛል”

ሴና ሰለሞን

**ግዮን፡- ሲና ሰለሞን የት ተወልዳ አደገች?**

ሲና፡- እሺ አመሰግናለሁ። ጭልሞ ወለጋ ደቡብ ቂቤ ወረዳ ተወልጄ እስከ 8ኛ ክፍል ከቆየሁ በኋላ አዲስ አበባ አጎቴ ጋር መጣሁ። ቀጣይ ትምህርቴንም ከአዲስ አበባ ሰበታ እየተመላለስኩ ተማርኩኝ።

**ግዮን፡- ወደ ሙዚቃው ጎራ እንዴት ተቀላቀልሽ?**

ሲና፡- ኢለመንተሪ እያለሁ ግጥም እሞክር ነበር። ኮሌጅም እያለሁ ሚኒሚዲያና ክበባት ላይ ስሰራ የፊልም የድራማ እንዲሁም የሙዚቃ ፍላጎቱ ከቀን ወደ ቀን እያደገ መምጣቱ የራሴን የጥበብ ውጤቶች እንድሰራ አድርጎኛል።

**ግዮን፡- በሙዚቃው ውስጥ ምን ያህል ጊዜ አሳለፍሽ**

ሲና፡-ከሙዚቃ ጋር አራት አመት የሚሆን አሳልፌአለሁ። ከእስር በፊት ሁለት አመት ማለት ነው።

**ግዮን፡- የታሰርሽበት ምክንያት ምን ነበር መቼ ነው የታሰርሽው ?**

ሲና፡- ጋዜጠኛ ነሽ በስውር የኦነግ በሆነው ቁሮ ሬዲዮ ድምፅ ላይ በጋዜጠኝነት ትሰሪያለሽ ተብዬ ነው። የምትሰሪው ሰውን ለትግል የሚያነሳሳ ወደ አመፅ የሚወስድ ነው ተባልኩኝ። ታህሳስ 3/2009 ዓ.ም እኔ ፊልም እየሰራሁ ነበር ካሳንችስ የነበረንን ሲን ቀረፃ አጠናቀን ወደ ፒያሳ ኤሊያና ሞል ለሌላ የሲን ቀረፃ እየተዘጋጀን እያለን በፌዴራልና በደህንነት ተያዝን።

**ግዮን፡-ስትያዥ ብቻሽን ነው ሌሎችም ነበሩ?**

ሲና፡- ከኤልያስ ክፍሉ ጋር ፊልምም ክሊፕም ፕሮዳክሽን በጋራ ነው የምንሰራው።

**ግዮን፡- ከዛ ወዴት ወሰዷችሁ?**

ሲና፡- ወደ ማዕከላዊ ወሰዱን

**ግዮን፡- ፍርድ ቤትስ አላቀረቡሽም?**

ሲና፡- አራት ወር ሙሉ በወር አንድ ጊዜ በየ28 ቀኑ ነበር ፍርድ ቤት የምንቀርበው ከዛ በኋላ ግን ለ3 ወር ያህል ዝም ብለን ነበር ቶርች ስንደረግ የቆየነው።

**ግዮን፡- ማዕከላዊ ብቻሽን ነበርሽ ከጨረሽ በኋላስ ወዴት ሄድሽ?**

ሲና፡- ማዕከላዊ ከጓደኞቼ ጋር ነበርኩ ወደ ቃሊቲ ነው የወሰዱን።

**ግዮን፡- ፍርድ ውሳኔ ላይ ደርሰሻል? ወይስ ክስሽ ተቋርጦ ነው?**

ሲና፡- ክሴ ተቋርጦ ነው። አራት ወር ከአንድ ሳምንት የፍርድ ቤት ቀጠሮ ከሰጡን በኋላ ነው ፍርድ ሂደት ላይ ሳለ ክሴ የተቋረጠው።

**ግዮን፡- የለቀቅሻቸው ዘፈኖችሽ ፖለቲካዊ ይዘት አላቸው?**

ሲና፡- እነሱ ናቸዋ እንደዛ የሚያስቡት። አንተ “ጠላት” የሚል ቃል በጥበብ ውስጥ ከተጠቀምክ ወደነሱ አቅጣጫ ይተረጉሙታል። “እኛን ነው ማለት ነው” ብለው ያስባሉ። የሰሩት ነገር አለ መሰለኝ የዘፈኑት አቅጣጫ ወደ ፖለቲካ አዙረው ከኦነግ ጋር ስም ሰጥተውት ነው በሃሰት ወንጅለው ለእስር የተዳረግኩት። ለዚህ ሁሉ ምክንያት አንደኛው ዜማ ላይ የነበረው ግጥም ነው።



**ግዮን፡- ግጥም አንቺ ነሽ የምትሰሪው? ከዘፈኖችሽ ውስጥ በአድማጩ በተለይ በኦሮሚያ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ስራሽ የትኛው ነበር?**

ሲና፡- አዎ እፅፋለሁ ግን ይሄኛው ላይ ያለው ግጥም ሌሎች የሰጡኝ እኔም ወድጄው የሰራሁት ቆንጆ ግጥም ነው። ሁሉም ተወዳጅ ናቸው ግን ይበልጥ በህዝቡ የተወደደው “አካሚንዲ ነጎምድሱ” ይመስለኛል።

**ግዮን፡- ከእሱ ውስጥ ጥቂት ግጥም በኦሮምኛ ንገሪኝና መልስሽ በአማርኛ ግለጭልኝ?**

ሲና፡- “አካሚንዲ ነጎምድሱ “በአማርኛ “ጠላት እንዴት ነው የሚደፋው” (ረጅም ሳቅ) ቀጥሎ “በጠመንጃ ነው” ያልነው (ረጅም ሳቅ) እና ጠላት እኛ ነን ወይ፤ እኛነን ወይ በጠመንጃ የምንደፋው አሉ እኔም እንግዲህ እናንተን ከመሰላችሁ ምን ይደረግ እሽ አልኩ (ሳቅ)።

**ግዮን፡- ወደ ቃሊቲ በመጣሽ ጊዜስ የነበረው ሂደት ምን ይመስላል?**

ሲና፡- ቃሊቲ ከገባን በኋላ ጠያቂ ቤተሰብ ሲመጣ በጣም አስቸጋሪ ነበር። የእስረኛ መብት የሚባል የለም። ይሄም ነፃነት ተብሎ ለሌሎች እስረኞች የሚሰጠው ነፃነት ለኛ የተከለከለ ነው። ከሌሎቹ እስረኞች ጋር ስንገናኝ በራሱ “ከአሸባሪ ጋር ለምን ትቀራረባላችሁ” ይሏቸው ነበር። እስር ቤት ውስጥ ያሉ ፖሊሶችና አመራሮች ጥሩ ነገር የላቸውም ለኛ። ግቢ ውስጥ እንደ ሰው አንቆጥርም። በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ነበር። ቤተሰብ ራሱ በግድ ነው ያስመዘገብነው። ከክፍለ ሀገር ድረስ ቤተሰቦቼ መጥተው ይመልሷቸዋል። ቃሊቲ ምንም ጥሩ ነገር አልነበረም እውነቱን ለመናገር።

**ግዮን፡- ፍርድ ቤት ቀርባችሁ መበደላችሁን መገለል እንደደረሰባችሁ አልተናገራችሁም?**

ሲና፡- ፍርድ ቤት ምንም ተስፋ የለህም። ለዜጎች ፍትሃዊነት ተብሎ ታስቦ የተዘጋጀ ሳይሆን ለዜጎች ማፊኛና ለእነሱ ፍላጎት ማርኪያ የተቋቋመ ቦታ ስለሆነ ተስፋ አይኖርህም። ችግራችንን በደላችንን እየተፈፀመብን ያለውን ኢሰብዐዊ ድርጊት ሁሉ ተናግረናል ግን ሰሚ ጆሮ አልነበረም። የአንድ ወገን ድምፅ ብቻ የሚሰማበት ተስፋ አስቆራጭ ቦታ ነበር።

**ግዮን፡- የእስር ግዜሽን ምን እያደረግሽ ነበር የምታሳልፊው?**

ሲና፡- አንዳንድ ጊዜ ሲገኝ አነባለሁ ከዛ ውጭ ግን ሙያዊ ነገሮችን በመስራት ለምሳሌ ዳንቴል በመስራት ነበር የማሳልፈው።

**ግዮን፡- ከአሁኑ በፊት እስር ቤት ታስረሽ ነበር?**

ሲና፡- ኮሌጅ እያለሁ ታስሬአለሁ። በ2000 ዓ.ም ለብዙ ወራት ታስሬአለሁ። ለአንድ አመትም ከትምህርት ታግጄአለሁ።

**ግዮን፡- ሙዚቃ ሙሉ አልበም አለሽ ወይስ ነጠላ ዜማዎች ናቸው?**

ሲና፡- አልበም የለኝም። ነጠላ ዜማዎችን ነው ሰርቼ የምለቀው። ሰባት ዜማዎች ከነ ክሊፖቸው ሰርቻለሁ።

**ግዮን፡- ድራማ ፊልም ሰርተሻል?**

ሲና፡- አዎ በኦሮሚያ ቴሌቪዥን ላይ ሰርቻለሁ። በዛ ያሉ ድራማዎችም ፊልሞችም ሰርቻለሁ።

**ግዮን፡- በጥበብ ስራዎች ላይ ነፃነትን ፍትህን የጠየቅሽባቸው አሉ ወደፊትም ትገፊበታለሽ? የወደፊት አላማሽ ምንድን ነው?**

ሲና፡- ከዚህ በኋላ ይበልጥ መስራት እፈልጋለሁ። አሁን ራሱ ጀምሬአለሁ። ፊልምና ዘፈን እየሰራሁ ነው። ምንም ወደ ኋላ የሚመልሰኝ ነገር የለም።

**ግዮን፡- በፖለቲካ እስረኛ ሆነሽ ከቆየሽ በኋላ ተፈተሻል። ከተፈታሽ በኋላ የሀገሪቱን ሁኔታ እንዴት ታዘብሽው? ምን ትመኝላታለሽ ለሀገርሽ?**

ሲና፡- ነፃነትን በጣም ነው የምመኘው። እውነቱን ለመናገር ሀገራችን እና ህዝባችን በዴሞክራሲ በነፃነት በእኩልነት እጦት እየተሰቃየ ይገኛል። ዲሞክራሲ የለም። አድሎና ጭቆና በርትቷል። ፍትህ የሚባል ነገር የለም። በወሬ ደረጃ ነው እንጂ በተግባር ለውጥና ፍትህ አይቼ አላውቅም። የኛ ፖለቲካ ደግሞ እስር ላይ ነው። እኔ አሁን ከእስር ተፈታሁኝ እንጂ የኛ ፖለቲካ ግን አሁንም እስር ላይ ነው። ሀገሪቱ እስር ላይ ናት። ህዝቡ አፈና ላይ ነው። ሰው ነው እየተፈታ ያለው እንጂ ፖለቲካችን ግን አልተፈታም። ስለዚህ ሁላችንም እንደ ኢትዮጵያዊነታችን የበኩላችንን አስተዋፅኦ እንደየ ሙያችን በማድረግ የታሰረች ሀገራችንን ማስፈታት አለብን። ለሁሉም የምትበጅ ሀገር መመስረት አለብን።

**ግዮን፡- ደምቢዶሎ የነበረሽን አቀባበል ምን ይመስል ነበር? ምን ተሰማሽ?**

ሲና፡- እኔ በጣም ነው የሚከብደኝ። ከነቀምት ጀምሮ ሺቁሳ ጊምቢ አይራ ጉልሶ አለምተከሊ ጫንቃ ቃቄ ደውቂዶ ከሌሎች ብዙ ካልጠቀስኳቸው ቦታዎች ነበር የመጡት ያልመጣ የለም። ደስ ነው ያለኝ። መንግሥት ሽብር ብሎ ነው ያሰረን። ህዝቡ ደግሞ እኛን ጀግኖቻችን ብሎ እንደዚህ ሲቀበለን ደስ ነው ያለኝ። ኸረ ኩራትም ተሰምቶኛል። የህዝብ ልጅን የመሰለ ነገር የለም። በሌላ አባባል አሸባሪ አይደሉም ማለቱ እኮ ነው ህዝቡ። እነዚህ ልጆች ሽብር አልሠሩም ነፃነትን ነው የጠየቁት ብሎ ነው ህዝቡ በተግባር የገለፀው። →

ግዮን፡- ለህዝቡ ምን ያስተላለፊሽው የተናገርሽው ነገር ምን ነበር?

ሲና፡- ከነቀምት ጀምሮ የሚቀበለኝን ህዝብ መልዕክቴን ሀሳቤን እያስተላለፊኩ ነው የተጓዝኩት፡፡ ሁሉም ቦታ ከህዝቡ ጋር ተቀላቅዬ የተናገርኩት እኛ ትላንት ስንጮኽህለት የነበረው ለነፃነት ለፍትህ ነው፡፡ ዛሬም ነገም የምንጮኸው የምንቀሳቀሰው ለነፃነትና ዴሞክራሲ የሠፈነበት እኩል ሀገር እንድትኖረን ነው፡፡ ከዚህ በኋላም መታሰር ወደ ኋላ አይመልስንም፡፡ ባለን እውቀትና ችሎታ ስራችንን እንሰራለን፡፡ ነፃ አስተዳደር እና የተባበረች ሀገር እስክትኖረን ድረስ አሁንም እንታገላለን እያልኩ ነው ወደ መጨረሻ ጉዞዬ የደረስኩት፡፡

ግዮን፡- ከዚህ በኋላም ይሄ እስር ለፃነትና ለዴሞክራሲ የማደርገውን ትግል አይገድበኝም እያልሽ ነው ያለሽው? ይሄ እስር አንቺን አይገድብሽም?

ሲና፡- አዎ አይገድበንም፡፡ እስር ነፃነት ለማግኘት የምታደርገውን ትግል አይገድብም ያጠነክረዋል እንጂ፡፡ ምንም አያግደኝም ታሰርኩ ተፈታሁ፡፡ አሁንም ነፃነት የለኝም፡፡ ባለኝ አቅም ጉልበት እና እውቀት እቀጥላለሁ የታሰረው ሕዝብና ሀገር እስኪፈታ ድረስ፡፡

ግዮን፡- ከእስር እንደምትለቀቂ ስታወቂ ምን ተሰማሽ?

ሲና፡- ምንም አልደነቀኝም፡፡ ሁሉ ነገሩን የተቀማ ሕዝብ ጮሆ ነው ያሰፈታኝ፡፡ ውድና የማይተካ ነፍሱን ሰውቶ ደምቶና ቆስሎ ንብረቱን መስዋዕት አድርጎ ነው ያስፈታኝ፡፡ ሁላችንንም ያስፈታን፡፡ መንግሥት ሲጨነቀውና ግፊቱ ሲበረታበት በምህረትና በይቅርታ አሳብቦ ፈታን፡፡ በተለይ የቄሮዎች (የወጣቶች) የመስዋዕትነት ትግል ፍሬ ውጤት ነው ለዚህ ያበቃኝ፡፡

ግዮን፡- የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲሰፋ በአጠቃላይ ምን መደረግ አለበት ብለሽ ታምንያለሽ?

ሲና፡- ኢትዮጵያ የእኩልነት የነፃነት የፍትሃዊነት ሀገር መሆን አለባት፡፡ በጎሳ በብሔር መከፋፈሉ ሳይመለስ ተቀርፎ ሁሉንም ብሔር ጎሳ በእኩል አይኗ የምትመለከት ኢትዮጵያን ለመፍጠር መስራት አለብን፡፡ ከጎሳና ብሔር በፊት ኢትዮጵያዊነት መዘመር ከፍ ማለት አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ በጋራ በአንድ አትዮጵያዊነት ተባብረን መታገል ይኖርብናል፡፡

ግዮን፡- እስር ቤት ሆነሽ የሚናፍቅሽ ነገር ምንድን ነው?

ሲና፡- ነፃነት

ግዮን፡- በመጨረሻ የምታስተላልፊው መልዕክትና ምስጋና ካለ እድሉን ውሰጂ?

ሲና፡- ከምንም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፡፡ እኔ በጣም ማመስገን የምፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብን ነው፡፡ የማስተላልፈው መልዕክት አሁንም ቢሆን በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ያልተፈቱ ወገኖች በመላ ሀገራችን አሉ፡፡ ሁሉም መፈታት አለባቸው፡፡ እኛ ከዚህ በኋላ ጥያቄአችን ህዝብና ሀገር እንድትፈታልን ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡ የሚይስፈራኝ ነገር የለም ትግል ይቀጥላል፡፡ ለነፃነታችን መታገል እንዳለብን ነው የምናገረው፡፡ በሽብር ብቻ አይደለም በግፍ፣ በሀሰት ውንጀላ 20 እና 25 አመት ያለጠያቂ ያለጧሂ የቆዩ አሉ፡፡ ለእነሱ መቆርቆር ጠያቂ የሌላቸውን መጠየቅ እንዲፈቱ ግፊት ማድረግ ከእኛ ይጠበቃል፡፡ መንግሥትም እኔ ነኝ ያጠፋሁት ብሎ አምኗል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም የግፍ እስረኞች መፍታት አለበት፡፡



# ‘‘የምሰራው ስራ ከፖለቲካ ጋር አያገናኘኝም’’

## ኤልያስ ክፍሌ

ግዬን፡- ራስህን በማስተዋወቅ እንጀምር?

ኤልያስ፡- ኤልያስ ክፍሉ እባላለሁ፡፡ የተወለድኩት በኦሮሚያ ልዩ ዞን መናገሻ ማርያም አካባቢ ኮሎቦ በሚባል ቦታ ነው፡፡

ግዬን፡- በምን ሙያ ላይ ነው የተሰማራኸው?

ኤልያስ፡- ብዙ ስራ ነው የምሰራው፡፡ ብዙ የሙያ ኮርሶችንና ስልጠናዎችን ከወሰድኩ በኋላና ያለኝን ነገር ካዳበርኩ በኋላ በሙዚቃ ክሊፕ ፕሮዳክሽን የተለያዩ ፊልሞችን እና ተከታታይ ድራማዎችን ሠርቻለሁ፡፡ ራሴንም የሙዚቃ ክሊፕ ሰርቻለሁ፡፡ መስፍን ጫላ ከሚባል ጓደኛ የጋራ አልበም ጀመሪያለሁ፡፡ በጎን ደግሞ የፕሮዳክሽን ስራ እየሠራሁ ነው፡፡ በስራውም ደስተኛ ነኝ፡፡

ግዬን፡- የታሰርከው መቼ ነው የእስሩ ምክንያት ምንድን ነው?

ኤልያስ፡- ታህሳስ 3/2009 ስራ ላይ በነበርኩበት ሰዓት ነው፡፡ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ቀረፃ ላይ እያለሁ ነው የተያዝኩት፡፡ OBS ላይ የአየር ሰዓት ነበረኝና ለዛ ግብአት (ሲን) ቀረፃ ላይ እያለሁ ፒያሳ ኢልያና ሞል አካባቢ በደህንነቶችና በታጣቂዎች ተከበን ተያዝን፡፡ ምክንያቱ ሽብርተኛ ነህ የሚል ነበር፡፡

ግዬን፡- ከዛ ወዴት ተወሰድክ?

ኤልያስ፡- ወደ ማዕከላዊ ወሰዱን፡፡ አብረውን የታሰሩ የነበሩ አምስቱ ተለቀቁ፡፡ እኔ እና የኔ ፕሮዳክሽን ማናጀር የሆነችው ሲና ሰለሞን ሁለታችን ገባን፡፡

ግዬን፡- የማዕከላዊ ቆይታህ እንዴት ነበር?

ኤልያስ፡- ብዙ አስጨናቂ ነገሮች ነበሩ፡፡ እዚህ ቦታላይ እገኛለሁ ብዬ አላሰብኩም፡፡ የምሰራው ስራ ከፖለቲካ ጋር ያገናኛል ብዬ ስለማስብ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም እኔ የምሰራው ጥበብ ነው፡፡ ጥበብ ላይ ደግሞ በህገ መንግሥቱ የመናገር የመግለፅ መብትን አይገድብም፡፡ ጥበብ ከህዝብ ለህዝብ ናት፡፡

ግዬን፡-ማዕከላዊ ምን ያህል ጊዜ ቆየህ?

ኤልያስ፡- ከ6 ወር በላይ ቆይቻለሁ፡፡ በጣም አሳዛኝና አስቃቂ ነገሮች አሳልፌአለሁ፡፡

ግዬን፡- እስኪ የደረስብህን ግለፅልኝ?

ኤልያስ፡- ሳይቤሪያ ከሚባለው ቦታ ተነስቶ እስከ ሸራተን ያለፍንበት ህይወት ዘግናኝ ነበር፡፡ ምናልባት ትንሽ የተሻለ የሚባለው ሸራተን ነው፡፡ ሳይቤሪያ 24ሰዓት ተዘግቶብህ ነው፡፡ ሰው ነህና ብርሃን ትፈልጋለህ፡፡ ያች ብርሀን ደግሞ የ10 ደቂቃ ናት፡፡

ግዬን፡- የተከሰስከው ምን ፈፅምሃል ተብለህ ነው?

ኤልያስ፡- ህዝቡን የሚያነሳሳ ወደ አመፅ የሚገፋፋ የጥበብ ስራዎችን ሰርተሃል፡፡ ዘፈነሃል ነው የሚለው፡፡ በተጨማሪም ኢሜይሌ ላይ ሰዎች ስብስክራይብ እያደረጉ ፅሁፍ ይለቃሉ፡፡ ያን እንደ ማስረጃ ተጠቅመው ጥፋተኛ ተብያለሁ፡፡ የሚገርም አንድም ቀን ኢሜይሉን ከፍቼው ተጠቅሜበት አላውቅም፡፡ ግን የግል ኢሜይል ላይ አይደለም የኢሜይል ገፁ ላይ በሚለቀቁ ነገሮች ነው የተከሰስኩት፡፡ ምንም በጭራሽ ሊመለከቱኝ በማይችሉ ነገሮች፡፡

ግዬን፡-ህክምና የማግኘት እድሉ ነበር?

ኤልያስ፡- ህክምና ምን ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በመጨረሻ ህመሜ የባሰ ደረጃ ላይ ሲደርስ ፖሊስ ሆስፒታል ተላኩኝ፡፡ ሁሉንም ነገር አዩኝ፡፡ ሊረዱኝ ሞከሩ፡፡ ጀርባህ ላይ ያለው ኦፕራሲዮን እናደርግህ ብለውኝ ነበር፡፡ ግን እኔ ማስደረግ አልፈለኩም፡፡ ምክንያቱም ቦታው አይመችም፡፡ ኦፕራሲዮን ከተደረኩ በኋላ የምመለስበት ቦታ እስር ቤት ስለሆነ ፈቃደኛ አልሆንኩም፡፡ ቂሊንጦ ከወረድኩ በኋላ ህክምና ጠየኩኝ፡ ፡ ሊልኩኝ አልቻሉም፡፡ ማስታገሻ ብቻ ነበር ደጋግመው የሚሰጡኝ፡፡ ቤተሰቦቼ የሚያመጡልኝ መድሃኒት ብቻ ነበር ለስጠቀም የነበርኩ፡፡

ግዬን፡-አሁን ከወጣህ በኋላ ጤናህ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

ኤልያስ፡- ህክምና እየተከታተልኩ ነው

ግዮን፡- ከተፈታህ በኋላስ ያለህ ስሜት ምን ይመስላል?

ኤልያስ፡- መፈታቴ ደስ ቢለኝም፡፡ እኔ ብፈታም የህዝብ የማያቋርጥ ጥያቄ አልተመለሰም፡፡


ግዮን፡- የህዝብ ጥያቄ ብለ የምታምንባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

ኤልያስ፡- በነፃነት ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብትን እኩልነት የተጠቀሚነት መብትን የጋራ ሀገር መገንባትን በፊንፊኔ ዙሪያ ሉት መፈናቀሎች ያሳዝኑኛል፡፡ የበተሰብ መብትን ያለ በቂ ካሳ በጉልበትና በህግ ንብረታቸውንተቀምጠው ቤተሰባቸው መበተኑ ያሳሰበኛል፡፡ የሚፈናቀለው አርሶ አደር ያሳስበኛል፡፡

ግዮን፡- ማስተላለፍ የምትፈልገው የምታመሰግነው ነገር ካለ?

ኤልያስ፡-መንግሥት የሕዝቡን ጥያቄ ማዳመጥ መመለስ አለበት ብዬ አስባለሁ፡፡ መንግሥት የህዝቡን ጥያቄ ሲመልስ በተጨባጭ ማየት የምንችለው ነገር መሆን አለበት፡፡ መሰረት ድንጋይ ጣልኩ ብለህ ነፋስ ላይ ሪቫን አትቆርጥም፡፡ ስለዚህ ነፋስ ላይ ሪቫን አትቆርጥም፡፡ ስለዚህ በተጨባጭ ህዝቡን የሚፈልገውን ነገር አሳይቶ ለውጥ ማየት መቻል አለብን፡፡

በመጨረሻም ከቤተሰቤ ጋር እንድቀላቀል የኦሮም ህዝብና ቄሮ ያደረጉትን ተጋድሎ ያልተቁረጠ መስዋዕትነት ከፍለው ግፊት አድርገው ከእስር እንድፈታ ስላደረጉልኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡



በፍቃዱ ዘ ሀይሉ

# የፍቺው ዜና የፈጠረው ተስፋ

የፖለቲካ እስረኞች ዜና ጥር 25፣ 2010 ነበር መጀመሪያ ማኅበራዊ ሚድያዎችን ያጥለቀለቀው። ዜናው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የፌስቡክ እና የትዊተር ገጾች መጀመሪያ ሲለቀቅ "ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈታሉ" በሚል ነበር። ነገር ግን ቆየት ብሎ በአርትኦት ታርሟል። በርግጥም ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ለፌዴራል መንግሥቱ ጋዜጠኞች ብቻ ክፍት በነበረው የአራቱ ገዢ ፓርቲዎች ጥምር መግለጫ ላይ የተናገሩት የፖለቲከኛ እስረኞች የሚለውን ቃል በቀጥታ አልተጠቀሙም ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉት "በራሳቸው ጥፋት የተፈረደባቸው ፖለቲከኞች እና ሌሎችም ግለሰቦች" ነበር። ብዙዎቹን የውጭ አገር ብዙኃን መገናኛዎች ያስገረማቸው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ መንግሥት የፖለቲካ እስረኞች መኖራቸውን ማመኑ ነበር።

ኤንፒአር የተባለ አሜሪካ ብዙኃን መገናኛ የፍቺውን ዜና "ተቃዋሚዎች ላይ ጨካኝ እርምጃ ሲወስድ ለከረመው እና ከዚህ ቀደም የፖለቲካ እስረኞች እንዳለው ላላመነው መንግሥት አስገራሚ አክሮባት ነው" ሲል ነበር የገለጸው።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት መግለጫውን ባወጣ ማግስት ጠቅላይ ሚኒስትሩ "የፖለቲካ እስረኞች" የሚል ቃል ሳይጠቀሙ እንደተጠቀሰባቸው ጠቅሶ እርምት ጠይቋል። በዚህም መሠረት ቢቢሲ የእንግሊዝኛ ድረገጹ ላይ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖለቲካ እስረኞች ይፈታሉ አሉ" በሚል የዘገበው በስህተት የተጣቀሰ መሆኑን አስተካክሎ እስከማተም ደርሷል።

መንግሥት ፍቺውን ለማድረግ የወሰነው "የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማስፋት እና አገራዊ መግባባት ለመፍጠር" እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመግለጫቸው አክለው ገልጸው ነበር። በርግጥም የደረቅ ወንጀለኞች መፈታት ለነዚህ ሁለት ግቦች የሚያበረክተው ነገር የለም። ይሁን እንጂ ተቃዋሚዎች "የፖለቲካ እስረኞች" የሚሏቸው ሰዎች ከተፈቱ ግን ለአገራዊ መግባባት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ያደርጋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ "የፖለቲካ እስረኛ" የሚለውን ለመጠቀም አለመድፈራቸው አስገራሚ ነገር አይደለም። በኢትዮጵያ ሕግ ፖለቲካዊ ወንጀል ብሎ ነገር የለም። ስለሆነም፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግሥታቸው በፖለቲካ አመለካከታቸው ዜጎችን እንዳሰረ ቢያምኑ በውጤቱ ተጠያቂ መሆናቸው አይቀሬ ነበር። ራሳቸው ላይ እንደመመስከር ነው የሚቆጠርባቸው። ከዚህ ተጠያቂነት ለማምለጥ ሲባል ይህንን መካዳቸው ሐቅ ባይሆንም የሚጠበቅ ነው። ይህንን በመረዳት ይመስላል፣ የእርምት መግለጫው ከወጣም በኋላ ብዙዎቹ የውጭ ብዙኃን መገናኛዎች "የፖለቲካ እስረኞች" እያሉ መዘገባቸውን የቀጠሉበት።

የፍቺው ዜና መውጣት ከፍተኛ ተስፋ የሰጣቸው ተቋማትም ነበሩ። ‹ዴሞክራሲ ኢን አፍሪካ› የተባለ ስለአፍሪካ ዴሞክራሲ የሚያጠና ድርጅት ዜናውን "ከመልካምነቱ የተነሳ እውነት የሚሆን የማይመስል" ነበር ያለው። በዜናው ከተደሰቱት ድርጅቶች ውስጥ የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን ያክል ግን ትልቅ ተስፋ የሰነቀ አልነበረም። አምነስቲ በተለይ ማዕከላዊ በመባል የሚታወቀው እና ብዙ ሰዎች የተሰቃዩበት የወንጀል ምርመራ ማዕከል ተዘግቶ ሙዚየም ይሆናል መባሉን እንደትልቅ እርምጃ ወስዶታል። አምነስቲ በዕለቱ ባወጣው መግለጫ "የማዕከላዊ መዘጋት ለኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብቶች አያያዝ አዲስ ምዕራፍ መከፈቱን ያበስራል" ነበር ያለው።

የአገር ውስጥ ብዙኃን መገናኛዎች ለእስረኞቹ መፈታት ውሳኔ ‹የሕዝባዊ ተቃውሞዎች ተፅዕኖን› በመጥቀስ ቀላል መልስ ለመስጠት ሲሞክሩ፣ የውጭዎቹ ግን ብዙ ምክንያት ፈልገውለታል። አልጀዚራ ላይ ቴምቢሳ ፋኩዴ በተባለ ተመራማሪ የተጻፈ ጽሑፍ "የአፍሪካ ኅብረት አባል አገራቱ ሰብኣዊ መብት እንዲያከብሩ ያደረገው ጥረት አንድ ውጤት" ሊሆን እንደሚችል ጠቅሷል። ይሁን እንጂ ሐቀኛው ምክንያት የአፍሪካ ኅብረትን ፍላጎት ማሟላት ብቻ እንዳልሆነም ተመራማሪው ይጠቃቅሳሉ። ኤርትራ እና ሶማሊያ የትጥቅ ትግል ለመረጡ ኢትዮጵያውያን መጠለያ በመስጠት በአገር ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደሚገቡ ያስታወሱት ጸሐፊው፣ ኢትዮጵያ እስረኞችን በመፍታት ይህንን ውጥረት በማርገብ በኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞቿ ላይ ማተኮር ትፈልጋለች ይላሉ። በሦስተኝነትም የሕዳሴውን ግድብ ይጠቅሳሉ። ግብጽ ተቃዋሚዎችን በመርዳት ሰበብ የሕዳሴውን ግድብ ግንባታ እንዳታስተጓጉል ኢትዮጵያ ለተቃዋሚዎቿ ምኅዳሯን ማስፋት አለባት በማለት።

እነዚህ ትርክቶች በአገር ውስጥ ካለው ይልቅ በውጪ አገራት ዘንድ በኢትዮጵያ የለውጥ ተስፋ እየፈነጠቀ እንደሆነ የሚያስመስሉ በርካታ ዜናዎች እንዲዘገቡ አድርጓል።

> **...ኤርትራ እና ሶማሊያ የትጥቅ ትግል ለመረጡ ኢትዮጵያውያን መጠለያ በመስጠት በአገር ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደሚገቡ ያስታወሱት ጸሐፊው፣ ኢትዮጵያ እስረኞችን በመፍታት ይህንን ውጥረት በማርገብ በኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞቿ ላይ ማተኮር ትፈልጋለች...**

ምንም እንኳን ብዙ የሚታወቁ እና የማይታወቁ የፖለቲካ እስረኞች እስካሁንም ድረስ በየእስር ቤቶቹ ቢኖሩም፣ መግለጫው ከተሰጠበት ጊዜ ወዲህ ብዙ ዕውቅ እና ሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች መፈታታቸውን ቀጥለዋል። የዕድሜ ልክ ፍርደኞችን ጨምሮ ሌሎችም ለረዥም ዓመታት የተፈረደባቸው የፖለቲካ እስረኞች ተለቅቀዋል። ቀሪዎቹ የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ጨምሮ ዕውቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና ፖለቲከኛው አንዷለም አራጌ የካቲት 7፣ 2010 መፈታታቸው ትልቅ ሰበር ዜና ነበር። ክሳቸው በሒደት ላይ የነበሩት የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ አመራሮች በቀለ ገርባ እና ሌሎችም በዋዜማው ተፈትተዋል። በተመሳሳይ ‹የወልቃይት የአማራ ማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ› አባላትም ክሳቸው ተፈትተው ከተለቀቁት ውስጥ ይቆጠራሉ። ይህንን ብዙዎቹ የውጭ ብዙኃን መገናኛ ብዙኃን ሁሉም እስረኞች ለመፈታታቸው እንደማሳያ አድርገው ወስደውታል።

ሲፒጄ እ.ኤ.አ. በ2018 ባወጣው የታሰሩ ጋዜጠኞች ቆጠራ ሪፖርቱ አምስት ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች መታሰራቸውን ገልጾ ነበር። ከአምስቱ ውስጥ ጋዜጠኞቹ ዳርሰማ ሶሪ እና ካሊድ ሰይድ እንዲሁም ጦማሪ ዘላለም ወርቃገኘሁ የእስር ግዜያቸውን ጨርሰው በአመክሮ የተፈቱ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ሁለቱ - ማለትም ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ - በአዲሱ ፍቺ በመለቀቃቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የታሰረ ጋዜጠኛ የለም የሚል ሪፖርት አውጥቷል።

ብዙዎቹ ዕውቅ የፖለቲካ እስረኞች ረቡዕ ተፈትተው፣ ሐሙስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመልቀቂያ ደብዳቤ ማስገባታቸውን መናገራቸውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ማስተካከያ እርምጃ አድርገው የወሰዱት ብዙዎች ናቸው። ይህ በእንዲህ እያለ፣ አርብ በኢትዮጵያ አስቸኳይ ግዜ ዐዋጅ መጣሉ ብዙ ሚዲያዎችን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ቀውስ ውስጥ እንደሆነ እንዲዘግቡ አስገድዷቸዋል።

‹ሂዩማን ራይትስ ዎች› የፖለቲካ እስረኞቹ ፍቺ ዜና በተሰማ ዕለት ባወጣው መግለጫ የእስረኞቹ መፈታት ወሳኝ እርምጃ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ ገልጧል። መግለጫው በመዝጊያ አንቀጹ እንዳለው "የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብኣዊ መብቶች አያያዙን ማስተካከልም ይጠበቅበታል። ይህም ሠላማዊ ተቃውሞዎችን መፍቀድን እና አፋኝ ሕጎችን መከለስን ይጨምራል። በተጨማሪም የውጭ መገናኛ ብዙኃንን ማግለል እና መገደብ ማቆም አለበት። ከታኅሣሥ ወር አጋማሽ ጀምሮ በብዙ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተቋረጠውን የበይነመረብ አገልግሎትን መመለስም ያስፈልጋል። እነዚህ ማስተካከያዎች የገዢው ፓርቲ ዜጎቹን በማድመጥ፣ አፈናን በማቆም ሰፊ የሰብኣዊ መብቶች ክብር ለማጎናፀፍ ያለውን ፈቃደኝነት ያሳያሉ።"

ግዮን
መጽሔት

ግዮን መጽሔት
በየ15 ቀን ቅዳሜ
ይጠብቁዋት!

ድርጅትዎንና
አገልግሎትዎን
ያስተዋውቁ!

በቀጣይ
ዕትማችን
የተመረጡ
አምዶቻችንን
ይዘን እንመጣለን

ፃፉልን፣
አስተያየት
ይስጡ ምልሻችን
ፈጣን ነው




ስልክ : +251 912165606
+251 912165606
ኢ-ሜይል: gihonmeg@gmail.com
Facebook: gihon2010meg@gmail.com